አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና የኮምኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ‹‹በእብናት ወረዳ ከባህላዊ ወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና››

በ

ጋሻው አሻግሬ

የፈተና ቦርድ

አማካሪ ፊርማ

[illegible] ______

የውስጥ ፈታኝ [illegible] ______

የውጭ ፈታኝ [illegible] ______

ሰኔ 04/ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|


ማውጫ ..... i

ምስጋና ..... iii

ሙዳዬ ቃላት ..... v

አጠቃሎ ..... vi

1 መግቢያ ..... 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 2

1.2 የጥናቱ ዓላማዎች ..... 2

1.2.1 የጥናቱ ዋና አላማ ..... 2

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች ..... 2

1.3 ጥናቱ የመለሳቸው የምርምር ጥያቄዎች ..... 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3

1.5 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እና የመተንተኛ ስልት ..... 3

1.5.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 4

1.5.2 የመረጃ መተንተኛ ስልት ..... 7

1.6 የጥናቱ ወሰን ..... 8

1.7 በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ..... 9

1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች ..... 9

1.7.2 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ..... 10

1.8 የመስክ ተሞክሮ ..... 11

2 ክለሳ ድርሳናት ..... 15

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 15

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ..... 24

2.2.1 የቃል ግጥም ምንነት ..... 24

2.2.2 የቃል ግጥም ተስተላልፎ ..... 24

2.2.3 የቃል ግጥም ባህርያት ..... 26

2.2.4 የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ..... 27

3 የጥናቱ አካባቢ ..... 32

3.1 የእብናት ወረዳ ..... 32

3.2 መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ..... 32

3.3 የህዝብ ስርጭት እና ማህበራዊ ግንኙነት .......... 33
3.4. ኢኮኖሚ .......... 34
3.5. መሰረተ ልማት .......... 35
3.6. የነዋሪዎቹ የስራ ክፍፍል .......... 35
4.በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና .......... 38
4.1.ምሬትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች .......... 38
4.1.1.የወፍጮ ስራ ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች .......... 38
4.1.2. ሴት በመሆን የሚደርሱ ምሬቶችን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች .......... 45
4.1.3. እድልን እጣ ፈንታንና በልጅነት መዳርን የሚያማርሩ ቃል ግጥሞች .......... 49
4.2 ውዳሴን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች .......... 56
4.2.1. እናትን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች .......... 56
4.2.2. እርሻ ማረስን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች .......... 60
4.2.3. አገርን የሚያወድሱ ቃልግጥሞች .......... 65
4.2.4. የአካባቢ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች .......... 69
4.3. ፍቅርን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች .......... 74
4.4.ንቀትና ጥላቻን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች .......... 78
4.5.2. የጐባንን ክፋት የሚገልፁ ቃል ግጥሞች .......... 85
5.ማጠቃለያ .......... 89
ይሁንታ .......... 91
ዋቢ ጽሑፎች .......... 92
አባሪ አንድ፡-ሀ/ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር .......... 96
አባሪ አንድ ለ/ አጋዥ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር .......... 98
አባሪ አንድ ሐ/ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር .......... 101
አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ ሰጭዎች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች .......... 102
አባሪ ሁለት ሀ/ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች .......... 102
አባሪ ሁለት ለ/ ለአጋዥ መረጃ ሰጭዎች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች .......... 103
አባሪ ሁለት ሐ/ ለቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የቀረቡ መሪ ጥያቄዎች .......... 104
አባሪ ሶስት - ከመስክ የተሰበሰቡ ቃልግጥሞች .......... 105
አባሪ አራት - ካርታዎች .......... 150
አባሪ አምስት - ፎቶግራፎች .......... 152

# ምስጋና

ከድንቁርና ህፀፅ እወጣ ዘንድ የእውቀትን መቅረዝ እያበሩ የግድፈትን ጨለማ ለአሻገሩኝና ለባዘኑልኝ ለጥበብ አባቴ ለዘሪሁን አስፋው ለእርስዎ የሚበቃ የአንደበት ምስጋና ባይኖረኝም ልዑል እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት እና ለረጅም ወራት ይጠብቅልኝ እያልኩኝ መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ።

ከመጀመሪያ አንስቶ ትብብራችሁና ቀና አስተሳሰባችሁ ላልተለየኝ ለእብናት ወረዳ ነዋሪዎች ምስጋና አቀርባለሁ። ጥናቱ ተጠንቶ እስኪጠናቀቅ ከቤታችሁ በመጐዝጐዝ፣ በመጥመቅና በመጋገር ጮማውን እየቆረጣችሁ፣ ማሩን እየጠመቃችሁ ላስተናገዳችሁኝ የድርቋዝባ ነዋሪዎች ለቄስ ወርቁና ለባለቤቱ ለወ/ሮ አበራሽ ንጋቱ፣ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ይህ ጥናት ዳር ይዘልቅ ዘንድ መረጃ በመስጠት፣ መንገድ በመምራት ለተባበራችሁኝ ለወ/ሮ አስረብብ አለቤ፣ ለወ/ሮ ደብሬ አለሜ፣ ለወ/ሮ እርጎዬ ለገሰ፣ ለወ/ሮ አስካል ቀለሙ፣ለተማሪ ክቴ ደመቀ፣ ለወ/ሪት ወርቅዬ ለገሰ፣ ለወ/ሮ ውብነሽ ታከለ፣ ለወ/ሮ እናት ንጋቱ፣ ለአቶ መላሽ ታፈስ እና ለአቶ አረጋ አበራ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ እላለሁ።

ለጥናቱ መሳካት በሐሳብና በገንዘባችሁ ለደገፋችሁኝ ውድ እህቶቼ ለወ/ሪት አምሳል ተስፋውና ለወ/ሪት ጌጤ ተስፋው ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። በገንቢ ሐሳብ ስኬትና ጥረት ሁሌም ከጎኔ ላልተለያችሁኝ ለወ/ሮ ፋንታነሽ ለገሰና ሀብለወርቅ ጋሻው ሰላሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ።

በፀሎት እና መልካም ምኞት ዘወትር ለምታስቡኝ ውድ ዘመዶቼ ለማሆይ ሙሉ ደሴ፣ ለአባቴ አቶ አሻግሬ ገላዬ፣ ለአቶ ለገሰ አለሙና ለአቶ ተስፋው ቀለሙ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

# አበርክቶት

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ፀሐይና ሐሩር፣ ብርድና ውርጭ የአየር ንብረት፣ ጠመዝማዛውና ወጣ ገባው ረጅም መንገድ ሳይገድብሽ በሳምንት ሁለት ጊዜ በአገልግል ስንቅ ተሸክመሽ ለአስተማርሽኝ እና አሁን በሕይወት ባለመኖርሽ የውለታሽን አንዷን የዝናብ ጠብታ ታህል ሳልከፈልኩሽ ለውድ እናቴ ለወ/ሮ ስንዴ አየለ ማስታወሻ ይሁንልኝ።

## ሙዳዬ ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ጐባን | = | ጣውንት |
| 2. | ሙገጐ | = | ምጣድ |
| 3. | እየሌ | = | አሞሌ ጨው |
| 4. | ግምል | = | አብሲት |
| 5. | አርጎዬ | = | ዘንጋዳ |
| 6. | ፎረ ፎር | = | የተራቆተ መሬት (ቦረቦር መሬት) |
| 7. | ውንጮ | = | የማሽላ አይነት |
| 8. | ክበብ | = | የቤተ ክርስቲያን ቅርጥ |
| 9. | ሽርፋ | = | የእህል ማከማቻ ጎተራ |
| 10. | መንዲስ | = | ትልቅ |
| 11. | አርባጫ | = | የምስጥ ኮይሳ |
| 12. | ምራን | = | እርሻ ሲታረስ ሞፈሩ ከቀንበሩ ጋር የሚታሰርበት ጠፍር |
| 13. | ቡንኝ | = | የጤፍ አይነት |
| 14. | ዳንግሌ | = | አውራ በግ |
| 15. | ቡክቡካ | = | ከእክማ እንጨት የሚወጣ ጥሩ ማዓዛ ያለው |
| 16. | ውድቂያ | = | በጫካ ሴት እና ወንድ ሲተኙ የሚከሰት ህመም |
| 17. | ውራንታ | = | ለእህል መስፈሪያ የሚያገለግል ስፌት |
| 18. | ማድጋ | = | የምርት መለኪያ ጆንያ |
| 19. | ቪላ | = | ሁለት ጣሳ የሚይዝ የእህል መስፈሪያ ዕቃ |
| 20. | ጥገት | = | የምትታለብ ላም |
| 21. | ሙጫ | = | ሕፃን |
| 22. | ወፍጠጪ | = | ስሩ ተቆፍሮ ለልብስ ማጠቢያ የሚያገለግል እፅዋት |
| 23. | ማውራ | = | የውሀ መቅጃ ሞላላ ቅል |
| 24. | መግላሊት | = | ከሸክላ የተሰራ የድስት መክደኛ |
| 25. | ሽንዳራ | = | ጠንጋራ |
| 26. | ካራ | = | ቢላዋ |
| 27. | አውራ | = | (ራ) ይጠብቃል የሳር አይነት |

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹በእብናት ወረዳ ከባህላዊ ወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና›› በሚል ርእስ የቀረበ ነው፡፡የእብናት ወረዳ ሴቶች በወፍጮ አውድ ላይ የሚያዜሟቸው እና የሚያንጐራጉሯቸው ቃል ግጥሞች ከዚህ ቀደም አልተጠኑም፡፡ ጥናቱ በገላጭ እና አውዳዊ ትንታኔ ስልት፤ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ የተጠና ነው፡፡የጥናቱ መረጃዎች በቀዳማይ እና ካልዓይ ምንጮች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በቀዳማይ ምንጮች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ሲሆን ካልዓይ ምንጮች ደግሞ ከመፃህፍት፣ ከጆርናሎች እና ከመመረቂያ ፅሁፎች የተወሰዱ ናቸው፡፡ ከቀዳማይ የተገኙት መረጃዎች እንደ ግለሰቦቹ ፍላጐት በመቅረፀ ድምፅ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ካሜራ እና በማስታወሻ ደብተር ተሰብስበዋል፡፡ጥናቱን ለመተንተን ገላጭ፣ ተንታኝ እና አውዳዊ የትንተና ስልቶችን እና የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን ለጥናቱ መመልከቻ ተጠቅሜአለሁ፡፡

ጥናቱ በእብናት ወረዳ ይመስረት እንጂ ሁሉንም የወረዳ ቀበሌዎች በገንዘብ እና በጊዜ እጥረት ምክንያት ማዳረስ አልተቻለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወፍጮ የሚፈጭባቸው ስፍራዎች ከከተማዋ የራቁ ቀበሌዎች ነበሩ፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ከ37 ቀበሌዎች መካከል በተመረጡ 9 ቀበሌዎች እና 32 ጐጦች ላይ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ የመረጃ ጊዜውም ከታህሳስ 26 እስከ የካቲት 10 ቀን 44 ቀናትን ወስዷል፡፡

በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡት ግጥሞች 612 ናቸው፡፡ እነዚህም የተሰበሰቡት ከ21 ቁልፍ መረጃ ቀባዮች፣ ከ31 አጋዥ መረጃ አቀባዮች እና ከ16 የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች በድምሩ 68 መረጃ አቀባዮችን በማሳተፍ ነው፡፡ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑባቸው የወፍጮ አውድ ላይ ከተሰበሰቡ እና ከተደራጁ በኋላ በያዙት ጉዳይ መሰረት ተከፋፍለው 55 ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡

ከጥናቱ እንደተገኘው የወረዳዋ ነዋሪ ሴቶች በወፍጮ ስራ ላይ የሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ምሬትን፣ ውዳሴን፣ ክፋትና ደግነትን፣ ፍቅርን እና ንቀትን ያሳያሉ፡፡ በቃል ግጥሞቹ ትንታኔ መሰረት የወረዳዋ ነዋሪ ሴቶች ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ አደረጃጀታቸው እና የህይወት ልምዳቸው ምን እንደሚመስል በጥናቱ ተገኝቷል፡፡

# 1. መግቢያ

ቃል ግጥም አንድ ማኅበረሰብ ብሶቱን፣ ስሜቱን፣ ደስታና ሀዘኑን የሚገልጽበት መሳሪያ ነው፡፡ (Fekade Azeze 1998,10-11)[1፡፡] ይህ ተግባር የሚፈጸመው በክዋኔ ነው፡፡ ቃል ግጥም በቃል እየተከወነ ከትውልድ ትውልድ ሲተላፍ ተለዋዋጭነት ይገጥመዋል፡፡ ስለሆነም ክዋኔና ተለዋዋጭነት የቃል ግጥም ዋነኛ ባህርያት ናቸው፡፡(Finnegan 1977,14፣ዘሪሁን አስፋው 1992÷2) ቃል ግጥም ለመከወን የመከወኛ አጋጣሚ እና የመከወኛ አውድ ያስፈልጉታል፡፡ (Okpewho 1992÷16) ይህ ጥናትም በእብናት ወረዳ በወፍጮ አውድ ላይ የሚከወኑትን ቃል ግጥሞች በመከወኛ አውዳቸው የወፍጮ አጋጣሚ ላይ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን የተጠና ነው፡፡

ጥናቱ በውስጡ አምስትም እራፎች አሉት፡፡እነሱም ምእራፍ አንድ መግቢያ የሚለውን የያዘ ሲሆን በስሩ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የመለሳቸው የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና የመተንተኛ ስልት፣ የጥናቱ ወሰን፣ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች እና የመስክ ተሞክሮ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ምእራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳንን የያዘ ሲሆን በስሩ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይገኙበታል፡፡ ምእራፍ ሦስት የጥናቱን አካባቢ (ዳራ) የያዘ ነው፡፡ ምእራፍ አራት ደግሞ ትንተና የተሰጠበት ሲሆን በስሩ ምሬትን፣ ውዳሴን፣ ፍቅርን፣ ንቀትን፣ ክፋትንና ደግነትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች የተተነተኑበት ነው፡፡ በጥናቱ አምስተኛ ምእራፍ ስር ደግሞ ማጠቃለያ እና ይሁንታ የያዘ ሲሆን፡፡ በመጨረሻም ዋቢ ጽሑፎች እና አባሪዎች ይገኙበታል፡፡

[1] የዓመተ ምህረት አገላለጽ የሀገር ውስጥ ጽሑፎች በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጣር የውጭ ሀገር ጽሑፎች ደግሞ እንደ ኤ.አ. ነው፡፡

## 1.1.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

እኔ ባደረግሁት ዳሰሳ መሠረት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እና በእብናት ወረዳ ከዚህ ቀደም በባህላዊ ወፍጮ ላይ የተጠና ጥናት ስለአላገኘሁ በአዲስ ርእሰ ጉዳይ ላይ ለማጥናት በማሰቤ ነው፡፡ ሁለተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ በዚሁ አካባቢ ተወልጄ ያደኩኝ ሲሆን በልጅነቴ እናቴና እህቶቼ ወፍጮ እየፈጩ ሲያንጐራጉሩ፣ ሲያዜሙ እሰማቸው ነበር፡፡ በዚሁ የወፍጮ ቃል ግጥም ደስታቸውን እና ሀዘናቸውን ሲገልጹ በተደጋጋሚ የመመልከት እድል ነበረኝ፡፡ በመሆኑም በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት በማድረግ የሴቶቹን ፍላጎትና ስሜት የማወቅና የማሳወቅ ፍላጐት ስላደረብኝ ነው፡፡
ሌላው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ የወፍጮ ቃል ግጥምን ብዙ ጊዜ ሴቶች ብቻቸውን ስለሚከውኑት ያለ ፍርሃትና ስጋት የውስጥ ስሜታቸውን ሊገልፁ ይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የሴቶቹን የህይወት ጉዞ እና አመለካከት ለማሳየት በማሰብ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት በውስጡ አቢይ እና ንዑስ አላማዎችን ያካተተ ነው፡፡

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና አላማ

በእብናት ወረዳ በባህላዊ ወፍጮ አውድ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ላይ ትንተና በማካሔድ የሴቶቹን ባህላዊ፣ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ሃይማኖታዊእና ስነልቦናዊ መልክ ማሳየት ነው፡፡

### 1.2.2. የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎች

- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞችን ከአውዳቸውና ከቴክስት አንጻር በመተንተን መልእክታቸውን መግለጽ፣
- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች መቼ፣ለማን እና ለምን እንደሚከወኑ በመለየት መተንተን፣
- በባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች ውስጥ ያሉ ትእምርት እና የመባያ ጉዳዮችን ዘርዝሮ በማውጣት መተንተን እና
- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞችን አንድምታ ከማህበረሰቡ ባህል እና እሴት አንጻር በመለየት መተንተን ናቸው፡፡

## 1.3.ጥናቱ የመለሳቸው የምርምር ጥያቄዎች

የዚህ ጽሑፍ ግኝት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች መልሷል ተብሎ ይገመታል።

- የሴቶቹ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እና የህይወት ጉዞ ምን ይመስላል?
- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች ምን መልእክት አላቸው?
- ቃል ግጥሞቹ መቼ? ለማን እና ለምን ይከወናሉ?
- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች ትእምርትና የመባያ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
- የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞች ምን ማህበራዊ እና ባህላዊ አንድምታ አላቸው?

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

ቃል ግጥሞቹ በሴቶች ይከወኑ እንጂ በዚህ ውስጥ የወንዶች አመለካከት ጭምር ይገለጣል። ስለዚህ የወንዶችና የሴቶች ማህበራዊ ደረጃ ምን እንደሚመስል ጥናቱ ሊጠቁም ይችላል። በስርዓተ ጾታ እና በመሳሰሉት የትምህርት መስኮች ላይ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኝዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ከጥናቱ በመነሳት የወረዳና የቀበሌ መንግስታዊ አካላት በሴቶች ላይ ለሚያወጧቸው ፖሊሲዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ጥናቱ ሴቶቹ በወፍጮ ላይ በሚያዜሟቸው፣በሚያንጐራጉሯቸው እና በሚያነበንቧቸው ቃላዊ ግጥሞች አማካይነት ስሜታቸው፣ ፍላጐታቸው፣ ብሶታቸው፣ ስኬታቸውና ምሬታቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል።

## 1.5.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እና የመተንተኛ ስልት

በፎክሎር ጥናት መረጃን በተፈጥሮ አውድ መሰብሰብ ፋይዳው ላቅ ያለ እንደሆነ (Goldstein 1964:76፣ፈቃደ፣1991፣22 እና Gray 2004:105) ያስረዳሉ።በመሆኑም የዚህን ጥናት መረጃዎች ከታኅሳስ 26/2005 ዓ.ም እስከ የካቲት 10/2005 ዓ.ም ድረስ ለ44 ቀናት ከመስክ በተፈጥሮ አውድ ሰብስቤአለሁ። የተገኙትን መረጃዎች የሰበሰብኩባቸውን ዘዴዎች እና መረጃዎችን የተነተንኩባቸውን ስልቶች ቀጥየ አቀርባለሁ።

### 1.5.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሜያለሁ።

#### 1.5.1.1.ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የፎክሎር አጥኚ የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብና ብሎም ለመተንተን ወደ መስክ ሲወጣ ወሳኝ የሆኑ የጥናት ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን መጠቀም ግድ ይለዋል። (Fetterman 1998:34) እኔም የጥናቱን መረጃ በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ ያስችለኝ ዘንድ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት የተባሉትን የፎክሎር መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ተጠቅሜአለሁ።

ምልከታ"Observation includes listening as well as looking"(Punch 2004:185) ምልከታ ሲባል ማስተዋልን፣ መረዳትን፣ ማዳመጥን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ባለመሳተፍ የሚደረግ ምልከታን ተግባራዊ አድርጌአለሁ። ይህን የተጠቀምኩበት ምክንያት ባህሉ ውስጥ ተወልጄ ያደግኩኝ ብሎም የቋንቋው ተናጋሪ ብሆንም እንኳ በሴቶች ወፍጮ ስራ ላይ ለመሳተፍ ባህሉ አይፈቅድልኝም።በባህሉ ወንድ ወፍጮ አይፈጭም።ስለዚህም ቃል ግጥሞቹን ይበልጥ ለመረዳት እችል ዘንድ ክፍት (open ended)፣ በከፊል የተወሰነ (semi-structured) እና የተገደበ (structured) የተባሉትን ሶስት የምልከታ ቴክኒኮች ተጠቅሜያለሁል።

ቃለመጠይቅ ከምልከታ በኋላ የሚከተል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በምልከታ ወቅት የነበረውን መረጃ የማስተዋልና የማዳመጥ ብዥታ እና ክፍተት ለመሙላት የሚወሰድ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በቃለ መጠይቅ ወቅት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የቃል ለቃል ግንኙነት ስለሚደረግ ተጨማሪ መረጃን የማግኘት እድል ይፈጥራል።(Goldstien 1964:103)

ቃለ መጠይቅ በሚድረግበት ወቅት አውድና አጋጣሚ የማይዘነጉ እና ችላ ሊባሉ የማይገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም የወፍጮ ቃል ግጥም ክዋኔ በሚካሄድበት አጋጣሚ ቦታ እና ጊዜ በመገኘት ቃለ መጠይቅ አካሂጃለሁ። በዚህም ምክንያት የተሻለ መረጃ በቅርብ ከማግኘቴ በተጨምሪ በእኔና በተጠኚዎቹ መካከል ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር አስችሎኛል። (Gomm 2008፡ 222)

የወፍጮ ቃል ግጥሞችን መረጃ ስሰበስብ ብዙዎቹ የማውቃቸው እና በቀላሉ የምረዳቸው ቢሆኑም አንዳንዶቹ ደግሞ ምርምርን የሚጠይቁ በመሆናቸው ምክንያት ቅኝታዊ ቃለ መጠይቅ እና ጥልቅ ቃለ መጠይቅ የተባሉትን የመጠይቅ ዓይነቶች ተጠቅሜአለሁ።

ቃለ መጠይቁን የአካሄድኩት ሁለቱን ቴክኒኮች በመጠቀም ነው። አንኳር አንኳር የተባሉ ጥያቄዎችን ብቻ በመምረጥ በከፊል ገደብ ያለው ቴክኒክ ተተቅሜያለሁ። ይህን ቴክኒክ የተጠቀምኩበት ምክንያ ለመረጃ ሰጭዎቹ እድል በመስጠት ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ስለአስቻለኝ ነው። ተከታዩ የተገደበ ቃለ መጠይቅ የተባለው ቴክኒክ ነው። ይህን የተጠቀምኩት ደግሞ ጊዜን ለመቆጠብና ዋናውን ጉዳይ ብቻ ለተጠያቂዎቹ በማቅረብ አጭር መልስ ለማግኘት ስለአስቻለኝ ነው። እነዚህን ሁለት የመጠየቂያ ቴክኒኮች በመጠቀም ከምልከታ ያመለጠውን ይሁን ግልጽ ያልሆነውን መረጃ በቦታው ተገኝቸ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ ጭምር በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተጠቅሜያለሁ።ይህን አካሄድ የመረጥኩት በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው ሰዎች ሳይቸገሩ የሚሰጡት መረጃ በመሆኑ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ፍላጐትና እውቀት ሊያስገኝ በመቻሉ ነው። ሁለተኛው ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በሚደረገው ቃለ መጠይቅ ጥሩ ግኑኝነትን ስለፈጠረልኝ ነው። (Fetterman 1998፡38)

መረጃ የሰበሰብኩት መሪ ቃለ መጠይቆችን በማዘጋጀት፣ መረጃ ሰጭዎችን በመመልመልና በመተዋወቅ ነው። ለቃለ መጠይቁ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ እንደ መቅረጸ ድምጽ፣ ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና የማስታወሻ ደብተር የመሳሰሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅሜያለሁ።

በዚህ ጥናት ውስጥ በ9 ቀበሌዎች እና በ32 ንዑስ ቀበሌዎች ላይ መረጃ የሰበሰብኩ ሲሆን 21 ቁልፍ መረጃ ሰጭዎችን እና 31 አጋዥ መረጃ አቀባዮችን በድምሩ 52 ሰዎችን በቃለ መጠይቅ መልክ በመረጃ አቀባይነት ተጠቀሜአለሁ።

የቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና የአጋዥ መረጃ አቀባዮች የተመለመሉበት የየራሳቸው መስፈርቶች አሏቸው። እነሱም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተመለመሉበት መስፈርት

በጾታ ሴቶች ብቻ ሲሆኑ በወፍጮ ስራ እና በስራው ላይ ቃል ግጥሞችን የማቀንቀን ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው፣የተጠየቁትን በአግባቡ በመመለስ ሙሉ መረጃ መስጠት የቻሉ እና ለቪዲዮ ካሜራ ፣ለፎቶ ካሜራ እና ለመቅረጸ ድምጽ ፈቃደኛ የሆኑ ናቸው፡፡

አጋዥ መረጃ አቀባዮች የተመለመሉበት መስፈርት ደግሞ ሴቶችን እና ወንዶችን የአካተተ ሲሆን ስለ እብናት ወረዳ እና ስለወፍጮ ቃል ግጥሞች ማብራሪያ መስጠት የቻሉ የመንግስት ሰራተኞች እና የአካባቢ ነዋሪ ወንዶች ናቸው፡፡ ሴቶቹ ደግሞ በወፍጮ ስራ እና በስራው ላይ ማቀንቀን የቻሉ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል ለካሜራ ወይም ለመቅረጸ ድምጽ ፈቃደኛ የሆኑ እና መረጃዎችን በከፊል መስጠት የቻሉ ናቸው፡፡

የቡድን ውይይት ይህ ሶስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን ከምልከታ እና ከቃለ መጠይቅ በኋላ የተካሄደ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ የጥናት ዘዴ ውስጥ ሶስት የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ሁለቱ ቡድን እያንዳንዳቸው አምስት፣ አምስት አባላትን የያዙ ሲሆን አንደኛው ቡድን ደግሞ ስድስት አባላትን የያዘ ነው፡፡በድምሩ 16 ሰዎች በቡድን ውይይት ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ 16 ተሳታፊዎች መካከል 3ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ የሴቶቹ ቁጥር የቀነሰበት ምክንያት እነሱ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ወቅት በብዛት የመሳተፍ እድል ስለነበራቸው ነው፡፡

የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የተመረጡበት መስፈርት በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው፣ስለ ማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ እና እሴት በቂ ግንዛቤ ያላቸው፣የቃል ግጥሞቹን የመባያ ጉዳዮችን እና የትእምርቶችን ትርጓሜና አንድምታ መስጠት የቻሉ፣ስለ አካባቢው የተሻለ እውቀት እና ችሎታ የአላቸውን የሀይማኖት አባቶችን፣የአገር ሽማግሌዎችን እና ሴቶችን በመምረጥ ነው፡፡የቡድን ውይይትን የተጠቀምኩበት ምክንያት ከወፍጮ ቃል ግጥሞቹ መካከል አንዳንዶቹ ቃላት አንድምታ እና ትርጓሜን የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹን ማህበራዊ አንድምታ፣ ትእምርት እና የመባያ ጉዳዮች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ብቻ ለመረዳት ይከብድ ስለነበር ችግሩን ለማቃለል ስል የቡድን ውይይት አካሂጃለሁ፡፡

ጥናቱ ከ12-82 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን በዋናነት አካቷል፡፡ተሳተፊዎቹን ለመጠየቅ ሁሉንም ማደራስና መሸፈን ስለማይቻል እንደ አስፈላጊነቱ የመረጣ ናሙና

(select sampling) ስልትን ተጠቅሚአለሁ፡፡ "Qualitative research involves sampling. This is because you can not study every one, every where doing every thing." (Punch 2004:105)

#### 1.5.1.2. ካልዓይ መረጃዎች

ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ይህ በቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተጻፉ መረጃዎች የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የምርምር መጻሕፍትን፣መጽሔቶችን፣የሁለተኛ እና የአንደኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፎችን ለጥናቱ እንደ መረጃ ምንጭ ወስጃቸዋለሁ፡፡

### 1.5.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት

በባህላዊ ወፍጮ የሚከወኑት ግጥሞች የሚስተላልፉትን መልእክት መግለጽ ይቻል ዘንድ የጥናቱ የመተንተኛ ስልት በዋናነት ገላጭ ነው፡፡

አውድ ራሱን የቻለ ዘመነኛ ንድፈ ሀሳብ ቢሆንም የጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና መተንተኛ ስልት ሆኖ የሚያገለግልበት አጋጣሚም ሰፊ ነው፡፡የፎክሎር ጥናት ክዋኔ ውስጥ ቴክስት እና አውድ የማይታለፉ የትኩረት ነጥቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከመረጃ መሰብሰቢያነት በተጨማሪ ለመተንተኛ ዘዴም አውድና ቴክስት ዋነኛ መሰረቶች ናቸው፡፡ (Dorson 1964:25፣ Bruce 1987፡29፣ Sims and Stephen 2005፡134፣)

ቡቴክስትና ኮንቴክስት መካከል ድንበር ማበጀት ስለሚከብድ ቃል ግጥሞቹን መረጃ ሰጭዎቹ ከሚከወኑበት አውድ ለመረዳት እና ለመተንተን እንድችል context and textual analysisን በመተንተኛ ስልት በተጨማሪ ተጠቅሜያለሁ፡፡ ‹‹The meaning of a text is its meaning in context. In terms of contextual analysis there is no dichotomy between text and context›› (Amos, 1992:210)

የመባያ ገዳዮች እና ትእምርት የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመረዳት እንዲቻል ፍካሬ (interpretation) የመተንተኛ ስልትን በአጋዥነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ጐንደር ዞን እብናት ወረዳ ካሉት 37 ቀበሌዎች መካከል በዘጠኙ ቀበሌዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት 37 ቀበሌዎችን ማካተትና መረጃ ለመሰብሰብ ካለው የጊዜ እና የገንዘብ እጥረት ምክንያት ለመሸፈን ስለሚያስቸግር ነው፡፡

እነዚህ ዘጠኝ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ቀበሌዎቹ ከከተማዋ ርቀት ቦታ ላይ የሚገኙ ሲሆን የዘመናዊ የእህል ወፍጮ አልፎ አልፎ ቢኖርም እንኳ ካለው የህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ ስለሆነም ወፍጮ የመፍጨት ስራ እና በዚሁ ስራ ላይ ቃል ግጥሞች የመከወናቸው አጋጣሚ አሁንም ድረስ አለ፡፡ ከሌሎቹ የወረዳዋ ቀበሌዎች መካከል በመቀጣዋ ንኡስ ወረዳ ስር የሚገኙት አጊሳ ፣ ደብር ተክለሃይማኖት፣ ግብጻዊት፣ ቁርቂራ፣ አዲያ፣ መናዲቅ፣ መና መ/ዓለም፣ አጃ ፋሲለደስ እና ዘቀልሞቃ የተባሉት ዘጠኝ ቀበሌዎች የወፍጮ ቃል ግጥሞችን ለማግኘት አመቺ በመሆናቸው ምክንያት ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡(አቶ አብቦ ሹመት፣አቶ አስቻለው ፈጠነ 04/05/2005/ ቃለ መጠይቅ)

እነዚህ ቀበሌዎች በስራቸው ደግሞ ዋጭኝ ማርያም፣ አሞዘና ማርያም፣ ግብርድባ ማርያም፣ሹም ወልዶ ማርያም፣ሳባ ጊዮርጊስ፣ ኩይና ጊዮርጊስ፣ ቀባይዚ አቦ፣ ታይበተስኪያን ኪዳነ ምህረት፣ ጣርሆ ማርያም፣ ግብጻዊት ማርያም፣ ብቢ ማርያም፣ ቁርቋራ ማርያም፣ ባርቃይባ ማርያም፣ ባሻየ አቦ፣ ባርቃይባ ጊዮርጊስ፣ ድርቋዝባ ሚካኤል፣ ዲንዳን ማርያም፣ ፎጠና አቦ፣ ግርማው ሚካኤል፣ ገብሩ አምባ መድኃኔአለም፣ ጋልጭሆ አቦ፣ ቀደብ ኢየሱስ፣ አባናዊ ኢየሱስ፣ አጃ ጊዮርጊስ፣ እነባር ማርያም፣ ፋሲለደስ፣ ዘቀልምቃ ሚካኤል፣ ምድር ቤት አቦ፣ ቤትኑራ ሚካኤል፣ መና መድኃኔአለም፣ ዲቅ ጊዮርጊስ፣ ገዴ ምድር ተክለሃይማት የተባሉ 32 ንዑስ ቀበሌዎች አሏቸው፡፡ እነዚህ ንዑስ ቀበሌዎች የባህላዊ ወፍጮ በብዛት የሚገኝባቸው በመሆኑ በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## 1.7. በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

የጥናቱን መረጃ በምሰበሰብበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ከእነዚህ መካከል በተለያዩ አጥኚዎች የሚጠቀሱ የገንዘብ፣ የመንገድ፣ የድካምና የውጣ ውረድ ታዋቂና ዘወትራዊ ችግሮች እንደ ጥናት ችግር አልወሰድኳቸውም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያቱ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት ቀድመው የሚታወቁ ችግሮች በመሆናቸው እኔ እንደሚከሰቱ ስለአወቅኩ መረጃ በምሰበስብበት አውድ ላይ የተከሰቱ አዳዲስ ችግሮችን እና ለችግሮቹ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ብቻ እገልጻለሁ፡፡

### 1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች

ሴቶቹ ወፍጮ የሚፈጩት ማለዳ በዶሮ ጩኸት በመሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተጠኚዎቹ ሴቶች በመሆናቸው ቃል ግጥሞቹን እንደልብ በሌሊት ተዛውሮ በየቤቱ እየገቡ ለመሰብሰብ ተቸግሬ ነበር፡፡

በመቅረጸ ድምጽና በቪዲዮ ካሜራ በምጠቀምበት ወቅት ድምጻችንን ያበላሽብናል በማለት እንዲሁም ሴት እንዴት እንደዚህ ያለ ገመና ትዘፍናለች ተብዬ በማህበረሰቡ እነወራለሁ በማለት፣ የፍቅር፣ የተቃውሞ፣ የንቀትና የጉባን ቃል ግጥሞችን እንደልብ ለማዜም ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሁሉንም ዓይነት ቃል ግጥም ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር፡፡

የአካባቢው ማህበረ ባህል ‹‹ሴት ልጅ ጭምት›› መሆን እንዳለባት ያስገድዳል፡፡ ስለሆነም እንደኔ ያለ እንግዳ እና ወንዶች በአካባቢው ሰብሰብ ካሉ የፍርሃት ስሜት ይታይባቸው ነበር፡፡ በተለይ ልጃገረዶች በእጅጉ በፍርሃት የሚዋጡበት አጋጣሚና ባለትዳሮችም መርጠን ካልዘፈንን ወይም የንቀት ዘፈን ከዘፈን ባሎቻችን ከሰሙን ማታ ይደበድቡናል በማለት በስጋት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆኑልኝም ነበር፡፡

ከነዚህ በተጨማሪ ወፍጮ የሚፈጨው ስራ ቀናትን ጠብቆ በመሆኑ በተፈለገው ቀን እና ሰዓት መረጃ ለመሰብሰብ አዳጋች ነበር፡፡ የወፍጮ ቃል ግጥምን ለማግኘት በየመንደሩ መዞርን የሚጠይቅ በመሆኑ የተፈለገውን መረጃ በታቀደው ጊዜ ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡

መብራት በቅርቡ ባለመኖሩ የቪዲዮ ካሜራ ባትሪ ለመሙላት መረጃ ከሚሰበሰብባቸው መንደሮች ወደ ቅርብ ከተማ መጓዝ ነበረብኝ። ከላይ እንደጠቀስኩት በአብዛኛው በዚህ አካባቢ ወፍጮ የሚፈጨው ሌሊት ዶሮ ሲጮህ በመሆኑ ቃል ግጥሞቹን በወፍጮው አውድ ላይ በቪዲዮ ካሜራ ለመቅረጽ ጨለማ በመሆኑ አስቸጋሪ ነበር።

## 1.7.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

በአካባቢው በሚገኙ ከጤና ኤክቴንሽን ሰራተኞች፣ ከአገር ሽማግሌዎች እና ከሃይማኖት አባቶች ጋር በጋራ ወፍጮ በሚከወንባቸው ቤቶች በመዘዋወር መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል። የአካባቢው ማህበረሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞቹ፣በአገር ሽማገሌዎቹና በሃይማኖት አባቶቹ ላይ ከፍ ያለ እምነት ስላለው የእነሱ ተቀባይነት አግዞኛል።

መቅረጸ ድምጽ እና ቪዲዮ ካሜራ ምንም አይነት የድምጽ መበላሸት እንደማያስከትልባቸው ታዋቂ ዘፋኞችን በመጥቀስ በማስረዳት እና በማሳመን ስጋታቸውን እንዲተዉ ጥረት አድርጌያለሁ።

ማህበረሰቡ ያወግዘናል መርጠን ነው የምንዘፍን ያሉትን ያለ እነሱ ፈቃድ ለማህበረሰቡ የዘፈኑትን የማላሰማና የማልናገር መሆኔን በማስረዳት ስጋታቸውን በማስወገድና በመተማመን መረጃ ሊሰጡኝ ችለዋል።ጭራሽ መቀረጽ አልፈልግም ያሉትን አይነአፋር ሴቶች ደግሞ ማስታወሻ ደብተር በመያዝ እንደዚሁም ከባሎቻቸው እና ከወላጆቻቸው ጋር ውይይት በማካሄድ እንዳይቆጧቸው በማድረግ ስጋታቸውን ለማቃለል ችዬ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ የገጠር አካባቢ ነዋሪዎች በመሆናቸው እና የአካባቢው ማህበረሰብ ከሚያሳድረው ተጽኖ አንጻር በአይን አፋር ስሜት ቃል ግጥሙ ላይ የመደነጋገር አጋጣሚዎች እንዳይፈጠሩ መቅረጸ ድምጹን በመክፈትና በወፍጮው አጠገብ በማስቀመጥ ሌሎች ሰዎቸና አጥኚው ጭምር ከአካባቢው ትንሽ ራቅ በማለት በነጻነት እንዲከውኑ አድርጌያለሁ።

በአካባቢው ክርስቲያኖች በበዓላት ቀናት በማይሰሩበት ወቅት የሙስሊሞቹን የወፍጮ ቃል ግጥሞች ከሸሆቹ ጋር በመቀናጀትና በመነጋገር መሰብሰብ ተችሏል። በመሆኑም የሚከሰተውን የጊዜ መባከን ለማስቀረት ተችሏል። ሌሊት በሚፈጩበት ወቅት መቅረጸ

ድምጽ እና ፎቶግራፍ በማንሳት መረጃውን የሰበሰብኩ ሲሆን ብርሃን በሚሆንበት ወቅት እና ጧት በሚፈጨበት አጋጣሚ ደግሞ ቪዲዮ ካሜራ በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

ለዚህ ጥናት መረጃ በምሰበሰብበት ወቅት የተለያዩ ሁኔታዎች ገጥመውኛል፡፡ እነሱም በታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተነስቼ ወደ ወረዳዋ ዋና ከተማ እብናት ገባሁ፡፡ ከዚህችው ከተማ ሆቴል ውስጥ ለአምስት ቀናት ተቀምጨ ወደ ተመረጡት ቀበሌዎች ለመሄድ ዝግጅት አደረግሁ፡፡ ከዚያም ከወረዳዋ አስተዳደር፣ የባህልና ቱሪዝም ጽ.ቤት፣ የመንግስት ኮምኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና ከህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰበሰብኩኝ፡፡ ከዚህ በመቀጠል የወረዳ አስተዳደሩ መኪና እስከሚገባበት ቦታ መኪና መደበልኝ፡፡ ከዚያም ከደመወዝ ከፋዮች፣ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሰራተኞች እና ከመምህራን ጋር በመገናኘት ወደ ቆላማው ክፍል ሄድን፡፡ ከቦታው እንደደረስን ከአካባቢው ማህበረሰብ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከጤና ባለሙያዎች እና ከመምህራን ጋር ትውውቅ አደረግሁ፡፡

ሥራ ከጀመርኩ በኋላ ይከሰታሉ ብዬ ያልጠበቅኳቸው ነገሮች ገጥመውኛል፡፡ እነሱም ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው እና የሌላቸው ተብለው በሁለት መልኩ ሲታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በርካታ ሰዎች እየመጡ ፎቶራፍ አንሳን፣ ሽዋ /ወባ/ ታመናል መርፌ ውጋን፣ ክኒን ስጠን ይሉኝ ነበር፡፡ በእብናት፣ በደብረ ታቦር፣ በባህርዳርና አዲስ አበባ ካሉ ዘመዶቻችን ጋር በስልክ አገናኘን የሚሉ ጥያቄዎች በስፋት ይቀርቡ ነበር፡፡ ከላይ ያነሳኋቸው ተሞክሮዎች ከእኔ ስራ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ችግሮች ናቸው፡፡ ከሥራዬ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ችግሮች ደግሞ ቀጥዬ አቀርባለሁ፡፡

በ09-05-2005 ዓ.ም ጭንጫ የሚባል ቦታ መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩ ጊዜ እየፈጩ ያገኘኋቸው ሴቶች ብዙ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ለመቅረጸ ድምጽም ሆነ ለቪዲዮ ካሜራ ፈቃደኛ የሆነች ሴት አላገኘሁም፡፡ በወቅቱ አንድ አብረውኝ የሄዱ አቶ ሞላ ዘገየ የተባሉ የ75 አመት እድሜ ባለ ፀጋ የሀገር ሽማግሌ ነበሩ፡፡ እናም ከሴቶቹ መካከል አንደኛዋ ነጠሩ አላዜ የተባሉ ትልቅ ሴትዮ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኝነታቸውን

የፈለገው ይምጣ በማለት ጮኸው ተናገሩ፡፡ ‹‹ታቦት እኮ ነው ይዘህብኝ የመጣህ›› በማለት የወሰድኳቸውን ሽማግሌ አክብረው መረጃ ሰጡኝ፡፡

በ16-05-2005 ዓ.ም ወ/ሮ ባንቻለም አየነው የተባለችው ሴት ወፍጮ መና መ/አለም ቀበሌ እየፈጨች አገኘኋት፡፡ ስትፈጭ እንደምትዘፍን ተነግሮኛል፤ ባሏም ፈቅዷል፡፡ በዚህ ጊዜ ቀድሞ አባቷ ሙተውባት ስለነበረ ከዘፈን ይልቅ ጉዳዩ ወደለቅሶ ተቀየረ፡፡ ውብነሽ ታከለ የተባለች ሴትም ባለቤቷ በሰው እጅ እናቷ ደግሞ ታመው ስለሞቱባት ምንም እንኳ የቆየ ክስተት ቢሆንም የወፍጮውን ዘፈን ወደለቅሶ ለውጦታል፡፡

በ29-05-2005 ዓ.ም በጧት ተነስተን ከኔጋር አቶ አረጋ አበራ እና አቶ መላሹ ታፈሰ የተባሉትን የአካባቢ ታጣቂዎች በመያዝ ‹‹እስላም ቤት›› ወደሚባል የሙስሊሞች መኖሪያ ሰፈር አቀናን፡፡ በዚህ ጐጥ አካባቢ ‹‹እህል አይበላ›› የሚባል ‹‹ውጅብ[2]›› አለ፡፡ ከዚህ ስፍራ በየዓመቱ የቅዱስ ዮሐንስ ፍየል እያረዱ የአምልኮ ስርዓት ይፈጽሙበታል፡፡ በመቀጠል የጥንት መፈራረጃ፣ መማማያ እና የውጅቡ እርድ ማረጃ ‹‹ጥኂራው ዋርካ›› ተብሎ የሚጠራ ትልቅ ዋርካ ከቤታቸው በላይ ይገኛል፡፡ መጀመሪያ ከዚህ ዋርካ ስር መቀመጥና አረፍ በማለት ውጅቡን ማክበር ደንብ ስለነበር ይህን አደረግን፡፡ ከዚህ ቦታ አሻገር ጥላሁን እና ሰኢድ ጌታው የተባሉ ሁለት ሙስሊሞች ተቀብለው ወደ ቤታቸው ወሰዱን፡፡

ከቤት ስንደርስ መጀመሪያ ቡና ተፈላ፡፡ ቀኑ ዕረቡ በመሆኑና ትንሽ ለማርፈድ ፈልጌ በአንደበቴ ፆም መሆኑን ሳልናገር ቡናው ይለፈኝ አልኩኝ፡፡ በዚህ ጊዜ አብሮኝ የሄደው አረጋ አበራ ቆንጠጥ አደረገኝ አይ መጀመሪያ ለአባባ ስጡ ብዬ ነው በማለት ነገሩን አሻሽዬ ቡናውን ተቀበልኩኝ፡፡ አይ መጀመሪያ በኛ እንግዳ ነው የሚቀበል እኛ ደግሞ ከሙስሊም ቤት አልጠጣም ልትል መስሎን ነበር አሉኝ፡፡ አንድ ቀን አብረውኝ የሚንቀሳቀሱትን አጋዥ ባልደረቦችን ሰብስቤ ስለምናደርገው ጉዳይ ማህበረሰቡ ሆነ ሴቶቹ ምን ይላሉ ብዬ ጠየቅኳቸው፡፡ ብዙዎቹ ሴቶች ‹‹ለመመረቂያ ጥናት ሳጠና ከአዲስ አበባ መጣሁ፡፡››

2. ውጅብ ማለት እንዳካባቢው ትርጓሜ በጫካ የተሸፈነ ሆኖ የሙስሊሞች መካነ መቃብር እና የአምልኮ መፈጸሚያ ቦታ ነው፡፡

ይለናል እንጂ መንግስት ችግራችን ተገንዝቦ መኪና ወፍጮ ሊተክልልን ነው። እንደዚሁም ለሴቶቹ ሊያዝንልን ነው እያሉ ይነጋገራሉ አሉኝ። /አቶ አረጋ አበራ፣ አቶ መላሸ ታፈሰ፣ አቶ ዋናው ደማም 2005 ቃለመጠይቅ/።

ሌላው በሁሉም ተጠኚዎች ትልቁ ገጠመኝ ለወፍጮው ዘፈን መረጃ በመስጠት በቀጥታ የምትጠየቅ የጉዳዩ ባለቤት የሆነችው ሴቷ አለመሆኗ ነው። ይልቁንም አብረውኝ ለመረጃው መሳካት የሚያግዙኝ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ሚሊሻዎች ይሁንታቸውን የሚጠይቁት ባለትዳር ከሆነች ለባልየው፣ ጥያቄው ከሁለት ሶስት ቀን ቀደም ብሎ ተደጋግሞ ይነገረዋል። በአንድ ጊዜ ፈቃደኛ አይሆንም። ተደጋግሞ ከተጠየቀ በኋላ እሺታውን ይናገራል።

እንደዚሁም የምትፈጨው ሴት አባት እና ወንድሞች እሺታቸውን ይጠየቃሉ። ለምሳሌ ውብነሽ ታከለ የተባለችውን ሴት ለመቅረጽ መጀመሪያ የተጠየቀው ታላቀ ወንድሟ ነጋሽ ታከለ ነው። የመጀመሪያው ቀን አይሆንም ብሎ በሁለተኛው ቀን ፈቃደኛ ሆኗል። ማሚት እሸቱን ለመቀረጽ ባልየው ስመኝ የኋላ የተጠየቀ ሲሆን ለእናንየ አበባው ደግሞ ባሏ የሆኑት ቄስ ደረጀ አያናው እና አማቷ አቶ አያናው አሰፋ በቅድሚያ ፈቃደኝነታቸውን ተጠይቀዋል።

በዚህ ጊዜ ሴቶች ሊዘፍኑ ለምን ወንዶች ይጠይቃሉ? እና ተደጋጋሚ ደጅ ጥናቱስ ለምን ያስፈልጋል? የሚሉ ሁለት ጥያቄዎችን አንስቼ ነበር። የተሰጠኝ መልስ ‹‹ምን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ ነው›› እንደዚሁም በእኛ አካባቢ አንድ ነገር ተጠይቆ ወዲያወኑ እሺ አይባልም ነገሩ መብሳላት (መጤን) አለበት አሉ። (አቶ ወንድማገኝ ሞላ፣ ቄስ ወርቁ ገላየ፣ ወ/ሮ አበባ ፍስሀ፣ቄስ ደረጀ አያናው፣ ቄስ ተሾመ ነጋሽ 19/05/2005 /የቡድን ውይይት)

ተወልጄ ያደኩበት አካባቢ ባይሆን ኖሮ ገጠመኞቹ ከዚህም ይበዙ ነበር የሚል ግምት አለኝ። ከዚህ የመስክ ተሞክሮ የተለያዩ ግንዛቤዎችን አግኝቻለሁ። እነሱም፡- አንድ አጥኚ ወደ መስክ ስራ በሚሄድበት ወቅት የአካባቢውን ማህበረሰብ አመጋገብ፣ አለባበስና አኗኗር ማክበር እንደሚገባው ተገንዝቤያለሁ።

አጥኚው በአካዳሚ የተረዳውን እውቀት ብቻ በመያዝ ወደ ስራው ዘው ብሎ መግባት የለበትም፡፡ በቅድሚያ የተጠኚዎቹን ማህበረሰቦች ሃይማኖት፣ ኢኮኖሚ፣ ባህላዊና ማህበራዊ አደረጃጀት ጊዜ ወስዶ መረዳት አለበት፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ጥናቱ መግባት ተገቢ እርምጃ መሆኑን በመስክ ቆይታዬ ተረድቻለሁ፡፡ እንዲሁም የእምነት ቦታዎችን ማክበር፣አመጋገባቸውን መቀበል፣ ስርዓታቸውን እና እሴቶቻቸውን መከተል፣ የመተዳደሪያደንብና ህጐቻቸውን ማወቅና ማክበር፣ በክርስቲያንም ሆነ በሙስሊሞቹ ክብረ በዓላት ራስን ማቅረብ መቻል፣የማህበረሰቡን የወንዶችና የሴቶች አደረጃጀት መከተል የሚያስፈልጉ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምእራፍ ስር ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ቅኝትና የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ይቀርባሉ፡፡

### 2.1.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በወፍጮ ቃል ግጥም ላይ በቢኤ፣ በኤምኤና በፒኤች ዲ ዲግሪ ደረጃ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን በሴቶች የስራ ዘፈኖቸ ላይ የተደረጉ የኤምኤና የቢኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች አሉ፡፡ እነዚህ ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸውን የተወሰነ ዝምድና የኤምኤ ጥናቶችን በማስቀደምና የቢኤ ጥናቶችን በማስከተል በቀረቡበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል መሰረት ቀጥዩ አቀርባለሁ፡፡

ብርሃኑ አሳየ ‹‹የባንጃና በአንክሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊኛ የሚያዜሟቸውን የሥራ ላይ ዘፈኖች ጭብጥ ገለጻና ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም፡፡ የኤምኤ ጥናት አቅርቧል፡፡

የጥናቱ ዓላማ በባንጃና በአንክሻ ወረዳዎች ሴቶች ስራ በሚሰሩበት አጋጣሚ የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች ጭብጥ መተንተን ነው፡፡ ብርሃኑ 200 ቃልግጥሞችን ሰብስቧል፡፡ አጥኚው መረጃውን የሰበሰበው በሐምሌ እና ነሐሴ ወራት 1999 እና እንደዚሁም በጥር ወር 1999 ወደ ቦታው በመሄድ በሚከወኑበት አጋጣሚ እና አውድ ነው፡፡

የሥራ ዘፈኖቹን የሰበሰበው በወቀጣ፣ በጭቃ ማሸት፣ በወፍጮ መፍጨት ሥራ፣ በሸክላ ዕቃዎች ስራ፣ በስፌት፣ በአውድማ ልቀለቃ፣ በአረቄ ማውጣት፣ በቆዳ ሥራ፣ በጉልጓሎና ኩትኳቶ፣ በምግብ ዝግጅት፣ በአጨዳና ጥጥ ፈተላ አጋጣሚዎች ነው፡፡

በእነዚህ አጋጣሚዎች የተሰበሰቡትን የስራ ላይ ዘፈኖች በሚያነሷቸው ጉዳዮች መሰረት ፍቅር 7፣ ፍቅርና ምርኮኛ 5፣ ሙገሳ 2፣ የግብረስጋ ግንኙነት 4፣ በፍቅር ሰበብ የተከሰቱ ጫናዎች 3፣ ጋብቻ 10፣ እማትና ምራት 4፣ መውለድና ማሳደግ 9፣ ጣውንትነት 8፣ ቤተሰባዊ ጉዳይ 3፣ ትምህርት 4፣ ፍቺ 6፣ ሥራ 7፣ ዘፈንና ዘፋኝነት 6፣ የመሬት ሽግሽግ 6፣ የመሬት ማዳበሪያ 4፣ ወታደራዊ ዘመቻ 4 እና ኤች

አይ ቪ ኤድስ 4 በማለት ለይቶ 96 ቃል ግጥሞችን ተንትኗል፡፡ ስራ በሚለው ክፍል ከ7 ቃል ግጥሞ መካከል 5 የወፍጮ ቃልግጥሞችን ለይቶ አሳይቷል፡፡ የዚህ አካባቢ ሰዎች በገንዘብ እጥረት እና በቦታ ርቀት ምክንያት በባህላዊ ወፍጮ እንደሚፈጩ በጥናቱ ጠቁሟል፡፡

አጥኚው በጥናቱ ግኝት የባንጃና ባንክሻ ወረዳዎች ነዋሪ ሴቶች በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች አማካይነት ያላቸውን ማህበራዊ ግኑኙነት፣ ፍላጎት፣ ጥላቻ ብሶትና ጫና ጥናቱ አሳውቋል፡፡

የብርሃኑን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ግጥሞቹን ከሰበሰበባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱ የወፍጮ ሥራ መሆኑ ነው፡፡ የሥራ ላይ ግጥሞቹ በሚከውኑበት አውድ በቀጥታ ከቃል ግጥሞቹ ባለቤቶች መሰብሰቡ እና በትንታኔው ክፍል ላይ ቃል ግጥሞቹ በሚያነሷቸው ጉዳዮች ተመርኩዞ ለመከፋፈል እና ለማዋገን መሞከሩ የእኔና የእሱ ጥናት እንዲመሳሰል አድርጎታል፡፡

የብርሃኑን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ልዩ የሚያደርገው ቃልግጥሞቹ በሴቶች ይከወኑ እንጂ የሴቶች የሥራ ዘፈኖች በሚል ከወፍጮ አጋጣሚ ይልቅ በሌሎች አሥራ ሁለት የሥራ ዘፈኖች ላይ በመመስረት ቃልግጥሞቹ በሚያነሱት ጭብጥ ተመርኩዞ ትንታኔ መስጠቱ ነው፡፡ ስለሆነም የብርሃኑ ጥናት በቃል ግጥሞቹ ጭብጥ መመስረቱ ከአውድ ይልቅ ለቴክስት ቅድሚያ የሰጠ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ድግሞ አውድና ቴክስትን አስተባብሮ የተጠና በመሆኑ ከብርሃኑ ጥናት ጋር በትንታኔ የትኩረት አቅጣጫ፣ በርእሰ ጉዳይ እና ጥናቱ በተካሄደበት ቦታ ከእኔ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል፡፡

ድርቤ ቀንዓ ‹‹በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ጭሮ ወረዳ አካባቢ የድኩና ሽብዶ ዘፈን ክዋኔ ግጥሞ ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም የኤምኤ ዲግሪዋ ማሟያ ጥናት አቅርባለች፡፡የድርቤ ጥናት ዓላማ የድኩና ሾብዶ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በመተንተን የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃ ማሳየት ነው፡፡ ድርቤ በአብዛኛው መረጃ የሰበሰበችው አርቲፊሻል መቼትን በመጠቀም ነው፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት የጠቀሰችው የሙቀጫ ወቀጣ ክዋኔ እየጠፋ በመሆኑ ወቀጣውንና የማሽላ ውቂያውን ክዋኔው በተፈጥሮ መቼት ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡

ድርቤ የድኮን፣የሽብዶንና የጉዛን ምንነት እና ባህርያት ከአብራራች በኋላ ስለ ውቂያ ክዋኔ የድኮ ዘፈን ግጥሞች ይዘት በሚለው ስር ንቀትን የሚያሳዩ 3፣ መለያየት የሚያሳዩ 7፣ የወንድና የሴትን ፍቅር የሚያሳዩ 4፣ የንብረት ጉዳይን የሚያሳዩ 3፣ ውዳሴን የሚያመለክቱ 6 በድምሩ 23 ቃልግጥሞችን ለይታ ትንታኔ ሰጥታለች፡፡

የሽብዶ ዘፈን ግጥሞች ይዘት በሚለው ክፍል ደግሞ ሙገሳን የሚመለከቱ፣ የልመና ግጥሞች እና ምክር አዘል ግጥሞች በማለት 10 ቃልግጥሞችን ተንትናለች፡፡ አጥኚዋ ከሰበሰበቻቸው 238 ቃልግጥሞች መካከል 33 ቃልግጥሞች ላይ ትንታኔ ሰጥታለች፡፡

ድርቤ በአባሪ መልክ በውቂያ ወቅት የሚዘፈኑ 29፣ የሙቀጫ ወቀጣ /ድኮ/ ግጥሞች 105፣ የወፍጮ ዘፈን /ድኮ/ ግጥሞች 25፣ የማሽላ ቆረጣ የሚዘፈኑ ግጥሞች 30፣ እና ማሽላ ሲወቃ የሚዘፈኑ የዘፈን /ሽብዶ/ ግጥሞች 49 በድምሩ 238 ቃል ግጥሞችን ሰብስባ በአባሪ መልክ አያይዛለች፡፡

ድርቤ በወፍጮ ላይ ተመስርታ ቃል ግጥሞቹን መሰብሰቧና መተንተኗ እንደዚሁም ይዘታዊ አከፋፈልና ትንታኔ መከተሏ የሷን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነጥብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቃልግጥሞቹ በማሽላ ውቂያና ቆረጣ በአርቲፊሻል መቼት መሰብሰቧ እና ከአውድ መውጣቷ ይህ ጥናት ከድርቤ ጥናት እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

‹‹የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና›› በሚል ርዕስ በ2004 ዓ.ም ቀለመወርቅ ተክሌ ባቀረበችው የኤምኤ ጥናት ዓላማ አድርጋ የተነሳችው በሀድያ ዞን የሚኖሩ ሴቶች የተለያዩ ሥራዎችን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዜሟቸውን ግጥሞች በአውዳቸው በመሰብሰብ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች መግለጽና መተንተን ነው፡፡

ቀለመወርቅ ተክሌ የሴቶችን የሥራ ላይ ዘፈኖች በአውድ በሚከወኑበት አጋጣሚዎች መረጃዎቹን ሰብስባለች፡፡ ቀለመወርቅ በእንሰት መፋቅ 12፣ በጓሮ አትክልት ኩትኳቶ 25፣ በስንደዶ ለቀማ 41፣ በወፍጮ መፍጨት 21፣ በወተት መናጥ 26፣ በእንጨት ለቀማ 5፣ በእረኝነት 19 እና በሙቀጫ መውቀጥ 7 በድምሩ 156 ቃልግጥሞችን ሰብስባለች፡፡ ከእነዚህ መካከል 47 ቃልግጥሞችን ተንትናለች፡፡

የዚህ ጥናት ግኝት የሀድያ ሴቶች ስለውበት፣ ማንነት፣ ጀግንነት፣ የዘር ሀረግ ያላቸውን አስተሳሰብ አሳይቷል። ከዚህ በተጨማሪ የሀድያ ሴቶች ስለ ስራ መተባበር እና ስለ ስራ ብርታት ያለቸውን ስሜት በአውራሪስ፣ በአንበሳና ነብር አስመስለው እንደሚያቀርቡ በጥናቱ ተገልጾአል።

ቀለመወርቅ ከሴቶች ሥራ መካከል በወፍጮ አውድ ላይ የተዘፈኑ ቃል ግጥሞች ላይ መመርኮዟ እና መተንተኗ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የጥናቱ ልዩነት ደግሞ ጥናቱ የሚጠናበት ቦታ፣ ርእሰ ጉዳይ እና ቃልግጥሞቹን በተለያዩ የሴቶች የሥራ አጋጣሚዎች ላይ መሰብሰቧ ነው። በተጨማሪ ግጥሞቹ በሚያነሱት ጉዳይ ከመተንተን ይልቅ በተሰበሰቡበት አጋጣሚ ላይ ተመስርታ ለመከፋፈል፣ ለማደራጀት እና ለመተንተን መሞከሯ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል።

ከዚህ ቀጥየ ደግሞ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡትን ጽሑፎች እቃኛለሁ።ሮማን ገብረ አምላክ ‹‹የአድዋ አውራጃ የስራ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1982 ዓ.ም ዲማጽ አቅርባለች። የጥናቱ ዓላማ በአድዋ አውራጃ ሴቶችና ወንዶች በስራ ላይ የሚያዜሟቸውን ቃልግጥሞች መሰብሰብና መተንተን ነው። ሮማን የእርሻ የተለያዩ ስራዎችና፣አዲስ ቤት በሚሰራበት ጊዜ የሚዜሙ ጠቅላላ 274 ቃልግጥሞችን ሰብስባለች። ከእነዚህ ውስጥ 12 ሴቶች በወፍጮ ላይ የሚያዜሟቸውን ቃልግጥሞች፣ ወንዶች ደግሞ በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያና በአረም የሚያዜሟቸውን 70፣ በድምሩ 82 ቃል ግጥሞችን ተንትናለች።የሮማን ጥናት ከመስክ የተሰበሰቡትን ቃል ግጥሞች ከመሰነድ እና ከመቀረስ ባለፈ ይህ ነው የሚባል የዓላማ የመረጃና የትንተና ክፍል የለውም።

የሮማን ዲማጽ ከእኔ ጥናት ጋር የሴቶች የወፍጮ ቃልግጥሞችን ሰብስባ ለመተንተን ያደረገችው ሙከራ ያመሳስለዋል። ነገር ግን ጥናቱ በአብዛኛው በወንዶች የስራ ዘፈኖች ላይ ማለትም ወንዶች ሲያርሱ፣ ሲያርሙ እና ሲያጭዱ የሚያዜሟቸውን የስራ ግጥሞች ላይ መመስረቷና ትኩረት መስጠቷ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል።

ያዜ ወርቁ ‹‹የደንቢያ አውራጃ የስራ ላይ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ›› በሚል ርዕስ በ1984 ዓ.ም ባቀረበው ዲማጽ በደንቢያ አውራጃ ሴቶችና ወንዶች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ የሚያዜሟቸውን 708 ቃል ግጥሞችን በቦታው በመሄድና የሚያውቁ

ሰዎችን በመጠየቅ ሰብስቧል፡፡ ጥናቱ የማህበረሰቡን ብሶት የሚገልጹ 12፣ በሬና ወንድም የሌለውን የሚያወሱ 10፣ ስራን የሚመለከቱ 9፣ ፍቅርን የሚገልጹ 14፣ ቅናትን የሚገልጹ 8፣ በድምሩ 53 ቃል ግጥሞችን ተንትኗል፡፡

አጥኚው ብሶትን የሚገልጹ በሚለው የትንተና ክፍል 3 የወፍጮ ቃልግጥሞችን እና በስራ ጉበዝ መሆንን የሚያሳዩ በሚለው ክፍል ደግሞ 2 በድምሩ 5 የወፍጮ ቃልግጥሞችን ተንትኗል፡፡ ይህ ጥናት የስራ ቃልግጥሞችን ከመሰብሰብና ከመሰነድ ያለፈ የተጠቀሰ የዓላማና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የለውም፡፡

ያዜ ሴቶች በስራ ላይ የሚያቀነቅኗቸውን ቃል ግጥሞች መሰብሰቡ እና በመረጃ የተገኙትን ቃል ግጥሞች በይዘት ለመከፋፈል እና ለመተንተን መሞከሩ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ያዜ የሴቶችን እና የወንዶችን ቃል ግጥሞች በአንድ ጉራ ለማጥናት መሞከሩ፣ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ፣ ርእሰ ጉዳይ እና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴው በአውድ ተመስርቶ ተጠኝዎችን ማሳተፍ አለመቻሉ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል፡፡

ህዝብ አዳም ገላ ‹‹የደጀን ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ይዘታዊ ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1986 ዓ.ም ዲማጽ አቅርቧል፡፡ አጥኚው የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ፣ በሚዘፍኑበት ቦታ በመገኘትና ሌሎች ሰዎች ግጥሞችን ጽፈው እንዲያመጡለት በማድረግ መረጃውን ሰብስቧል፡፡ ህዝብ አዳም በዋናነትም ሴቶች የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች ሰብስቧል፡፡ እነሱም በወፍጮ ስራ ላይ 37፣ በአረም የሚዘፈኑ 40፣ በጉልጓሎ የሚዘፈኑ 14፣ በስፌት የሚዘፈኑ 101፣ በሰብል ጥበቃ 45፣ በጉዞ ላይ የሚዘፈኑ 13፣ በእንጨት ለቀማ 36 በድምሩ 368 ቃል ግጥሞችን ሰብስቧል፡፡ በትንተናውም ቃልግጥሞቹ ፍቅርን፣ ስንፍናን፣ ጀግንነትን፣ ጥላቻንና ሀሜትን እንዲሁም እናትን እንደሚያነሱ በማሳየት 54 ቃል ግጥሞችን በይዘት ከፋፍሎ ተንትኗል፡፡ ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ የመረጃ አሰባሰብ እና ትንተና አንጻር ሲታይ ጥሩ የሚባል ነው፡፡

ይህ ዲማጽ ሴቶች በስራ ላይ የሚዘፍኗቸው ቃል ግጥሞች ላይ በመመርኮዝ ግጥሞቹን በይዘት ለመተንተን ያደረገው ሂደት ከኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ህዝብ አዳም ብዛት ባለው የሴቶች የስራ ዘፈን አጋጣሚዎች ላይ በመመስረቱና የቃል

ግጥሞቹን በአውድና በአጋጣሚ ላይ አለመሰብሰቡ፣ ብሉም ትንታኔ አለማካሄዱ እና የጥናቱ ቦታ የተለያየ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ሰፊ ልዩነት እንዲኖረው አድርጎታል።

‹‹የደሴ ዙሪያ ሴቶች የሥራ ላይ ግጥም›› በሚል ርዕስ በ1992 ዓ.ም ዘሀራ ሰይድ ያቀረበችው ዲግሪ ዓላማ በቃል ግጥሙ የሴቶችን አኗኗር እና አስተሳሰብ ማሳየት እና ስነቃል የመጥፋትና የመለወጥ ባህሪ ስላለው በመነገር ላይ ያለውን ስነቃል ለመጭው ትውልድ መዝግቦ ለማቆየት የሚል ነው።

አጥኚዋ ቃለ መጠይቅ በማድረግና የሚያውቁ ሰዎችን ቃል ግጥሞቹን ጽፈው እንዲሰጧት በማድረግ መረጃ ሰብስባለች። ዘሀራ ከስራው ጋር ግኑኝነት ያላቸው 26፣ ግኑኝነት የሌላቸው 59፣ ፍቅርን የሚገልጹ 67፣ ጥላቻን የሚገልጹ 33፣ ሀገርን የሚያነሱ 17 በድምሩ 202 ቃልግጥሞችን ሰብስባለች። ከእነዚህ መካከል ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው 76 (9 የወፍጮ) ቃል ግጥሞችን እና ግንኙነት የሌላቸው 48 በማለት ከፍላ በድምሩ 124 ቃልግጥሞችን ተንትናለች። የዘሀራ ጥናት ከዓላማ፣ ከመረጃ አሰባበሰብና አተናተን አኳያ ሲታይ ጥምረት ያለው ነው። በጥናቱ ላይ ተመርኩዞ የደሴ ዙሪያ ሴቶችን አስተሳሰብ እና አመለካከት ያሳየ ጥናት ነው።

ዘሀራ ከሴቶች የሥራ ዘፈኖች መካከል አንዱ በሆነው በወፍጮ አውድ ላይ መመስረቷ እንዲሁም ቃል ግጥሞቹን በይዘት መከፋፈሏና መተንተኗ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነጥብ ነው። በአንፃሩ ጥናቱ የተካሔደበት አካባቢ፣ መረጃ የመሰበሰቢያ አጋጣሚዎች መብዛታቸውና መለያየታቸው ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር የሚለዩት ነጥቦች ናቸው።

አመነ ወርቁ ‹‹በቸኻ አካባቢ የሴቶች የሥራ ላይ ግጥም ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1993 ዓ.ም ዲግሪ አቅርቧል።የጥናቱ ዓላማ ሴቶች በሚሰሩበት ወቅት ምን ይላሉ፣የአካባቢው ማህበረሰብ አኗኗር ምን ይመስላል እና የሥራ ግጥሞቹን ወደ ጽሑፍ ለውጦ ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፍ የሚሉ ናቸው።

አመነ ወርቁ መረጃ የሰበሰበው ሴቶች ሲዘፍኗቸው የነበሩትን እና የሚያስታውሷቸውን በራሱ በመመዝገብ፣ በተለያዩ የእድሜ ክልል ያሉ አስራ ሁለት ሰዎችን በመረጃ አቀባይነት በመጠቀም እና በአካባቢ ያሉ ተማሪዎችን ሰብስበው እንዲያመጡለት

በማድረግ ነው። ቃል ግጥሞቹን በአምስት ክፍል በመመደብ ጉሳን የሚገልጹ፣ እናትን፣ ጋብቻና የትዳር ህይወትን የሚገልጽ፣ በጉ ስራን እና ባህላዊ እምነቶችን የሚገልጹ በማለት አስራ አምስት ቃል ግጥሞችን ተንትኗል።

የአመነ ዲማጽ በሴቶች የሚከወኑ ቃልግጥሞችን መሰብሰቡና መተንተኑ እንደዚሁም ቃል ግጥሞችን በይዘት ለመክፈል እና ለመተንትን ያደረገው ሙከራ ከእኔ ጥናት ጋር በመጠኑ ያመሳስለዋል። በሌላ መልኩ በሰፊው ጐልቶ የሚታየው ልዩነቱ ነው። አመነ በአውድ ተመርኩዞ መረጃዎችን አለመሰብሰቡ፣ አላማው ቃልግጥሞቹን ለመቅረስ መሆኑ እና የአተናተን ስልቱ አውድን ብሎም ቴክስትን አለመከተሉ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል።

አቢይ ጌታሁን ‹‹በመስቃን ብሔረሰብ የሴቶች ማህበር /ዳዶ/ ክዋኔ እና በክዋኔው ወቅት የሚቀርቡ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1993 ዓ.ም ያቀረበው ዲማጽ አላማ በመስቃን ብሔረሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች በማህበር ስነስርዓት ላይ የሚቀርቡ ቃልግጥሞች መሰብሰብና ማጥናት ነው። አቢይ መረጃውን የሰበሰበው በክዋኔው በመገኘት በመቅረጸ ድምጽ በመቅረጽ እና ወደ ጽሑፍ በመቀየር በተጨማሪም የዕድሜ ባለጸጐችን በመጠየቅ ነው።

በጥናቱ ያተኰረው የዳዶን ምንነትና ታሪካዊ አመጣጥ በማብራራት ነው። የምረቃ ቃል ግጥም በሚለው ክፍል ውስጥ በምግብ ሥነ ሥርዓት፣ በቡና ሥነ ሥርዓት እና በጫት ሥነ ሥርዓት፣ ብሎ ስድስት ቃል ግጥሞችን ተንትኗል። እንደዚሁም በክዋኔ ወቅት የሚቀርቡ ቃልግጥሞች ይዘት ትንተና በሚለው ክፍል ደግሞ ትምህርት ሰጭ ግጥሞች 6፣ የሙገሳ ግጥሞች 6፣ እና የልመና ግጥሞች 7፣ በድምሩ 19 ቃል ግጥሞችን ተንትኗል። ከዚህ በተጨማሪ ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑት በመስቃንኛ እና በስልጢኛ ቋንቋ ሲሆኑ እነዚህን ግጥሞች ወደ አማርኛ ተርጉሞ አቅርቧል።

አቢይ በሴቶች የሚከወኑ ቃል ግጥሞችን በአውድ ተመስርቶ መረጃ መሰብሰቡ እና ለመተንተን መሞከሩ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነጥብ ነው። የአቢይ ጥናት አላማ የዳዶን ታሪካዊ አመጣጥ እና ምንነት ለማሳውቅ የተነሳ ነው።ይህ ደግሞ ተጠኝዎቹን የዘነጋ እና ወደ ታሪክ ያደላ በመሆኑ በትኩረት አቅጣጫ ይለያል። እንደዚሁም በርእሰ ጉዳይ እና በጥናቱ ቦታ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል።

ደመቀ ቢያዝን ‹‹የሙቀጫ ግጥም በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ›› በሚል ርዕስ በ1997 ዓ.ም ያቀረበው ጥናት ዓላማ የሙቀጫ ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና በማድረግ ቃል ግጥሞቹን መዝግቦ ማስቀመጥና የሙቀጫ ግጥሞችን አቀራረብ ሂደት ማመልከት ነው፡፡ ደመቀ ከማህበረሰብ ጋር በአካል በመገኘትና ተማሪዎችን በመጠቀም 42 ቃል ግጥሞችን ሰብስቧል፡፡

አጥኚው ብሶትን የሚገልጹ 5፣ ጣውንትን የሚገልጹ 3፣ ሀሜትን የሚመለከቱ 2፣ እና ቅናትን የሚመለከቱ 5 በድምሩ 25 ቃል ግጥሞችን ተንትኗል፡፡ ደመቀ በጥናቱ ውስጥ የሙቀጫ ቃል ግጥሞችን የሚመለከቱ 5 ብቻ ሰብስቦ እነሱንም አልተነተናቸውም፡፡ ስለሆነም በርዕሰ ጉዳዩ፣በአላማው እና በትንተናው መካከል ግንኙነት ባለመኖሩ ይህ ነው የሚባል ውጤት ያለው ጥናት ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

የደመቀ ጥናት በሙቀጫ አጋጣሚ የሚከወነው የሴቶች ቃል ግጥም በወፍጮ አጋጣሚ ሊባል የሚችል መሆኑ እና ቃል ግጥሞቹን በይዘት ለመተንተን የተጠቀመባቸው የመተንተኛ ስልቶች ሲነሱ ከዚህ ጥናት ጋር በመጠኑ እንዲመሳሰል ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ የጥናቱ ቦታ፣የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ፣ መረጃ በአውድ ላይ ተመስርቶ አለመሰብሰቡ እና ቃል ግጥሞችን ለመቀረስ በመነሳቱ ምክንያት ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩ ያደርገዋል፡፡

የኔአለም አረደ‹‹ የጥዮ አካባቢ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች የይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ 1997 ዓ.ም ያቀረበችው ጥናት ዓላማ የስራ ላይ ግጥሞችን በይዘታቸው መፈረጅና መተንተን ነው፡፡ እንደዚሁም የግጥሞቹን ይዘት ተንትኖ ማሳየት እና ግጥሞቹ የሚጠቁሙትን የሴቶች ማህበራዊ ሚና ማመልከት ነው፡፡ አጥኟዋ የስራ ግጥሞቹ በሚከወኑባቸው ቦታዎች በመገኘት ተማሪዎችን በማሳተፍ እና መቅረፀ ድምፅ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ የኔዓለም ከስራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ግጥሞች በሚል በስፌት 4፣ በላም ማለብ 9፣ ውሃ በመቅዳት 3፣ በወቀጣ 2፣ በወፍጮ 5፣ በልጆች ማባበል 28 ቃል ግጥሞችን ከመስክ ሰብስባለች፡፡

ከስራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው በሚለው ክፍል ስለ እናት 5፣ መለየትን የሚገልፁ 20፣ ጋብቻና የትዳር ህይወትን የሚገልፁ 8፣ ሀሜትን የሚያወግዙ 4፣ ስንፍናን የሚያወግዙ 4፣ ፍቅርን የሚገልፁ 42፣ ለጣውንት የተገጠሙ 9 በድምሩ 143

ቃል ግጥሞችን ሰብስባለች። ከእነዚህም መካከል 35 ቃል ግጥሞችን መርጣ ትንተና የሰጠች ሲሆን በወፍጮ አጋጣሚ ከሰበሰበቻቸው 5 ቃል ግጥሞች መካከል 2ቱን ቃል ግጥሞ ተንትናለች። የየኔአለም ጥናት ግኝት የጥዮ አካባቢ ሴቶች በስራ ላይ በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች አማካኝነት የህይወት ጉዞአቸው አድካሚ እና አሰልቺ መሆኑን አሳይቷል።

የኔአለም የሴቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀት ለማሳየት መሞከሯ፣መረጃ በተፈጥሮ መቼት መሰብሰቧ እና ቃል ግጥሞቹ በሚያነሱት ይዘት ተመስርታ መተንተኗ ከኔ ጥናት ጋር እንዲመሳሰል አድረጎታል። በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች ላይ መረጃዎችን መሰብሰቧ እና ቃል ግጥሞቹን በቴክስት እንጅ በአውድ አለመተንተኗ ደግሞ የእኔን እና የእሷን ጥናት ያለያየዋል።

ከዚህ በላይ የተዳሰሱት ጥናቶች በሴቶች ስራ ላይ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በእነዚህ የክዋኔ አጋጣሚዎች መካከል አንዳንዶቹ የወፍጮ ቃል ግጥሞችን ተመልክተዋል።አብዛኞቹ አጥኚዎች የሰበሰቧቸውን መረጃዎች የተነተኑት የቃል ግጥሞቹን ይዘት ነው። በዚህም ጥናቶቹ ከኔ ጥናት ጋር በተወሰነ ደረጃ ይመሳሰላሉ።

የጥናቶቹ ልዩነት ደግሞ በተለይ የቢኤ ጥናቶች የመረጃ አሰባሰባቸው በአውድ የተወሰነ አይደለም። ይልቁንም ሲባሉ ከሰሟቸው፣ ከራሳቸው ልምድ፣ ተማሪዎችን እና መምህራንን በመጠቀም በወፍ በረር የተሰበሰቡ መረጃዎችን ነው ያመጡት። የአብዛኞቹ የጥናት አላማና አነሳሽ ምክንያት ደግሞ ቃል ግጥሞቹን ለመቀረስ ማሰብ ነው። የትንታኔ አሰጣጣቸውም ቢሆን ብዙዎቹ በይዘት ይመርኮዙ እንጂ የቃልግጥሞቹን ትርጉም፣ መባያ ጉዳዮች፣ አንድምታዎች እና ፍካሬያዊ ፍቺዎች ተመርኩዘው አልተነተኗቸውም። ይልቁንም ግጥሙን በመስማት ብቻ ሊታወቁ የሚችሉ እማሬያዊ ፍቺ ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። ይህ አካሄድ በኤምኤ የመመረቂያ ጽሑፎች ላይም ቢሆን የሚስተዋል ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ከዚህ በተጨማሪ በኤምኤ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ደግሞ በይዘት ከመመርኮዝና ከመተንተን ይልቅ ግጥሞቹ የተሰበሰቡበትን አጋጣሚ መክፈያ መንገድ በማድረግ ትንታኔ ሰጥተዋል (ቀለመወርቅ ተክሌ 2004)።

የእኔ ጥናት አካሄድ ደግሞ በወፍጮ አውድ የተሰሙ ቃልግጥሞች ላይ ብቻ በመመስረት የሴቶችን አስተሳሰብ እና ስሜት በቃልግጥሞቹ አውጥቶ ማሳየት ነው። በዚህም የቃል ግጥሞቹ ፍካሬያዊ ፍቺ እና አንድምታ ተተንትኗል። በመሆኑም የተዳሰሱት ጥናቶች ከጥናቱ ቦታ፣ ትኩረት እና ዓላማ ከዚህ ጥናት ጋር ሲነፃፀሩ መጠነኛ ተመሳስሎ ይኑራቸው እንጂ በዋናነት ልዩነታቸው ያመዝናል።

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.2.1.የቃል ግጥም ምንነት

ቃል ግጥም የአንድ ማህበረሰብ ይሁን አንድ ቡድን የውስጥ ስሜቱን፣ ብሶቱን ደስታና ሀዘኑን የሚገልጽበት የስነቃል ዓይነት ነው። ቃል ግጥም የአንድ ማህበረሰብን አስተሳሰብ አመለካከት እና የህይወት ጉዞ ለማወቅ ያስችላል። ሰዎች የሚደገፉትን ይሁንታ የሚቸሩበት እና የሚቃወሙትን ደግሞ የሚተቹበት መሳሪያ ነው። ቃል ግጥም ማህበረሰቡ የመቃወማቸው ይሁን የመደገፋቸው ሚና ሳይታወቅ በሰላም የሚያመልጡበት ጥበብ ነው። (Philip Peak and kwsiyankha 1967:423 Okpewho 1992:78 Fekade 1998 10 -11 ፈቃደ 1994፣335)

### 2.2.2. የቃል ግጥም ተስተላልፎ

ቃልግጥም በሮማንቲክ፣ በማስታወስ (memorization) እና በመደረስ (composition) መንገድ ከቦታ ቦታ እና ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል። (Finnegan 1977: 135 - 152) የሮማንቲክ አመለካከት አቀንቃኞች ቃል ግጥም ከዘመን ዘመን የሚሸጋገረው ና የሚተላለፈው ቀድሞ መነሻ ስለ አለው ነው ብለው ያምናሉ። ከአንድ ቦታና ጊዜ ተነስቶ ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ይሰራጫል የሚል አቋም አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ የሮማንቲክ አስተሳሰብ ደጋፊዎች ባልተጻፈውና በተጻፈው ቃል ግጥም መካከል ድንበር ለመተከል ይሞክራሉ። የሮማንቲክ የቃል ግጥም ተስተላልፎና አፈጣጠሩ አንድ መነሻ ያለው ነው። ስለሆነም ከአንድ ቦታ ወይም ምንጭ ተነስቶ እንደ ጅረት ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚፈስ ነው የሚሉ አስተሳሰቦች ይነሳሉ።ይህ አካሄድ የማህበረ ባህሉን አስተሳሰብ የሚገዳደር መሆኑን በመጥቀስ ቃል ግጥምን በአንድ የቦታና የዘመን ማዕቀፍ ውስጥ አስሮና ቀይዶ ማስቀመጥ ተገቢነት የለውም የሚል መከራከሪያ ይነሳል። (Finnegan 1977:139-140)

ሁለተኛው የቃልግጥም መተላለፊያ መንገድ ማስታወስ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ማንኛውም ድሮ የነበረ ቃልግጥም ከአባት ወደ ልጅ፣ ከቦታ ቦታ እና ከዘመን ዘመን በማስታወስ እየተነገረ የሚተላለፍ እንደሆነ የሚያምን ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በማስታወስ ንድፈ ሀሳብ ላይ የመሰከሩ ሰዎች የድሮውን (የነበረው) የሚያጸኑ፣ ከዋኜው በሚፈጥረው አውድ የሚመሰረቱ እና ሁለቱን የሚያነጻጽሩ በሚሉ በሶስት ጎራ ተከፍለው የሚያከራክሩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ የተስተላልፎ አስተሳሰብ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ፡፡የጥያቄዎቹ መሰረትም አንድ ሰው የሰማውን በሙሉ ለመድገምም ይሁን ለማስታወስ ተፈጥሯዊ ባህሪው ስለሚገድበው እና ቃል ግጥሞቹ የማስታወስ ችሎታም ከሰው ሰው ይለያያል የሚሉ ናቸው፡፡ (Finnegan 1977:143)

የቃል ግጥም ተስተላልፎ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ እና ከትውልድ ትውልድ በሚያደርገው ፍሰት እየተረሳና ከወቅቱ ጋር በተረሳው እየተተካ የሚሔድ መሆኑ መታወቅ እንዳለበት በአጽንኦት ያስረዳሉ፡፡

ስለሆነም ይህን የማስታወስ ድክመት ይሁን ክፍተት ለመሙላት ቀጣዩና ሶስተኛው የተስተላልፎ መንገድ ድረሳ ነው፡፡ ድረሳ ተስተላልፎ ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ በቃል የሚተላለፍ በመሆኑ የመረሳት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ክፍተት ለመሙላት ዋነኛው መንገድ ድረሳ ነው የሚል አሰተሳሰብ አለው፡፡ ድረሳ በከዋኙ፣ በክዋኔ በአውድ እና አጋጣሚ ተጽዕኖ ስር የሚወድቅበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ቃልግጥም በባህሪው ለክዋኔና ለአውድ ተገዥ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ድረሳ ለቃልግጥም ለተስተላለፎ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ የድረሳ ቃልግጥም ተስተላልፎ የሰው ልጅ አእምሮ ውስን በመሆኑና በተለያዩ ወቅታዊ አጋጣሚዎች ሙሉ በሙሉ የቆየውን ቃል ግጥም እንዳለ ማስታወስ ስለሚቸግር አዲስ በመፍጠር የመረሳቱን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡የቃል ግጥም ድረሳ በተገቢው መንገድ ከአውድ፣ ከአካባቢውና ከዘመኑ ሁኔታ ጋር በማስማማት ካልተፈጠረ በነባሩ ቃል ግጥም ጭብጥ፣ አዝማች እና ሐረግ ላይ ለውጥ ስለሚያመጣ የመጀመሪያው የቃልግጥም ቅርጽ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ (Finnegan 1977:142-145)

ከላይ የተጠቀሱ ሶስት የቃል ግጥም ተስተላልፎ መንገዶች ወይም ዘዴዎች የየራሳቸው ጠንካራ ጐን ቢኖራቸውም እንደዚሁ የሚታይባቸው የተስተላልፎ ድክመትም አለ፡፡ በመሆኑም እንደ መፍትሄ ሊወሰድ የሚገባው የቃል ግጥም ተስተላልፎ በሶስትና በአራት ቀንበቦ ማስቀመጥ ተገቢ አለመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሱት የተስተላልፎ ንድፈ ሀሳቦች አንደኛው በሌላኛው ሊደገፍና ከድክመቱ ሊወጣ የሚችልበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህኛው ሌላኛው ይበልጣል ወይም ያንሳል ከማለት ይልቅ አንደኛው የሌላኛውን ክፍተት በመሙላት የቃል ግጥምን ተስተላልፎ ህያው ያደርጋሉ ወደሚለው እሳቤ መሄዱ ተገቢ ነው፡፡

## 2.2.3. የቃል ግጥም ባህርያት

ቃልግጥም ፈርጀ ብዙ ባህሪያት ቢኖሩትም በዚህ ክፍል ቃልግጥም ፣ የመከወን እና የመለወጥ፣ ባህርያት ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሌሎቹ የቃል ግጥም ባህርያቶች በእነዚሁ ዋና ዋናዎቹ ላይ ሊጠቃለሉ ስለሚችሉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቃላዊነት፣ ዜማዊነት፣ ድግግሞሽ ሁሉ የቃል ግጥም ባህሪ ሆነው ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ (ዘሪሁን 1992፣25፣ ብርሃኑ ገበየሁ 1995÷5)

የቃል ግጥም አንዱ ባህሪ ተለዋዋጭነት ነው፡፡ የቃል ግጥም ለመለወጥ የሚያጋልጡት ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡ አንደኛው መንገድ ቃል ግጥም ተፈጥሮውና ተስተላልፎው በቃል መሆኑ ነው፡፡ በአንደበት ተፈጥሮ በአንደበት ይተላለፋል፡፡ ስለዚህ በአንደበት የሚነገርን ሙሉ በሙሉ አስታውሶ ለመከወን ስለማይቻል ይጐድላል፣ በጐደለው ከዋኙ ሞልቶ በሚከውንበት ጊዜ የነበረው ወይም የቀደመው ቃል ግጥም ላይ የቃል፣ የሐረግ ብሎም የቅርጽ ለውጥ ይከሰታል፡፡

ሌላው የቃል ግጥም ተለዋዋጭነት የሚከሰተው ከከዋኙ የክዋኔ ችሎታ፣ በክዋኔው አውድ፣ የማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ለውጦች ሲከሰቱ ቃል ግጥሙን አብሮ ከዘመኑ ጋር ለማስማማት ሲባል ሊለወጥ ይችላል፡፡ ሌላውና በሶስተኛ ደረጃ የቃል ግጥም ተለዋዋጭነት የሚከሰተው በከዋኙ አሻሽሎ ለማቅረብ ካለው ፍላጐት እና ቃል ግጥሞችን አካባቢያዊ ከማድረግ አኳያ የአካባቢ ቀለም ለመቀባት ሲባል ነው፡፡

በዚህ ጊዜ በቃል ግጥሙ የቃላት፣ የሐረጋት፣ ብሎም የአዝማች መለወጥ ሊያጋጥም ይችላል:: ስለሆነም ቃልግጥም ከወቅቱ ጋር ተስማምቶ በሙሉ ወይም በከፊል የመለወጥ ሁኔታ ያጋጥመዋል:: (Finnegan 1970:374፣ ዘሪሁን 1992:24፣ ብርሃኑ 1995:5)

### 2.2.4. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ

ይህ ንድፈ ሀሳብ ስነልሳን፣ አንትሮፖሎጂ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎርን የመሳሰሉ ዲሲፕሊኖችን ለማጥናት የሚያስችል ቴዎሪ እንደሆነ የዘርፉ ተመራማሪዎች ይናገራሉ:: ከነዚህ መካከል Bauman በማህበረ ባህሉ ያሉ ድብቅ ሁኔቶችን ለመረዳት የሚያስችል ዘዴ ነው ይላሉ (Bauman, 1987,34):: እንደዚሁም Sims እና Stephen ስለ ክዋኔ ሲያስረዱ ህዝቦች ወይም ቡድኖች በአንድ በተለየ አጋጣሚ እና መቼት የሚገናኙበት መንገድ ነው ካሉ በኋላ ይህ ግንኙነት ወይም ክዋኔ ለቡድኑ አንዳች ጉዳይን ማስገኛ ወይም የመፍጠሪያ ገቢር ነው ይላሉ::

"Basically that people communicate within specific situation and settings and the communication are 'performed' for certain reasons and in certain ways that have meaning the member of folk group." (Sims and Stephen, 2005:133).

እንደዚሁም Goldstien የተባሉ ሰው የፎክሎር ክዋኔ በእውቀት፣ በጥበብ፣ በትርጉም የተሞላ፣ተለዋዋጭነት ያለው እና የቆየውን የማህበሩን አውድ መሰረት የሚያደርግ ንድፍ ሀሳብ ነው በማለት ያብራራሉ (Goldstien 1962:95)::

ስለ ክዋኔ ፎክሎረኞች ትኩረት መስጠት ያለባቸው በአንድ የፎክሎር ዘውግ ክዋኔ ላይ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣በማን እና ለምን እንደሚከወን ማወቅ ነው:: እንደዚሁም ምን አይነት ግኑኝነት ይሁን ተግባቦት እንደተፈጠረ መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው:: የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በቡድኖች መካከል ተግባቦትን በመፍጠርና ለማህበረ ባህሉ አንዳች ጠቃሚ ጉዳዮችን በአእምሮ ውስጥ ያስጠብቃል:: (Bauman, 1992:105, Sims and Stephen 2005:134)::

ቃልግጥም ዋና ባህሪው ቃላዊ ነው ቃላዊ በመሆኑ ደግሞ ለመረሳት ይሁን ለመጠፋት ክፍት ነው። ስለሆነም እንዳይጠፋ ይሁን ህያው ሆኖ እንዲቀጥል መክወን አለበት። ይህን ብሂል (ፈ.ቃ.ደ 1984፡ 3) የስንቃል ህይወት፣ ደምስሩና የልብ ምቱ ክዋኔ እንደሆነ ያስረዳሉ። ቃል ግጥም በየዘመኑ ተዘርቶ በቅሎ አብቦና አፍርቶ ታጭዶና ተበራይቶ ወደ ጎተራ ከገባ በኋላ ተፈጭቶ ተቦክቶና ተጋግሮ ህብስቱ የሚቀርበው በክዋኔ ነው። ያለክዋኔ ቃልግጥም ፍሬ አልባ ነው። በመሆኑም በክዋኔ ነፋስ ቃልግጥም ገለባው ከጥሬው፣ እብቁን ከምርቱ በመለየት መተንተን እና መተርጎም አለበት። ለቃልግጥም መተንተንና መተርጎም ክዋኔ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።(Finnegan 1992:93)

ክዋኔ በመኖሩ በከዋኙና በታዳሚው ብሎም በማህበረሰቡ መግባባት ከመፈጠሩ ባሻገር የማህበረሰቡ ባህል፣ ደንብ፣ ህግና ስርዓት እንዲጸና ያስችላል። እንደዚሁም በቃልግጥሙና የክዋኔው ባለቤት በሆነው ማህበረሰብ መካከል የከዋኙና የቡድኑን ኃላፊነትና ግዴታዎች ጭምር በክዋኔው እንደገና እየታደሱ ይጸናሉ። ‹‹Performance involves on the part of the performer an assumption of accountability to an audience for the way in which communication is carried out›› (Bauman 1977:14)

ስለሆነም ክዋኔ በከዋኙና በሚዜምለት ይሁን በሚንጐራጐርለት ማህበረሰብ ወይም ቡድን (folk group) መካከል የደስታ ይሁን የሀዘን፣ የጣፋጭ ይሁን የምሬት ተግባቦት የሚፈጠርበት መንገድ ነው። በክዋኔ ወቅት ቀድሞ ያልነበረ ወይም ሀሩም ሆኖ የቆየ እና ታፍኖ የኖረ ህይወት ይተነፍስ ዘንድ ፍቃድ ያገኛል። በክዋኔው ርዝማኔ ልክ ብልጭ ብሎ ድርግም የሚል ነፃነት ይኖራል። ‹‹Performance heightened awareness of the act of the expression and gives licence›› (Bauman 1977:14) የክዋኔ ሐረግ ሲነሳ ወይም የክዋኔ ሀረግ ሲመዘዝ አብረው የሚሳቡ ጉዳዮች ከዋኝ፣ ተሳታፊ፣ ቃልግጥም፣ አውድ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።እነሱም እንዳቸው በሌሎቹ ላይ እየዋሉና እያደሩ ወይም እየተዳበሉ ክዋኔን ያስገኛሉ። የአንዳቸው መለየት ይሁን መጠፋት በክዋኔ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለሆነም ክዋኔ በአግባቡ ሊኖር የሚችለው እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች በአግባቡ ሲገኙ ነው። የቴክስት፣ የአውድ፣ የከዋኝና የተሳታፊ መኖር ወይም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የክዋኔ መክሰቻዎች በአንድነት መገኘት ጥሩ ክዋኔን ይፈጥራሉ። ይህን አስመልክተው ‹‹Performance the

frame creates a social space with clear boundaries in whcih performers and audience take part in the artistic and evaluative process within that space›› (Sims and Stephen, 2004:141) ቀጥሎ ከላይ የተጠቀሱትን የክዋኔ መከሰቻዎች በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡

### 2.2.4.1. ከዋኝ

ከዋኝ ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የቃል ግጥሙን ክዋኔ በዋናነት የሚመራ ነው፡፡ ከዋኝ ብዙ ጊዜ በእድሜ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃና በመሳሰሉት ጉዳዮች ተመስርቶ በሚከወነው ጉዳይ ከማህበረሰቡ ወይም ከቡድኑ በተሻለ መልኩ እውቀት ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ከዋኝ በአንድ ቃልግጥም ክዋኔ የህብረተሰቡን የህይወት ልምድ በማሳወቅ ቀዳሚ ስፍራ አለው (Dorson, 1972:286) በቃልግጥም ክዋኔ ላይ ከዋኞቹ እንደ አዝማሪ እና የቅኔ ችሎታ ያላቸውና በሙያው የተካኑ ሲሆኑ የተወሰነ ገንዘብ የሚያገኙበት አጋጣሚ አለ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እንደዚሁ ከማህበረሰቡ ተወልደው በማደጋቸው ምክንያት በአላቸው ልምድ የተሻሉ አቀንቃኝ ዘፋኝና አንጐራጓሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተሳታፊና በከዋኝ መካከል ቁርጥ ያለ ድንበር ለማበጀት አስቸጋሪ ነው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ተሳታፊው በአንድ ክዋኔ ላይ የጎደለውን እየሞላ፣ የተዘነጋውን እያስታወሰ መከወን መቻሉ ነው፡፡ በዚህና በመሰል የቅርብ ተራክቦ ምክንያቶች የከዋኝና የተሳታፊ ድንበር የሚፈርስበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ (Finnegan 1970:90፣ 1992:97፣ ብርሃኑ ገበየሁ 1995÷8)

እንደ Finnegan አገላለጽ የተሳታፊና ክዋኔ ግንኙነት በስድስት ሊከፈሉና ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነሱም ከዋኝና የተሳታፊ የታወቀ ድንበር መኖር፣ በከዋኝና ተሳታፊ መካከል ንጽጽራዊ ልዩነት መኖር፣ በከዋኝና ተሳታፊ መካከል መሰረታዊ አጠቃላይ ልዩነት መኖር፣ ንቁ ተሳታፊ መሆን፣ በከዋኝና በተሳታፊ መካከል ትንሽ ልዩነት ያላቸው እና ያለተሳታፊ የሚደረግ ክዋኔ ናቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ክፍሎች መካከል ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ያለ ተሳታፊ የሚደረግ ክዋኔ (solitary performance) የሚለው ነው፡፡ ይህ አይነቱ ክዋኔ በአብዛኛው የወፍጮ፣ የእረኞች፣ የትካዜና የብሶት እንጉርጉሮዎችን ያጠቃልላል፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች የሚከወኑ ቃልግጥሞች ብዙ ጊዜ ግለሰባዊ ስሜቶችን ስለሚመለከቱ ለተሳታፊዎች ቦታ ላይኖራቸው ይችላል፡፡

(Finnegan 1992፣98) ይህ ሲባል ግን የእነዚህ አይነት አጋጣሚዎች ፍጹም ግለሰባዊ ናቸው ማለት አይቻልም። የዚህ ጥናት መነሻ የሆነው የወፍጮ ቃል ግጥም ክዋኔ ‹‹በይ፣ አበጀሽ፣ እንዲያ በይ›› ባትባልም ሴቷ በሌሊት ተነስታ ስትፈጭ ባል ይሁን ሌሎች እንግዶች ቃልግጥሙን እየሰሙ መመሰጣቸውና ራሳቸውን መመርመራቸው አይቀርም። እንደዚሁም በግርድፍና ስልቅ ወፍጮዎች ላይ በቡድን ሆነው አውጭና ተቀባይ በመሆን የሚዘፍኑበት ሁኔታም ብዙ ነው። ስለሆነም በወፍጮ ቃልግጥም ክዋኔ ወቅት ክዋኔው ከተሳታፊ ፍጹም የጸዳ ነው ማለት አይቻልም።

### 2.2.4.2. ቴክስት

ቴክስትን ቀንብቦና ወስኖ ማስቀመጥ የሚከብድ ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት ቴክስት ከአውድና ከአጋጣሚ ተነጥሎ የወጣ ብቻውን የሚቆም አለመሆኑ ነው። በክዋኔው ላይ ለክዋኔው ፍሬ ሆነው የሚያገለግሉ ቃልግጥሞች፣ ባህላዊ ሙዚቃዎች፣ እንጉርጉሮዎች፣ ታሪኮች እንደዚሁም በክዋኔው ላይ ያሉ ቁሳዊ ባህሎች ሁሉ እንደ ቴክስት የሚወሰዱ ናቸው። ስለሆነም በቴክስትና በአውድ መካከል ያለው ዝምድና የስጋና የነፍስ አይነት በመሆን ያለ አንዱ ሌላኛው ሊኖርም ሆነ ሊጸና አይቻለውም። በወፍጮ ቃል ግጥም ላይ ከቃልግጥሙ ባሻገር ወፍጮው ወይም የሚፈጭበት መቼት እንደ ቴክስት ሊወሰድ ይችላል። በሌላ አተያይ ደግሞ ቃልግጥሞቹ እንደ አውድ ሊያገለግሉ ይችላሉ ።ስለሆነም ይህ ቴክስት ነው፤ ያኛው ደግሞ አውድ ነው ብሎ ቋሚ ድንበር ከመተከል ይልቅ የሁለቱ ተራክቦ ያስገኘውን ትርጉም ለመረዳት መጣር ተገቢ ነው። (Amos 1992:20-35, Sims and Stephen 2005:134)

### 2.2.4.3. አውድ

የመስኩ ተመራማሪዎች ስለ አውድ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። እነሱም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስለ አውድ ብያኔ ሲያስቀምጡ ዞረው የሚገናኙበት ቀለበት አለ። ይህ ቀለበት አውድ ማለት አንድ ፎክሎራዊ ይሁን ባህላዊ ድርጊት እንደዚሁም ስነ-ቃል የሚከወንበት ጊዜና ቦታ ነው።የፎክሎር መረጃ የሚሰበሰብበት እና ክዋኔው የሚከወንበት ተጨባጭ የሆኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ሁሉ አውድ ናቸው። አውድ ማህበራዊ አውድ እና ተጨባጭ አውድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። (Amos 1992:21,

Sims and Stephen 2005:134) ማህበራዊ አውድ ሰፊ እና በውስጡ ሊዘረዘሩ የሚችሉ ማህበራዊ ቡድኖችን የሚያጠቃልል ሲሆን ቤተሰብ፣ ጉሳ፣የሚከተሉት ሃይማኖ ፣ሥራ የመሳሰሉትን ማህበራዊ ጉዳዮች ያካትታል። (Amose 1992:25-27፣ Shoemaker 1990:8፣ Sims and Stephen 2005:159)። ከላይ እንደተገለጸው የሰዎች የተግባቦትና የግንኙነት ደረጃዎች የተለያዩ ናቸው። ይህ ልዩነት የሚከሰተው ወይም የሚፈጠረው ደግሞ በማህበራዊ አውድ አማካኝነት ነው። በዚህ የተነሳ አንድ የቃል ግጥም በቴክስት ደረጃ አንድ ቢሆንም እንኳን በሚከወንበት ማህበራዊ አውድ ልዩነት ያስከትላል ማለት ይቻላል።

ተጨባጭ አውድ አንድ ቃልግጥም የሚከወንበት ጊዜና ቦታ መቼት የሚለውን የሚያጠቃልል ነው። ክዋኔው በሚከወንበት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የሚከወንበት ጊዜ ጧት፣ ማታ፣ ሌሊት፣ በጋ፣ ክረምት የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን እንደዚሁም ከዋኙ የሚገለገልባቸው መሳሪያዎች፣ የከዋኙ እንቅስቃሴ እና ድምጽ ሁሉ በዚሁ ተጨባጭ አውድ ስር የሚመደቡ ናቸው።ይህ አውድ አንድን የፎክሎር አይነት ለመተንተንና ለመረዳት የተሻለ ጠቀሜታ አለው። ክዋኔውን ከተፈጥሮ አውድ ጋር ለማግኘት ስለሚያስችል ጊዜን፣ ቦታን እና የክዋኔውን ድባብ ስለሚያስቃኝ የቃልግጥሙን አንድምታ የማህበረሰቡን እሴት እና የቃል ግጥሞቹን ምስጢር ለመረዳት ያስችላል።(Sims and Stephen 2005÷138)

በመሆኑም የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነውን የባህላዊ ወፍጮ ቃል ግጥሞችን መረጃ ለመሰብሰብ እና ለመተንተን ያመች ዘንድ ተጨባጭ አውድን መሰረት ያደረገ ጥናት ነው።ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ቃል ግጥም የመረጃ አሰባሰብ ወቅት እንደ Shoemaker (1990:8) አገላለጽ የባህላዊና ማህበራዊ አውዶች ዋና ክፍል የሆኑትን የአውድ አንድምታዎች፣ የቡድን ተግባቦት፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ ፣ ሁኔታዊ አውድ እና ተቋማዊ አውድ የመሳሰሉትን ስድስት የአውድ ዋነኛ ማጠንጠኛ መንገዶችን በመመርኮዝ እና መረጃ በመሰብሰብ ትንታኔ ተሰጥቷል። ከትንታኔው በኋላ የባህላዊ ወፍጮ ቃልግጥሞች ክዋኔ ለምን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት ይከወናሉ፣ ምን ማህበራዊ አንድምታ እና እሴት አላቸው ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ አስገኝቷል።

## 3. የጥናቱ አካባቢ

በዚህ ምእራፍ የእብናት ወረዳ መልክአ ምድር፣የህዝብ ስርጭት፣ማህበራዊ ግንኙነት ፣መሰረተ ልማት፣ኢኮኖሚ እና የነዋሪዎቹ የስራ ክፍፍል ይቃኛሉ።

### 3.1. የጥናቱ አካባቢ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ካሉት 13 ዞኖች መካከል ደቡብ ጐንደር መስተዳድር ዞን አንዷ ናት። ደቡብ ጎንደር ላይ ጋይንት፣ ታች ጋይንት፣ ስማዳ፣ ምዕራብ እስቴ፣ ምስራቅ እስቴ፣ ደራ፣ ፎገራ፣ሊቦ ከምከም፣ፋርጣ እና እብናት የተባሉ አስር የገጠር ወረዳዎች አሏት። እንደዚሁም ደብረ ታቦር፣ ንፋስ መውጫ፣ መካነ ኢየሱስ፣ ወረታ እና አዲስ ዘመን የተባሉ አምስት የከተማ አስተዳድር ወረዳዎችን ይዛለች። ከእነዚህ ወረዳዎች መካከል ይህ ጥናት የሚያተኩረው በእብናት ወረዳ ነው። ቀጥሎ ስለ እብናት ወረዳ ዝርዝር መረጃ አቀርባለሁ።

#### 3.1.1. የእብናት ወረዳ

የእብናት ወረዳ ከአዲስ አበባ 714 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ከክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር 122 ኪ.ሜትር እና ከዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ታቦር ደግሞ 109 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። (የእብናት ወረዳ የመ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት የጽሑፍ መረጃ 2005፣ አቶ በቃሉ ዋለ ካሴት ቁጥር 1)

#### 3.1.2. መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ

የወረዳዋ የመሬት አቀማመጥ 15% ሜዳማ፣ 45% ተራራማ፣ 30% ወጣገባ፣ 10% ሸለቋማ ነው። የወረዳዋ አመታዊ የዝናብ መጠን ደግሞ ከ500-600 ሚ.ሜትር የሚደርስ ሲሆን የወረዳዋ የሙቀት መጠን ደግሞ ከ25-30 ዲግሪ ሴልሺየስ ይደርሳል። ወረዳዋ ከባህር ጠለል በላይ ያላት ከፍታ ከ1800-2150 ሜትር ይደርሳል። ወረዳዋ ደጋ፣ወይና ደጋ እና ቆላ የአየር ንብረቶች አሏት። ከእነዚህ የአየር ንብረቶች መካከል ወይና ደጋው ክፍል የወረዳዋን ሰፊ ቦታ ይሸፍናል። ስለሆነም ደጋ 15%፣ ወይና ደጋ 50%፣ እና ቆላማ 35% ይሸፍናል። (የእብናት ወረዳ መ.ጉ.ኮ. ጽ/ቤት 2005 የጽሑፍ መረጃ፣ አቶ በቃሉ ዋለ 2005፣ ቃለ መጠይቅ ካሴት ቁጥር 1)

ወደ ተከዜ ወንዝ አካባቢ ያለው በረሃማ የመሬት ክፍል በእጣን ዛፍ እና ሙጫ የተሸፈነ ነው። ወረዳዋን አልፎ አልፎ ቆላማውን አካባቢ ድርቅ የሚያጠቃው ሲሆን በደጋማው አካባቢ ደግሞ በአንጻሩ እንደ ቅላላ ያሉ የደጋ መልዛ ተራሮች ደግሞ አብዛኛውን በአመት ውስጥ በደመና እና በጉም የሚሸፈኑበት ጊዜ ብዙ ነው።

የእብናት ወረዳ በምስራቀ የላይ ጋይንት ወረዳ፣ በሰሜን ምስራቅ የሰሜን ወሎ ወይም የቡግና ወረዳ፣ በምዕራብ አቅጣጫ የሊቦከምከም ወረዳ፣ በሰሜን የምስራቅ በለሳ ወረዳ፣ በሰሜን ምስራቅ የዋግኽምራ ዞን ወይም የድሀና ወረዳ እና በደቡብ አቅጣጫ ደግሞ የፋርጣ ወረዳዎች ያዋስኗታል። የተከዜ ወንዝ ከምስራቅ ወደ ሰሜን አቅጣጫ አቋርጦ በመሄድ ከሰሜን ወሎና ከዋግኽምራ ዞኖች ጋር ይለያታል።

የእብናት ወረዳ በውስጧ አባዝንጀር፣ ሸኚር አምባ፣ ቅለላ እና አጋልሺት የሚባሉ ሰንሰለታማ ተራሮች አሏት። እንደዚሁም በወረዳዋ ውስጥ ጥቅን፣ ንሲ፣ ማላ፣ መወን፣ ሲምን (በሮባር)፣ አቢያ፣ ቢለን፣ ጎለየ እና ጣቢዛ የሚባሉ ወደ ተከዜ የሚፈሱ ወንዞች ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል የጉለየ ወንዝ ወረዳዋን ከጋይንት የሚለያት ሲሆን የንሲ ወንዝ ደግሞ ወረዳዋን ከምስራቅ በለሳ ጋር ይለያታል። (2005 ቃለመጠይቅ ካሴት ቁጥር 1፣ የደ.ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005 ዓ.ም)።

ወረዳዋ በድሮው ቆላ እብናት ደጋ እብናት፣ ቆላ መልዛ ደጋ መልዛ እና ቆላ መቀጣዋ፣ ደጋ መቀጣዋ ተብለው በሶስት የተከፈሉ ንዑስ ወረዳዎች /ግዛቶች/ የተዋቀረች ነበረች። በአሁኑ አከፋፈል ደግሞ ቋሊስ፣ አጊሳ፣ አጃ፣ ገላ ማጠቢያ እና ሰለማያ የሚባሉ አምስት ንዑስ ወረዳዎች አሏት። እንደዚሁም ወረዳዋ በ35 የገጠር ቀበሌዎች እና በሁለት የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ በ37 ቀበሌዎች የተዋቀረች ናት።

## 3.1.3. የህዝብ ስርጭት እና ማህበራዊ ግንኙነት

የወረዳዋ የህዝብ ቁጥር ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን በከተማና በገጠሩ ተለይቶ የሚታይ ነው። በከተማ፣ ወንድ 7,162፣ ሴት 9,703 የህዝብ ቁጥር ሲኖረው እንደዚሁም የህዝብ ስርጭቱ በገጠር ደግሞ ወንድ 128,402፣ ሴት 118,853 ደርሷል።

በወረዳዋ ውስጥ የወንዱ ቁጥር 135,563 እና ሴት 128,557 ሲሆን ጠቅላላ የወረዳዋ ህዝብ ቁጥር 264,120 ነው፡፡ (የደ.ጐንደር ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005)

ከወረዳዋ ህዝብ 96.5% የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ 2.5% ያህሉ ደግሞ የእስልምና ሃይማኖትን ይከተላሉ፡፡ የሁለቱም ሃይማኖቶች ተከታዮች በመቻቻልና በመደጋገፍ የሚኖሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ የስጋ ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡ በሰርግ፣ በጥምቀት፣ በመውሊድ እና በመሳሰሉት ክብረ በአላት ወቅት አብረው የመብላትና የመጠጣት የቆየ ልማድ አላቸው፡፡ በወረዳዋ 10 መስጊዶች እና ከ246 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ /የደ.ጐንደር ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005፣ አቶ በቃሉ ዋለ 2005 ቃለ መጠይቅ ካሴት ቁ. 1/

### 3.1.4. ኢኮኖሚ

የእብናት ወረዳ አብዛኛው ህዝብ 93.33% የሚተዳደረው በግብርና ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 1.35% በንግድና በመንግስት ስራ ኑሯቸውን ይገፋሉ፡፡ 0.5% ደግሞ በሽመና፣ በሸክላ ስራ እና በብረት ቅጠቀጣ /በእደ ጥበብ ስራ/ የሚተዳደሩ ሲሆን ቀሪዎቹ 3.15% ደግሞ በቀን ስራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡

አልፎ አልፎ ድርቅ የሚከሰት ቢሆንም የወረዳዋ የአየር ንብረት ለግብርና ስራ ተስማሚ ነው፡፡ በመሆኑም በወረዳዋ ውስጥ በደጋማው ክፍል ባቄላ፣ ገብስ፣ ሽምብራ፣ ጓያ የመሳሰሉት የሰብል አይነቶች በዋናነት ይመረታሉ፡፡ እንደዚሁም በወይና ደጋማውና ቆላማው ክፍል ደግሞ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ማሽላ፣ ተልባ፣ ጥጥና አተር የመሳሰሉት ሰብሎች በብዛት ይመረታሉ፡፡ በወረዳዋ ወይና ደጋና ቆላማ አካባቢ ንብ የማነብ ስራ በሰፊው የሚሰራ ሲሆን የቀንድ ከብቶችና ፍየሎች በብዛት ይረባሉ፡፡ በደጋማው አካባቢ ደግሞ በጐችና ፈረሶች በብዛት ይረባሉ፡፡ በወረዳዋ በስፋት በበሬ የማረስ ልምድ የተዘወተረ ቢሆንም በደጋማው አካባቢ በፈረስ ይታረሳል፡፡ (የደ.ጐንደር ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005፣ አቶ አስቻለው ፈጠነ 2005 ቃለ መጠይቅ ካሴት ቁጥር1)

### 3.1.5. መሰረተ ልማት

የእብናት ወረዳን የመሰረተ ልማት ሁኔታ ስንመለከት የወረዳዋ ርዕሰ ከተማ እብናት ሰለማያ የተባለች ንዑስ ወረዳ የ24 ሰዓት መብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው። ከአዲስ ዘመን ከተማ እስከ እብናት 42 ኪሎ ሜትር ደረጃውን የጠበቀ የገጠር መንገድ አለ ። እንደዚሁም ከእብናት በለሳ በገጠር መንገድ ድርጅት የተሰራ 42 ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ ይገኛል።

የወረዳዋን ከተማ ከገጠር ቀበሌዎች ለማገናኘት በህብረተሰቡ ድጋፍ መንገዶች በመሰራት ላይ ናቸው። ነገር ግን ወደ ቆላማው አካባቢ እንደ ደብር ተክለሃይማኖት፣ ግብጻዊት ማርያም፣ አዲያ ቁርቋራ በመሳሰሉት ቀበሌዎች የመኪና መንገድ ስራ እንቅስቃሴ አይታይም።

ወረዳዋ የባንክ አገልግሎት በቅርቡ ያገኘች ሲሆን 7 ጤና ጣቢያዎች፣ 3 አዳጊ ጤና ጣቢያዎች እና 42 ጤና ኬላዎች ይገኙባታል። የትምህርት ተቋማትን ስንመለከት ደግሞ 19 አማራጭ ት/ቤቶች፣ 87 መደበኛ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና 3 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሏት። አንድ የመሰናዶ እና አንድ የቴክኒክና ሞያ ትምህርት ቤት በወረዳዋ ይገኛሉ። (የእብናት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005 እና የደቡብ ጐንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም የጽሑፍ መረጃ 2005)።

### 3.1.6. የነዋሪዎቹ የስራ ክፍፍል

በእብናት ወረዳ በሴቶችና በወንዶች መካከል የስራ ክፍፍል ይታያል። ወንዶች እርሻ በማረስ፣ ምንጣሮ በመመንጠር፣ ንግድ በመነገድ ኑሮአቸውን ይገፋሉ። እንደዚሁም አደባባይ መውጣት፣ በሽምግልና፣ በስብሰባ፣ በሃይማት እና በእድር ቦታዎች በመገኘት ሁሉ አብዛኛውን ድርሻ ወንዶች ይወስዳሉ። (አቶ አለቤ ጥሩነህ፣አቶ ዋናው ደማም፣አቶ ለገሰ አለሙ፣ቄስ አሰፋ ይግዛው፣አቶ ቡላድ አየለ 21/05/ 2005 ዓ.ም የቡድን ውይይት)

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች የስራ ክፍፍሉን ብዙውን ድርሻ ይወስዳሉ። የሚያከናውኗቸው ስራዎችም በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ ተብለው በሁለት ክፍሎች


ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በቤት ውስጥ እህል መፍጨት፣ እንጀራ መጋገር፣ወጥ መስራት፣ልጅ ማሳደግ የመሳሰሉትን ስራዎች ይሰራሉ፡፡ከቤት ውጭ የሚያከናውኗቸው ስራዎች ደግሞ እንጨት መልቀም፣ ውሐ መቅዳት፣ ልብስ ማጠብ የመሳሰሉት ሲሆኑ በአካባቢው ማህበረሰብ የስራ ክፍፍል መሰረት ለወንዶች የተሰጠውን ጉልጓሎ፣አረም፣ አጨዳ እና አውድማ ልቅላቆ ስራዎችን ጭምር ያከናውናሉ፡፡ እነዚህን በርካታ ስራዎች በቀን ብቻ ሰርተው ማጠናቀቅ ባለመቻላቸው ምክንያት የወፍጮውን ስራ በአብዛኛው በሌሊት ይፈጫሉ፡፡ የመኪና ወፍጮ አልፎ አልፎ ቢኖርም እንኳን በመኪና የተፈጨው አይበረከትም በሚል እምነት፣ የማስፈጫ ገንዘቡ ውድ በመሆኑ እና ባሎቻቸው ለማስፈጨት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የተነሳ ሴቶች አሁንም ድረስ ወፍጮ የመፍጨት ኃላፊነት አለባቸው (ወ/ሮ እርጎዬ ለገሰ 14/05/ 2005 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ ካሴት ቁጥር 1)

ስለዚህ ከሴቶች ፈርጀ ብዙ ስራዎች መካከል መፍጨት አንዱ እና አሰልቺው ስራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ "ሴቶች በዚህች ወረዳ በተለይ ወደ ቆላማው አካባቢ አሁንም ድረስ ወፍጮ ይፈጫሉ፡፡" (አቶ አብቦ ሹመት 2005 ቃለ መጠይቅ ካሴት ቁጥር 1)"

ባህላዊ ወፍጮ እናት ወፍጮ፣መጅ (የወፍጮ ልጅ)፣ ቋት፣መቋቻ ፣ መውቀሪያ እና ሙሬ የተባሉትን ቁሳቁሶች አካቶ የያዘ ነው፡፡ እናት ወፍጮ የሚባለው ከስር በኩል የሚገኘው ትልቁ ድንጋይ ሲሆን ለመፍጨት ትልቁን ድርሻ ወስዳል፡፡ መጅ ደግሞ ከእናት ወፍጮው በላይ በኩል እየተመላለሰ እህሉን የሚያደቀው ክፍል ነው፡፡ መቋቻ ከወፍጮው በኋላ በኩል የሚገኝ በጭቃ የተሰራ እና ጥሬው እህል የሚቀመጥበት ክፍል ነው፡፡ ቋት ደግሞ የተፈጨው እህል የሚከማችበት ከጭቃ የተሰራ ጎድጓዳ ቦታ ሲሆን ሙሬ ደግሞ ከዘንጋዳ መቃ ልጣጭ፣ ከአክርማ ሰበዝ እና ሙሬ ተብሎ ከሚጠራው የሳር ዓይነት የሚዘጋጅ ሲሆን እህል ከመፈጨቱ በፊትና በኋላ ወፍጮን ለመጥረግ የሚያገለግል ነው፡፡

ከመስክ የተመለከትኳቸው ባህላዊ ወፍጮዎች ከኋላ በኩል ከፍ ከፊት በኩል ዘቅዘቅ ብለው ከካባ እንደሻው ወፍጮ በስተቀር ከበሩ በስተቀኝ በኩል የተተከሉ ናቸው፡፡ ከኋላ በኩል ከፍና ከፊት በኩል ዘቅዘቅ ብለው መተከላቸው እህል ለመፍጨት አመቺ እንዲሆን የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ወፍጮዎቹ ከበር አካባቢ መተከላቸው ደግሞ አንድም

ወፍጮውና የፈጪዋ የዘፈን ድምጽ የተኙትን ሰዎች እንዳይረብሽ በማሰብ ነው፡፡ አንድም እህል ከመፍጨት በተጨማሪ ከጋጥ ያሉ ፍየሎች፣ ከቆጥ ያሉ ዶሮዎች እና ከበረት ያሉ ከብቶች በአራዊት እንዳይጠቁ እና በሌባ እንዳይነዱ የጥበቃ ስራ ለመስራት በማሰብ ነው፡፡ ወፍጮዎቹ ከበሩ በስተቀኝ በኩል መተከላቸው ደግሞ የቤቶቹ በር በስተቀኝ በኩል ስለሚከፈት ዱቄቱን ከነፋስ ለመከላከል ስለሚያስችለ ነው፡፡ (ዋጋው አወቀ፣ ቡላድ አየለ 21-05-2005 ቃለ መጠይቅ)




ፎቶግራፍ /1 ወ/ሮ ፍቅሬ አለሙ

( በ27/05/05 ደብር ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

# 4.በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና

ይህ ምእራፍ በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና የሚሰጠበት ክፍል ነው፡፡ ትንታኔው ሴቶቹ በተደጋጋሚ በሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የሚያነሷቸው ጉዳዮችም በአብዛኛው ምሬት፣ ውዳሴ፣ ፍቅር፣ ንቀት፣ ክፋትና ደግነት ናቸው፡፡

## 4.1. ምሬትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች በሚደርሱባቸው የስራ ጫናዎችና መሰል እንገልቶች ምክንያት ምሬታቸውንና ብሶታቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ አጋጣሚዎች መካከል በወፍጮ ስራ ላይ የሚያዜሟቸው ግጥሞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቃል ግጥሞቹ የተደራጁበትና የተዋገኑበት መንገድ በወቅቱ ከነበረው የወፍጮ አውድ እና የከዋኞቹ ሁኔታ በመነሳት ነው፡፡ ስለሆነም በሌላ መቼት ግጥሞቹ ሌላ አይነት ይዘት፣ ትርጓሜ እና አንድምታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የግጥሞቹ ትንታኔ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡ በየርዕሶቹ ስር እምስት አምስት ቃል ግጥሞች ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.1.የወፍጮ ስራ ምሬትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች


*13.[3]ሰው በእጁ አልገደልኩኝ*
*ሰው በዓይኔ አልገደልኩኝ*
*በጥርሴ አልገደልኩኝ*
*እጣዬ ሆነና ለወፍጮ ታደልኩኝ፡፡*
*/ክርክም አዳነ 22-05-2005/*

ይህ መረጃ ረቡዕ 22/05/2005 ዓ.ም ግብጣዊት ቀበሌ ወ/ሮ ክርክም አዳነ ወፍጮ ስትፈጭ ያዜመችው ነው፡፡ ግጥሞቹ በተሰበሰቡበት ማህበረሰብ እብናት ወረዳ ሰው የገደለ ግለሰብ ጥፋተኛና ወንጀለኛ ተብሎ ሃይማኖቱና ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ‹‹አጥንተ ሰባራ›› በመባል ለአበልጅነት ለጋብቻ ማህበርተኛነት ለዕድር አባልነት አይፈለግም፡፡ ከእነዚህና ከመሰል ማህበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ ይገለላል፡፡(ክርክም 22/05/2005)

3.ይህ ቁጥር በአባሪ ሶስት(የግጥሞቹ ስብስብ) ውስጥ የተሰጠውን ቁጥር ያመለክታል

ዓይነ-በላ የሚባለው በማህበረሰቡ አጠራር ‹‹ቡዳ›› እየተባሉ የሚጠሩት ከላይ ከተጠቀሱት ሃይማኖታዊና ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች የተገለሉ ናቸው፡፡ ‹‹በጥርሴ አልገደልኩኝ››

ያለችው ሀረግም ያዜመችው ሰው በጥርሳቸው በጫጭቀው ጉዳት እንደሚያደርሱ አራዊት አለመሆኗን ያመለክታል፡፡ከዋኟ ከላይ የተጠቀሱት ነፍሰ ገዳይ፣ ‹‹ቡዳ›› እና አራዊት እንደሚፈፅሙት ያለ የከፋ ድርጊት አልፈፀምኩም ግን እጣዬ ሆኖ እንደ ወንጀለኛ፣ እንደ ክፉ ሰሪ ተቆጥሬ ወፍጮ ፈጪታ ሆኜ እንድኖር ተፈርዶብኛል በማለት በዕጣ ፈንታና በእሷ መካከል ያለውን የመረረ ቁርኝት ትገልፃለች፡፡



ፎቶ 2 ወ/ሮ ክርክም አዳነ
(በ22/05/05 ግብጻዊት ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)


*49. ቢወቅሩት አይሰላ ወፍጮዬ ነኳላ*
*ባሌ መናጢ ነው ራቱን ካልበላ፡፡*
*/አዱኛዩ ተሾመ[4]፣ 15-05-2005፣ ማስታወሻ/*

---

4..በጥናቱ የተጠቀሱት መረጃ ሰጪዎች ፈቃደኝነታቸው ተጠይቆ መጠሪያ ስማቸው ተወስዷል፡፡ የቃል ግጥሞቹን እውዳዊ ፍቺ ለማምጣት ሲባል ግጥሞቹ የተከወኑባቸው መቼቶች ቀናት ወራትና ዓመተምረት ተገልፀዋል፡፡

በ15/05/2005 ዓ.ም ከአዱኛዬ ተሾመ የተገኘ ግጥም ነው፡፡ ግለሰቧ የፈጨችና የዘፈነችውበማለዳ ተነስታ ሲሆን ከወላጆቿ ድግስ በመጣችበት ጊዜ ነው፡፡ አዱኛዬ ፎቶ ግራፍ ትነሳ እንጂ ለቪዲዮ ካሜራ ለመቅረፀ ድምፅ አብረውኝ የነበሩትን ሰዎች እና ለክብረ በአል የመጡትን እንግዶች በመፍራት ፈቃደኛ አልነበረችም፡፡ እሷ ውስጥ እየፈጨች እኔና መሰል ሰዎች ጥግ ላይ ቁጭ ብለን በማዳመጥ ቃል ግጥሙን በማስታወሻ ደብተር ያዝኩኝ፡፡ የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ሴት በሁለት ጠገግ እና ውጥረት ላይ የቆመች ናት፡ በአንድ በኩል ወፍጮው ስል ባለመሆኑ ሥራዋን አድካሚ አድርጎታል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ የባልየው መናጢ መሆን በተጨማሪ የሚፈጨው እህል ደርሶ ለባሏ የምታቀርበው ምግብ በጊዜ እንዳታቀርብ አድርጓታል፡፡ በጊዜ ካልደረሰ ደግሞ ባሏ የሚያመጣባባት ቁጣና ግልምጫ ያሳስባታል፡፡ ‹‹ባሌ መናጢ ነው እራቱን ካልበላ›› የሚለው ስንኝ የባሏን ሀይለኝነትና ግልምጫ ተደባዳቢነት ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በሁለት ግራና ቀኝ ጥፊ እየተመታች ኑሮዋን ትገፋለች ማለት ይቻላል፡፡



ፎቶ ግራፍ /3 ወ/ሮ አዱኛዬ ተሾመ

( በ15/05/05 መና ዲቅ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

ባልየው የወፍጮውን መበላሸት ከምንም ሳይቆጥር ራቱን በጊዜ ካልበላ ከታገሰ በቁንጥጫ፣ አለያም በጡጫ እና በእርግጫ መከራዋን የሚያበላት መሆኑ የግጥሙ አንድም ታያሳያል፡፡ በዚህ ምክንያት ነገሮቹ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› በመሆን

በዚህኛው ወፍጮው በዚያኛው በኩል ባልየው በመተጋገዝ በግለሰቧ ኑሮ ላይ የኮሶ ጽዋ ያጨልጧታል፡፡

*1.እጀን ለብር አምባር ስመኘው ስመኘው*
*እግዜር ክፉ ሰው ነው ከወፍጮ አቆራኘው፡፡*
*/ውብነሽ ታከለ ካሴት ቁጥር 9/*



ፎቶግራፍ/ 4 ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ

( በ08/05/05 ቁርቋራ አዲያ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

በእብናት ወረዳ አካባቢ ልጃ ገረዶች በተዳሩ ጊዜ ብር አምባር የሚባል ዱከት ወይም የእጅ ካቴናና መሰል ነገር ከእጃቸው ያጠልቃሉ፡፡ ቃል ግጥሙን በወፍጮ ላይ ያቀነቀነችው ባለታሪክ የሁልጊዜ ህልሟና ምኞቷ በአካባቢው ባህል እንደ መሰል እህቶቿና ጓደኞቿ ተድራ ወግ ማዕረግ ማየት ነበር፡፡ ከዚያም ሲያልፍ ወልዳ መሳም፣ አሽታ መቃም ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ምኞቷና ስኬቷ ባለመገናኘታቸው ምክንያት ከወፍጮ ጋር አቆራኝቷታል። የዘወትር መገኛዋ ወፍጮ ስር ሆኗል። እጇ ብር አምባር አያጠልቅም፤ እንሶስላ አይሞቅም። ያልታደለው የግለሰቧ እጅ የወፍጮ መጅ መጨበጥ የዘወትር ተግባሩ ሆኗል። በዚህ አሰልቺ ወፍጮ የመፍጨት ተግባር የተማረረችው ግለሰብ የሰማይና የምድሩን ሁሉ ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን ትሞግታለች። በየቤተ እምነቶቹ እግዚአብሔር የሚመሰልበትን የርህራሄ፣ እና የአዛኝነትን ባህርያት በመንጠቅ የማህበሩን እምነትና ህግ ጭምር ትንዳለች። ‹‹እግዜር ክፉ ሰው ነው ከወፍጮ አቆራኘኝ›› የሚለውን ስንኝ ስንመለከት ለባለ ታሪኳ ርዕይ ከንቱ መቅረት እግዚአብሔር ኃላፊነቱን እንዲወስድ የሚጠቁም ነው። ፈጣሪዋን በሰው ከመመሰሏ ባሻገር ‹‹ክፉ ሰው›› በማለት ታማርራለች። ምኞቷና ተግባሯ አራባና ቆቦ የሆነባት ባለታሪክ ፈጣሪዋን ‹‹ክፉ›› ብላ በመናገር ከወፍጮው ድካም፣ ከመጁ ቁስል እረፍት ትናፍቃለች። ወይም ለዚህ ተግባር የዳረጋትን ፈጣሪዋን በመገሰጽ የአካል እረፍት ይሁን የመንፈስ ድህነት ለማግኘት ትጥራለች።

*2. ወፍጮው ውረድ ውረድ ቋቱ ሙላ ሙላ*
*እንደልብ አይገኝ የሰው ቤት እንጀራ ::*
*/ካባ እንደሻው ካሴት ቁጥር 3/*

ቃል ግጥሙ አርብ 17/05/2005 ዓ.ም አጊሳ ቀበሌ ወጪኝ ማርያም ጎጥ ከአቀንቃኟ ካባ እንደሻው የተገኘ ነው። የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ በሰው ቤት ውስጥ ተቀጥራ የምትሰራ መሆኗን በቃለ መጠይቅ ነግራኛለች። ከምታከናውናቸው ሥራዎች መካከል አድካሚውና ጊዜዋን የሚወስደው ወፍጮ ነው። ግለሰቧ የሰው ቤት እንጀራን ያነሳችው አንድም ድካም፣ ውርደት፣ ንቀት፣ ስድብ፣ ግልምጫና ቁንጥጫ የተቀላቀለበት ነው። ከዋኟ ይህን የስቃይና የመከራ እንጀራ ከወፍጮ ስር እየዋለች ትመገባለች።

ከወፍጮ ሥራ በተሻለ የዕለት ጉርሷን፣ የአመት ልብሷን የሚሰጣት ማንም አዛኝ ይሁን ጀግና የለም። በግለሰቧ የሰው ቤት እንጀራ ተማላጅ ይሁን ተለማኝ፤ አዛኝ ይሁን ጀግና ወፍጮው ነው። ስለሆነም ለወፍጮው አቤት በማለት ተማጽኖ ታቀርባለች። ‹‹ወፍጮውውረድ ውረድ ቋቱ ሙላ ሙላ›› የሚለው ስንኝ የቋቱ ዱቄት እንቅብ በሞላ ቁጥር የባለ ታሪኳ ስቃይ ይቀንሳል። ስለሆነም ወፍጮው የመለመን፣ የመማለድ እና በእሱ በጐ ፈቃድ የዕለት ጉርስ የማስገኘት ስልጣን አለው። የግለሰቧ

ህልውና በወፍጮ ላይ የተመሰረተ መሆኑ እና መፍጨት ብቻ ሳይሆን ቋቱ በዱቄት ካልተትረፈረፈ ቤቱ ጠኔ እንደሚሆን ቃልግጥሙ ይጠቁማል። ‹‹እንደ ልብ አይገኝ የሰው ቤት እንጀራ›› የሚለው ስንኝ የሰው ቤት እንጀራ ምን ያህል ከባድ እና እንደ ኮሶ የመረረ መሆኑን የሚጠቁም ነው። ለዚህም ማጠየቂያሚሆነው ግለሰቧ ተቀጥራ ከምታገለግልባቸው ሰዎች ይልቅ ግዑዝ የሆነው ወፍጮ በንጽጽር ተሸሏታል። ወፍጮው ከሰላና ከተመቸ እንደምንም በልቼ አድራለሁ በማለት በወፍጮውና በእሷ መካከል ያለውን የቅርብ ቁርኝት ትጠቁማለች።




ፎቶግራፍ /5 ወ/ሮ/ ካባ እንደሻው

( በ17/05/05 አጊሳ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

*3. ዱር ውዬ ስመጣ በላኝ ረማጨው*
*ከቤት ስገባ ግርድፍ ስልቅ ወፍጮው*
*ከእንግዲህ አልሰላም መሄዴ ነው ትቸው፡፡*
*/ቦሴ ውብሸት /15-05-2005/ ቃለመጠይቅ/*

ይህን መረጃ ግለሰቧ አይነአፋር በመሆኗ እና በእለቱ ቃና ዘገሊላ በአል የተጠሩ ብዙ እንግዶች ስለነበሩ ቀረፃውንና ቪዲዮ ካሜራውን አልፈቀደችም፡፡ ይሁን እንጂ ፎቶ ግራፍ እና በማስታወሻ መረጃ እንድይዝ ፈቅዳልኛለች፡፡ የእናት አባቷ አገር አጃ ፋሲለደስ ሲሆን አሁን ሦስተኛ ባሏን አግብታ መና እንደምትኖርና ከደጋ ወደ ቆላ ተድራ መምጣቷን ነግራኛለች፡፡ (ቦሴ ውብሸት15/05/ 2005 ቃለ መጠይቅ)



ፎቶግራፍ 6 ወ/ሮ ቦሴ ውብሸት

( በ15/05/05 መና ዲቅ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

ግጥሙ ሴቶች በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያለባቸውን የስራ ጫና የሚገልጽ ነው፡፡ እንጨት ለመልቀም፣ ውሃ ለመቅዳት ከቤት ወጥተው ወደ ውጭ በሚሄዱበት ወቅት አካባቢው ቆላ ከመሆኑ የተነሳ የጸሐዩ ሐሩር ያቃጥላቸዋል፡፡

ከቤት ሲመለሱም ቢሆን የቤት ስራ ናላቸውን ያዞራቸዋል፡፡ ‹‹ዱር ውዬ ስመጣ በላኝ ረማጫው›› የሚለው ስንኝ አካባቢው ቆላ ከመሆኑ የተነሳ የፀሐዩ ሐሩር ከቤቱ ስራ ጋር ተደምሮ ያሰቃያት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ቦሴ የተባለችው ሴት ከጫካ ገብታ እንጨት ሰብራ ተመልሳቤቷ ስትገባ እረፍት የላትም፡፡ ይልቁንም የጥራጥሬው ግርድፍ እና የልም እህሉ ስልቅ አይኑን አፍጥጦ ይጠብቃታል፡፡ የቤት ውስጥና ከቤት ውጪ ያሉ አሰልቺ ስራዎች ባስቸጋሪ የአየር ንብረትና ቦታ ስለገጠማት ምሬቷ ያይላል፡፡ ብሶቷ ይገነፍላል፡፡ በምንም አይነት መንገድ ይህን ህይወት ለመቀጠል እንደማትችል ትወስናለች፡፡ ከዚህ አይነት ትዳር ይልቅ መሰደድን ይሁን ቤቱን ጥላ መሄድን ትመርጣለች፡፡ በትዳር ላይ ታምጻለች፡፡

‹‹ከእንግዲህ አልሰላም መሄዴ ነው ትቸው›› የሚለው ስንኝ ግለሰቧ ሀብቱን ንብረቱን፣ ጨርቁን ማቄን ሳትል ቤቷን (ደጃፍ እንደመለሰ፣ ማጀት እንደጐረሰ) ለባልየው ለቃ ለመውጣት መወሰኗን የሚጠቁም ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ስለ ወፍጮ ሥራ የተቀነቀኑትን ቃልግጥሞች ሲታዩ የወፍጮ ስራ የሴቶቹ የምሬት ህይወት የሚታይበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 4.1.2. ሴት በመሆን የሚደርሱ ምሬቶችን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

*59. ምነው በጨለማው ምነው በሌሊቱ*
*ጅብ አይበላሽም ወይ ልጃገረዲቱ፡፡*
*/ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ካሴት ቁጥር 8/*

ይህ ቃል ግጥም በእብናት ወረዳ በተለይም መረጃው በተሰበሰበበት አዲያ ቀበሌ ሴት ልጅ ነጻ እንቅስቃሴ የሌላት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ሴት ልጅ እኩል ከወንድ ጋር መሄድ እንደማትችል የሚገልጽ ሲሆን የማህበረሰቡ ህግ ደንብና ስርዓት ለሴቷ ጨለማ ነው፡፡ ይህን ንቃና ደቅድቃ በድፍረት ለመራመድ ከሞከረች ሴቷ ጅብ ይጠብቃታል፡፡ ‹‹ጅብ›› ከዚህ ላይ የሚታወቀው አውሬ አይደለም፡፡በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች ይጠቁማል፡፡ ሴት ልጅ ብቻዋን ብሎም ለእይታ በሚከለክል ጫካ ይሁን ወንዝ ከወረደች ተገዶ የመደፈር እና ተጠልፎ የመወሰድ ጥቃቶች ይደርሱባታል፡፡ እነዚህ ጥቃቶች ደግሞ የመገረፍ፣ የመውደቅና የመሰበር፣ የመድማትና የመፈንከት አካላዊ ጉዳቶችን ያስከትላሉ፡፡ እንዲሁም በጓደኛ የመናቅ እና የመዋረድ የበታችነት ስሜት

የመሳሰሉት ስነ ልቦናዊ ውድቀት ይከተላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአልተፈለገ እርግዝና እና ለአባላዘር በሽታዎች ስለሚጋለጡ በመደፈር ሳቢያ በሴቶች ላይ የሚከተሉት አደጋዎች ተዳምረው ከድጡ ወደማጡ››እንዲሉ የከፋ ናቸው፡፡

ስለሆነም በጅብ ጥርስ ከመዘንጠል ይሁን ከመታኘክ አያንሱም፤ ትይዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጅብ ‹‹አይበላሽም ወይ ልጃገረዲቱ›› የሚለው ስንኝ ጅብ ሳይሆን የሚደርሱትን ጥቃቶች አስከፊነት ለመጠቆም የቆመ ተመጣጣኝ ስም ነው፡፡ ከእነዚህ እና መሰል ጥቃቶች ለመጠበቅና ለመዳን ሴት የዚህ አካባቢ ተወላጅ እንቅስቃሴዋ ሁሉ በጊዜና በቦታ የተገደበ መሆን እንዳለበት ቃልግጥሙ ያዘክራል፡፡

*65. እናቱ በድሌ ምን ያሳዝንሻል*
*ሴትነቴን እንጂ ሀብቴን ወልደሻል፡፡*
*/ደብሬ አለሜ ካሴት ቁጥር 9/*

የቃልግጥሙ አቀንቃኝ ሴት በመሆኗ ምክንያት የሀብትና የንብረት ባለቤት አልሆነችም፡፡ ልጃቸው ድሃ በመሆኗ እና በማጣቷ ምክንያት እናቷ አዝነዋል፡፡ አዘናቸው ደግሞ ከዕድል ጋር ከእጣፈንታ ጋር በማያያዝ የተፈጥሮ ስጦታ አድርገው በማሰብ ነው፡፡ ልጅቱ ደግሞ ዕድል የሚባለው በትር በድህነቷ ላይ ቦታ እንደሌለው የናቲቱን ሀሳብ በመቃወም አጽንኦት ትሰጣለች፡፡ ይልቁንም ለዚህ ችግር የዳረጋት ሴትነት እንደሆነ ታጸናለች፡፡ ‹‹ሴትነቴን እንጂ ሀብቴን ወልደሻል›› የሚለውን ስንኝ ለሴት ልጅ የሚሰጠው የሀብት ንብረት፣ የቤት ባለቤት የማሳጣት ልምድ እንደሆነ ታስረዳለች፡፡ ስለሆነም ቃልግጥሙ በዚህ አካባቢ ሴትነት ድህነት፣ ሴትነት ስቃይ፣ ሴትነት መከራ እንደሆነ አጽንኦት ይሰጣል፡፡

*67. ልጅነቴ መልካም ልጅ መውለዴ ክፉ*
*የማናት እመጫት እያሉኝ አለፉ፡፡*
*/ፍቅሬ አለሙ ካሴት ቁጥር9/*

የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ፍቅሬ አለሙ በህጻንነቷ ለማደጐ በመዳሯ ምክንያት እና በዚሁ አጋጣሚ በአስራ አምስት አመቷ ልጅ በመውለዷ በልጅነቷ ልጅ መታቀፏን ከአንደበቷ ይሰማል፡፡ ግለሰቧ ታሪኳን እንደነገረችኝ ከሆነ ባልየው ካስወለዳት በኋላ መሬት የለሽም በሚል ፈቷታል፡፡ (ፍቅሬ አለሙ ሰኞ 27/05/2005 ዓ.ም) ስለሆነም ቃል ግጥሙ እንደሚጠቁመን ልጅነቷን ትወደዋለች፡፡ ይሁን እንጂ ‹‹በመልካም አንገት እንቅርት›› እንዲሉ ልጅቷ የልጅ እናት መሆኗ ጐድቷታል፡፡

‹‹ልትታጭና ልትፌጭ›› አልቻለችም፡፡ ለጋ ዕድሜዋን ተመልክተውና አይተው የመጡት ወንዶች ‹‹የማናት እመጫት›› እያሉ አልፌዋታል፡፡ ይህን ብሶትና ገጠመኝ በማማረር ማህበረሰቡ ልማድ የሆነውን ሴት ልጅን ያለ ዕድሜዋ ለባል መስጠት ትቃወማለች፡፡



ፎቶግራፍ /7 ወ/ሮ ፍቅሬ አለሙ

(በ27/05/05 ደብር ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

*58.አንተ ላይ ደመና አንተ ላይ ሰማይ*
*የልጃገረድ ቀን አልተገኘም ወይ፡፡*
*/ውብነሽ ታከለ ካሴት ቁጥር7/*

የዚህ ቃልግጥም አቀንቃኝ ውብነሽ ታከለ የተባለችው ግለሰብ በአካባቢው ማህበረሰብ ለሴት ልጆች የሚሰጠው ቦታ አናሳ መሆኑ ተሰምቷታል፡፡ ‹‹ሴት ወደማጀት ወንድ ወደ አደባባይ›› የሚባለው የቆየ ብሂል አንገሽግሿታል፡፡ የዚህ አይነቱን ኑሮ እንደ

ጨለማ እንጂ እንደ ቀን አልቆጠረችውም። ስለዚህ ከእሷ በላይ ለሆነው ለረቂቁና ለሩቁ ፈጣሪዋ የልጃገረድ ቀን መቼ እንደሚገኝ ጸሎት ታቀርባለች።

የቃ ልግጥሙ እንድምታ በአባዊ ስርዓቱ የታሸው የማህበረሰቡ መተዳደሪያ ደንብ ለሴቶች ብሎም ለልጃገረዶች የሚመችና የሚበጅ አለመሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በመነሳት ሴቷ እኩል ፍርድና ብይን የሚታይበት ሁኔታ ከአካባቢው ማህበረሰብ በቀላሉ ይመጣል ብላ አትጠብቅም። ይልቁንም በዚያኛው አለም የልጃገረዶች በደል ይግባኝ ይሰጠው ዘንድ አቤት ትላለች። ይህ ቃል ግጥም ልጃገረዶች በጨለምተኛ ህይወት ውስጥ የሚኖሩ እና እየኖሩ መሆኑን በመግለጽ የፍትህ ያለሽ እያሉ እውነተኛ ፍርድ፣ እውነተኛ መብት እየተጠሙ ይሁን እየናፈቁ ህይወትን የሚገፉ መሆኑን የሚያዘክር ነው።

*66.እንዝርት ያለ ወልቆ አይሽከረከርም*
*አህያ ተጭና አትንከባለልም*
*የሰጐን እንቁላል ወድቆ አይሰበርም*
*ሴትነት ነው እንጂ መልክ አያሳድርም።*
*/ደብሬ አለሜ ካሴት ቁጥር 9/*



ፍቶግራፍ 8 ወ/ሮ ደብሬ አለሜ

(በ27/05/05 ደብር ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

ይህ መረጃ በ27/05/2005 ኢ.ም ደብር ቀበሌ ከወ/ሮ ደብሬ የተገኘ ነው። ግጥሙ ሴትነት ማለት በዚህ ማህበረሰብ ትርጓሜ አሰጣጥ መሰረት መጋገር፣ መጥመቅ፣ መፍተል፣ መስፋት የመሳሰሉትን ሙያዎች የሚወክል ቃል ነው። ስለሆነም ሴት ልጅ ማህበረሰቡ በጀግንነት ከፈረጃቸው ተግባራት መካከል በማረስ፣ በመማር፣ በማስተማር፣ በንግድ ስራ፣ በጦር ሜዳ አትታማም። ሴት ልጅ ራሷን ችላ የሀብት ባለቤት ልትሆን እና ልትቆም እንድትችል አይጠበቅም። ከዚህ ይልቅ ሴት ልጅ ቤት ሊያስይዛት፣ ትዳር ሊያስመሰርታት የሚችለው የተሰጣት መጠነ ሰፊ የቤት ስራ የውድድር ሜዳዋ ነው። ሞራ የመሰለ እንጀራ ስትጋግር፣ የዶሮ አይን የመሰለ ጠላ ስትጠምቅ፣ ሽታው የሚያውድ ወጥ ስትሰራ፣ በጥቅሉ በሞያዋ አንቱ ስትባል ትዳሯ እንደሚሞቅ፣ እንደሚደራ እና እንጀራ በልታ እንደምታድር ቃልግጥሙ ያስታውሳል።

‹‹ሴትነት ነው እንጂ መልክ አያሳድርም›› የሚለው ስንኝ የዚሁ ሴትን ልጅ ከስራ ጋር አገናዝቦና አቆራኝቶ ከጧት እስከ ማታ፣ ከኩተት እስከ ሽበት በቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ባሉ ስራዎች ተጠምዳ ስትባዝን እንድትኖር መደረጉንና ይህንኑ ተግባርም የተፈጥሮ ጸጋ አድርጋ እንድትቀበል የሚያሳምን ቃልግጥም ነው። በዚህ ምክንያት የዚህ አካባቢ ሴት ልጅ ለመልኳና ለውበቷ ቦታ ከመስጠት ይልቅ ከሙያ ጋር የበለጠ መታተርና መጠንከር እንዳለባት አምና እንድትቀበል መቀበል ብቻ ሳይሆን እንድትፈጽም አጽንኦት እንደሚሰጥ ግጥሙ ያሳያል።

### 4.1.3. እድልን እጣ ፈንታንና በልጅነት መዳርን የሚያማርሩ ቃል ግጥሞች

*71.አስለምደዋለሁ እገሬን ያለ ጫማ*
*እንዳጌጡ መኖር አልተገኘምና።*
*/ውብነሽ ታከለ ካሴት ቁጥር7/*

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ በታች ጫማ በላይ ጥላ የሚሆን የህይወት ዋስትና የላትም። ያለችበት ማህበረሰብም ሆነ የኢኮኖሚው ደረጃ እንድታጌጥ ዕድል አይሰጡም። ከዚህ ይልቅ በስቃይና በመከራ የመረረ ኑሮ ትጋፈጥ ዘንድ ግድ ብሏታል። የአካባቢውን ስቃይም ሆነ መከራ ለማስለመድና መስሎ ለመኖር ትታትራለች።

‹‹ጉንዳን ሳይመጣ አመድ ነስንስ›› እንደተባለው ሴቶች በማጌጥና በድሎት ይኖሩ ዘንድ አይቻላቸውም፡፡ ስለሆነም ነገሮች ከተከሰቱ በኋላ ከመቸገር ቀድሞ ነገሮች እንደሚከሰቱ ገምቶና አውቆ መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ቃል ግጥሙ እንደተገኘ አይበላም፣ እንደተቀዳ አይጠጣም፣ እንደተገዛ አይለበስም በማግኘት ማጣት፣ በመሳቅ ማልቀስ የህይወት ጉዞዎች እንደሆነ የሚያጸና አንድምታ አለው፡፡ ከዚህ በመነሳት ውብነሽ ትናንትን በድሎት ዛሬን በምሬት የምትኖር ልጃገረድ እንደሆነች በምታዜመው ቃልግጥም ገልጻለች፡፡

*69. ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ ጨርቄ ወጣ*
*ከእንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ፡፡*
*/አስረበብ አለቤ ካሴት ቁጥር 6/*

*የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ አስረበብ አለቤ ቤተሰቦቿ ‹‹በአጥንት›› ከሚመስላቸው በሀብት* ከሚወዳደራቸው ሰው ጋር ከመዳራቸው በፊት ስድስት ሙክት ያህል ‹‹ግጥግጥ›› በሚል ስም እየታረደ ተበልቷል፡፡ ጠጅ ተጥሏል፡፡ ጮማ ተቆርጧል፡፡ ይሁን እንጂ ግለሰቧ ስለ ሁኔታው ብዙም የምታስታውሰው ነገር አልነበረም፡፡ (አስረበብ አለቤ ሰኞ 20/08, 5/2005 ዓ.ም)



ፎቶግራፍ 9 ወ/ሮ አስረበብ አለቤ

(በ20/05/05 ግብጻዊት ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

በዕድሜ ለአቅመ አዳም የደረሰው የግለሰቧ ባል ደግሞ ልጅቱ ለአቅመ ሄዋን ባለመድረሷ የነተሳ ‹‹የጭንገረድ›› አግብቶ ሶስት ልጆች ወልዷል፡፡ በዚህ ድርጊት የተቀየሙት አባቷ አቶ አለቤ ጥሩነህ ልጅቱን አፋተው ለሚመስላቸው ባለሀብት ከአንድም አራት ጊዜ ድረዋታል፡፡ ስለሆነም የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ሴት ይህን ታሪኳን ለመግለጽ ‹‹ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ ጨርቄ ወጣ›› የሚለውን ቃል ግጥም ከአለፈችበት ህይወት ጋር አጣቅሳ እንጕራጕራለች፡፡

ቀድሞ የነበራት መልክ በጊዜ ኡደትና በማህበሩ የትዳር በትር ትብብር ጠውልጓል፡፡ ፈርጀ ብዙ በሆኑ የሴት ልጅ ጫናዎች ምክንያት አካሏ ረግፏል፡፡ ‹‹ከእንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ›› የሚለው ስንኝ በእርግጥ አባቷ አቶ አለቤ ጥሩነህ ሀብታም የሚባሉ እና በ3 ጥንድ የሚያሳርሱ የአካባቢው ታዋቂ ሰው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ልጃቸውን ወግ ማዕረግ ለማየት በሚል እሳቤ ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች ሲድሯት ኑረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በግለሰቧ ዘንድ የማታውቀውና ያልፈቀደችው የጋብቻ ድርጊት በመሆኑ ከሽያጭ ቆጥራዋለች፡፡ ያለ ፈቃድ የሚደረግ ጋብቻ ከሽያጭ ጋር ይፈካከራል፡፡ ያለ እሷ ይሁንታና እውቅና ትዳር ሲከናወን መኖሩ በግለሰቧ ዘንድ ባዕድ ነው፡፡ ተቀባይነት የለውም፡፡ ‹‹ቢሸጡኝ›› የሚለው ቃል ሰብእናዋን የፈተነ ራሷን እንደ ቁስ አካል የፈረጀ የጋብቻ ተግባር እንደነበር ለማዝከር የቆመ ቃልነው፡፡የምሬቷ ደረጃ ጣራ የነካ መሆኑን ለመግለጽ ራሷን ከግዑዝ አካልና ከእንስሳ ጋር ትመድባለች፡፡ በዚህ ምድቧ በቤተሰቦቿ መልካም ፈቃድ የምትሸጥና የምትለወጥ እንደነበር ታስረግጣለች፡፡ በዚህ የከፋ የሽያጭና መልስ ተግባር ለጋ ጊዜዋ በከንቱ የባከነ መሆኑን በምሬት ትገልጻለች፡፡ በቤተሰቦቿ አመለካከት ወግ ማዕረግ የተባለው ትዳር በእሷ ዘንድ ግን ከዚህ በኋላ እንዳገለገለ ዕቃ፣ እንዳረሰ በሬ ዋጋ የማታወጣ ቁስ ይሁን እንስሳ እንዳደረጋት ነው ምሬቷ የሚያመለክተው፡፡

*85.እሄዳለሁ እንጂ ምን አለ መሄዴ*
*ክፉና በጐውን እያወቀ ሆዴ*
*የኔ እናት አባቶይ የገደል ምሳና*
*እኔ ነኝ ልጅቱ እድሌ የጠና*
*የኔ ባልንጀሮይ እንደኔ ያልሆኑ*
*አጅባር ተማሪ ቤት ደብረታቦር ያሉ፡፡*
*⁄እርጎየ ለገሰ ካሴት ቁጥር 10⁄*

ይህ ግጥም ማክሰኞ 14/05/2005 ዓ.ም ከእርጎዬ ለገሰ መና መድኀኔአለም ቀበሌ የተገኘ ነው፡፡ እርጎዬ ሌሊት በ8፡00 ስለፈጨች የወይራ ፍልጥ እሳት ተያይዞ ዙሪያውን ከበው እየሞቁ ባሏ አይተን፣ አባቷ አቶ ለገሰና እበይ ጠጋ አብረውኝ ነበሩ፡፡ ለእኔ ደግሞ ዙሪያውን ታጥፎ የተሰፋ ፎጣ ደረቡልኝ፡፡ አባቷ አቶ ለገሰ ‹‹አይዞሽ ልጀ ወይ አዲስ አበባ ትሄጅ ይሆናል ማን ያውቃል›› እያሉ እንድታዜም አደፋፍረዋታል፡፡ እርጎዬ የመጀመሪያ ባሏ ከመሞቱ በፊት እስከ 3ኛ ክፍል ተምራለች፡፡በኋላ ግን ትምህርቷን አቋርጣለች፡፡አጭተኛ መቆሚያ መቀመጫ በማሳጣቱ ለ2ኛ እና 3ኛ ባል ተድራለች፡፡ ከእሷ ጋር ትምህርት ጀምራ የነበረችው ትንሽ እህቷ ወርቅዬ ለገሰ አጎታቸው ወስዷት ደብረ ታቦር ተምራ አሁን የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ሆና በእነርሱ ቀበሌ ትገኛለች፡፡ ‹‹እሷ በመማሯ ከዚህ ደረጃ ደረሰች እኔ ልጅ አሳዳጊና ወፍጮ ፈጪ ሆኜ ቀረሁ›› (እርጎዬ 14/05/2005 ዓ.ም) ብላኛለች፡፡



ፎቶግራፍ 10 ወ/ሮ እርጎዬ ለገሰ

(በ14/05/05 መና መድኀኔ አለም ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ እርጎዬ ኑሮ መሯታል። ህይወት አስቃይቷታል። ስለሆነም አካባቢውን ለቃ አገሯ ለመሄድ ወስናለች። አካባቢው ለመኖር አላስቻላትም። ግለሰቧ ነገሮች ይስተካከላሉ፣ ወራቶች ያልፋሉ፣ ብላ ኑሮን በአካባቢዋ ለመጋፈጥ ጥረት ስታደርግ ኖራለች። ይሁን እንጂ ጥረቷ አልተሳካላትም። ከዚህ ይልቅ በኑሮ ሂደት በጊዜ አዙሪት ክፉና በጉውን አውቃለች።ኑሮዋ ከበጉ ጉኑ ክፉው፣ ከጥቅሙ ጉዳቱ እያመዘነባት ስለመጣ ለውሳኔ ተዘጋጅታለች። ለዚህ መራራ ህይወት ማምለጫ ብላ የወሰደችው ደግሞ አካባቢን ለቆ መሔድ ነው። ‹‹የእኔ ባልንጀሮች እንደኔ ያልሆኑ አጅባር ተማሪ ቤት ደብረ ታቦር አሉ››። በሚለው ስንኝ እርጎዬ ወላጆቿን በመውቀስ ምሬቷን ትጀምራለች። አብረዋት አፈር ፈጭተው ውሃ ተራጭተው ከአደጉ ሴት ጓደኞቿ መካከል ከትዳር ቀንበር አምልጠው የተማሩትን እንደ መታደል ትቆጥራለች። የእሷን የዕድለ ሰባራነት ለስቃይ ለመከራ እንደተፈጠረች በመቁጠር ምሬቷን በወፍጮ ስራዋ ላይ ትገልጻለች።

በእርግጥ በዚህ ቀበሌ አካባቢ አልፋ ደብረታቦር ገብታ የምትማር ልጃገረድ ማግኘት (ከንፍሮ ቅቅል ደረቅ ባቄላ) እንደማግኘት ይከብዳል። የአቀንቃኟ ጓደኞች ግን በተለየ መንገድ ደብረታቦር ተምረው የተለወጡ እንዳሉ ትገልጻለች። ከዚህ ማህበረሰብ የሴቶች ጫና የመጨረሻና መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ትምህርት ብቻ በመሆኑ በትምህርት በመቅናትና በዚህ መንገድ በመሄድ ለቀጣዩ መጭ ልጃገረዶች ማምለጫ መንገድ በመጠቀም ብሶቷን ገልፃለች።

*74.እንዲህ ወደ ማታ ደም እየነሰረኝ*
*ቀድሞ ባልወለድ ነበር የሚሻለኝ።*
*/ውብነሽ ታከለ ካሴት ቁጥር8/*


ሴት ልጅ በዚህ ወረዳና ቀበሌ ከጧት እስከ ማታ የቤቱን ስራ ለማሟላት ስተባዝን ትውላለች። ጉጆ አስር አይሞላም እንደተባለው አስር ሊሞላላት አልቻለም። ኑሮው አንገሽግሿታል። በዚህ ላይ ጤናዋ ታውኳል። ስታዝን ውላ ጉኗን በእንቅልፍ ለማሳረፍ በምትጥርበት ሰዓት ይነስራታል። ‹‹እንዲህ ወደ ማታ ደም እየነሰረኝ›› የሚለው ስንኝ ‹‹ነስር›› የሚለው ቃል ነስር ደምነው፣ ደም ደግሞ መስዋዕትነት ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ወደ ማታ ነው። ማታ መሆኑ ውብነሽ ሙሉ ህይወቷን መስዋት መክፈሏን የሚያዘክር ነው። ስለሆነም ሴት ልጅ በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ መስዋዕትነት እንደምትከፍል ራሷን ለሌሎች አሳልፋ እንደምትሰጥ የሚያስረግጥ ቃልግጥም ነው።

የኑሮዋ ውጣውረድ መስዋዕት መሆን እጅግ ያበሳጫትና ያንገሸገሻት ውብነሽ አለመፈጠሯን ትወዳለች፡፡ ‹‹ቀድሞ ባልወለድ ነበር የሚሻለኝ›› የሚለው ስንኝ ህይወት መራራ ከሆነች፣ ነገሮች ሁሉ ውስብስብ ከሚሆኑ የሚወሰደው ምርጫ አለመወለድ ነው፡፡

ግለሰቧ በዚያ ቢሉት ድካም፣በዚህ ቢሉት ጫና በአጠቃላይ ውጥረት፣ ብሎም እስከ መስዋዕት የሚደርስ እና የመረረ ኑሮ ሆኖባታል፡፡ ከዚህ በመነሳት በብዙዎች ህያዋን ዘንድ የሚደነቀውን እና አይጠገቤውን የሰው ልጆች ይሁን የተፈጥሮ አፈጣጠር ጥበብን ትተቻለች፡፡ ስለሆነም ውብነሽ ሰው ወደዚህ አለም የመጣበት ጥበብ ፍሬ ፈርስኪ እንደሆነ በቃልግጥሙ ተፈጥሮን በመሞገትና በመተቸት ጭምር ብሶቷን ገልጻለች፡፡ እንደዚሁም በዚህ ቀበሌ አካባቢ ሴቶች የሀብትና የቤት ባለቤት የመሆን እድል የላቸውም ይህን የሚመለከት ግጥም ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

*118. ዓዜን ክውን ክውን እስካደርግላችሁ*
*ሃብቴን ሽክፍ ሽክፍ እስካደርግላችሁ*
*ለምን ገፋ ገፋ ታደርጉኛላችሁ፡፡*
*/ባንቻለም አየነው ካሴት ቁጥር7/*

ይህ ቃል ግጥም ሐሙስ 16/05/2005 ዓ.ም ከባንቻለም አየነው የተገኘ ነው፡፡ በወቅቱ አባቷ ሙተውባት ስለነበር ትችል የነበረውን የዘፈን ቃናና ለዛ እንዲሁም የግጥም ችሎታ በመቀነስ በለቅሶ አይነት ነው ያዜመችው፡፡ (ባንቻለም አየነው ሐሙስ 17/05/2005 ዓ.ም)



ፎቶ ግራፍ/ 11/ ወ/ሮ ባንቻለም አየነው

(በ16/05/05 መና መድኀኔ አለም ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

በዚህ ማህበረሰብ ባህልና ደንብ መሰረት ሴት ልጅ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ በመልክ ለማታውቀው ወንድ ተድራ ወደማታውቀው አካባቢ በመሄድ ትዳር ትመሰርታለች፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹ለሰው ባዕዳ ለአገሩ እንግዳ›› በመሆን በባይተዋርነት ትኖር ዘንድ ግድ ይላታል፡፡ በዚህ መካከል የትዳር አለመግባባት በሚፈጠረበት ወቅት ባልየው፣ አማቾቿ እና የባል ዘመዶች በአንድ ላይ ያምጹባታል፡፡ መውጫና መግቢያ ያሳጧታል፡፡ የዚህ ቃልግጥም አቀንቃኝ ባንቻለም በዚህ ውጥረት ውስጥ ሆና የተሰማትን ምሬትና ብሶት ለመግለጽ ነው በወፍጮ ስራ ላይ ሆና የምታንጐራጉረው፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ የቤትና የመሬት ባለቤት ባትሆንም በጉልበቷ ያዘመረችውን አዝመራ በእውቀቷ የሰፋችውን ስፌት እና የፈተለችውን ጋቢ እንኳን ትክውን ዘንድ የጊዜ ዕድል አሳጥተዋታል፡፡ ፋታ ነስተዋታል፡፡ በእርግጥ ሁኔታዎች ተስተካክለው፣ ነገሮች ተመልሰው ቤት ትሰራ ዘንድ እንደማትችል ታውቀዋለች፡፡ ይሁን እና ያላትን ተንቀሳቃሽ ንብረት የምታገኝበት ጊዜ ማጣቷ አማሯታል፡፡

## 4.2 ውዳሴን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

ይህ ክፍል የውዳሴ ቃል ግጥሞች የሚተነተኑበት ነው።ግጥሞቹ በአብዛኛውና በተደጋጋሚ እናትን፣እርሻ ማረስን፣አገርንና የአካባቢ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚሞገሱ ናቸው። ቀጥሎም የግጥሞቹ ትንታኔ ይቀርባል።

### 4.2.1. እናትን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች

*134. እናት አለሚቱ የበረሃ ሎሚ*
*እኔ ልሙትልሽ አንቺ አትታመሚ ::*
*(እርጉየ ለገሰ ካሴት ቁጥር 9)*

ከላይ የተጠቀሰው ቃልግጥም እናትን ከበረሃ ሎሚ ጋር ያመሳስላል። ይህ ቃል ግጥም የበረሃ ሎሚን ባህሪ ለእናት መስጠቱ በዋናት የበረሃ ሎሚ ከበቀለበት አካባቢ አንፃር ሲታይ በረሃ በመሆኑ የፀሐይ ጨረር ያቃጥለዋል። ውሃ ከሚያርሰው እና ልምላሜ ከሚያስጌጠው ተፈጥሮ የራቀ ነው። በመሆኑም ምቾት የለውም። እናት በረሃ ከበቀለ ሎሚ ጋር መመሳሰሏ ደግሞ ሙሉ ህይወቷን ይሁን ሙሉ ምቾቷን ለልጅ በመስጠቷ ምክንያት ለራሷ የምታስቀረው ምንም አይነት ድሎት የለም። በዚህ ምክንያት ከበረሃ ሎሚ ጋር ትይዩ ሆና ተገልጻለች። ሌላው ሎሚ በዚህ ማህበረሰብ አካባቢ ለአይነጥላ፣ ለወለሎች፣ ለቋቁቴ፣ ለንኪት ለደረመን እና ለመሳሰሉት ሁሉ መድኃኒት ነው።(እርጎየ ለገሰ 14/052005/) እናትን ከዚህ ለመድኃኒትነት ከሚያገለግለው እጽዋት ጋር መመሰሏ ደግሞ እናት የረሃብ፣ የጥም፣ የእርዛት መድኃኒት ናት ለማለት ነው።እንደዚሁም ‹‹እኔ ልሙትልሽ አንቺ አትታመሚ›› የሚለው ሁለተኛው ስንኝ ቃል ግጥም ደግሞ እናት ብትታመም አንድ ብቻዋን አይደለችም። በማህጸን የተጸነሰ፣ በዳዴ የሚድህ ወይም በእግሩ የሚንደረደር ደመ ነፍስ ህፃን ይኖራል። የእናት ሞት ቀርቶ ህመም ሲታሰብ የበርካታ ህይወት ህመም ወይም ሞት ከተፍ ማለቱ አይቀርም።በሌላ አይን ሲታይ ደግሞ እናት ከታመመች እናት ከሞተች የባለታሪኳ እጣፈንታ የሥቃይ ህይወት ስለሚሆን የራሷን ሞት ትመርጣለች።ቃልግጥሙ የሚያመለክተው ስለ እናት የሚከፈል የፍቅር ሞት ብቻ አይደለም። ይልቁንም ያለ እናት የሚገጥመውን የኑሮ ውጣውረድ በመፍራት ስለራስ እና ስለ ብዙ ሰዎች ህይወት ሲባል የሚወሰድ ምርጫ ነው።


*122. እናት አለም አልኳት ስሟን አሳንሼ*
*ዘጠኝ ወር አርግዛኝ ስጋዋን ለብሼ*
*ሶስት አመት አጥብታኝ ክንፏን ተንተርሼ፡፡*
*(እስረበብ አለቤ ካሴት ቁጥር 5 /ሰኞ 20/05/2005)*

የተጠቀሰው ቃልግጥም ለእናት የተሰጣት ስያሜ ከምታስገኘው መጠነ ሰፊ ጥቅም ጋር ሲነጻጸር ተመጣጣኝ አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡ በእርግጥ እናት ስትባል እንዲሁ በዳሰሳው ወይም በግርድፉ ከሆነ የወለደች እንዲሁም ያሳደገች ተብሎ ሊታለፍ ይችላል፡፡የቃል ግጥሙ አንድምታ ግን ከዚህ ያልፋል፡፡ እናትን ስናስታውስ ወይም ስናስብ ጥልቅ ምርምርን ይጠይቃል፡፡ ‹‹ዘጠኝ ወር አርግዛኝ ስጋዋን ለብሼ›› የሚለውን ስንኝ ብንወስድ የእናት ማህጸን እጅግ እጹብ ድንቅ የሆነ እና የተፈጥሮ ጥበብ የታከለበት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ይህ ማህጸን አሁን ከምንባዝንበት እና ከምንደክምበት አለም በፊት የነበርንበት ቀዳሚ አለም ነው፡፡ በመሆኑም የእናትን ስጋ መልበስ እና ከእናት ጋር የነበረ ውህደት የረቀቀ እና ከእናት በተጨማሪ ተፈጥሮ ጭምር የሚደነቅበት ውብ ስራ ነው፡፡ የእናት አስፈላጊነት በዚህ በስጋ መልበስ ብቻ አያበቃም፡፡ ይልቁንም ዘጠኝ ወር ተጠልለን ከኖርንበት አለም ወደዚህኛው አለም በልደት ድልድይ ስንሸጋገር እናት እንዲሁ በቃህ ከኔ ተለይ አትልም፡፡ የመጭውን አዲስ አለም ሶስት አመት በማጥባት፣ ክፉና በጎውን በማስተማር ከዚህኛው አለም ጋር ተስማምተን እና ተለማምደን የምንኖርበት የማህበራዊና ባህላዊ ህግ በማስተማር የማህበረሰቡ አባል ሆነን እንድንቀሳቀስ በመምህርነት ቀዳሚውን ድርሻ ትወስዳለች፡፡

እነዚህ ተቆጥሮ የማያልቀው ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሊያደርገው የማይቻለው የማርገዝ፣ የመውለድና የማጥባት የእናት ውለታዎች ሁሉ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ተግባራት ናቸው፡፡ እናት ዘጠኝ ወር ስጋዋን ስታለብስና በምጥ ወቅት ከዚያም በማጥባት ወራት ለልጅ የምትታመመውን ሕማማት እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡ ስለዚህ እናት አለም ናት፣ እናት መምህር ናት፣ እናት ዶክተር ናት፤ እናት መጋቢ ናት፤ የእነዚህ ሁሉ ባለሙያ የሆነችው እናት እናትአለም ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ የእናት ተግባርና ባህሪ ላይ በመቆምና በመመርመር ስለ እናት በቂ ግንዛቤ ይሁን እውቀት መጨበጡ ላይ ቃል ግጥሙ ትኩረት ያደርጋል፡፡

*123.የቁርቋራ ማርያም ቀስተ ደመናይቱ*
*በይ እንቺ ቁሚላት ለእናት አለሚቱ::*
*(እናንየ አበባው ካሴት ቁጥር3)*

ይህ ቃል ግጥም ማስከኞ 07 /05/ 2005 የተሰበሰበው የእናንየ አበባው ባለቤት የሆኑት ቄስ ደረጀ አያናው እና አማቷ አቶ አያናው አሰፋ በአሉበት ነው።እናንየ ወላጆቿ ቁርቋራ ማርያም ናቸው።እሷ በልጅነቷ ተድራ ወደ ዱርቃዘባ በመምጣቷ ምክንያት እናቷን ውሃ ቀድታ እንጀራ ጋግራ አላገዘጃትም።‹‹የቁርቋራ ማርያም ትቁምላት እንጅ ውሃ ባሽኮ፣እንጨት ጭባኖይ ነው የሚሰበር። ከዚያ ሁሉ አግኘት አላውቅም።በልጅነቴ ተድሬ ከዚሁ ቀረሁ።››(እናንየ አበባው ማክሰኞ 07/ 05 2005)




ፎቶግራፍ 12/ ‹‹ሀ›› እናንዬ አበባው ‹‹ለ›› ትዕግስት አያናው

(በ07/05/05 አዲያ (ዱርቃዝባ) ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

እናንየ እናቷ ንባሽኮ ከሚባለው ወንዝ ውሃ ቀድታ ጭባኖይ ከሚባለው ተራራ እንጨት ለቅማ ባለማገዟ ቆጭቷታል። በዚህ ምክንያት እናቷ ከጧት እስከ ማታ ስተባክን እና ስትባዝን ትታያታለች። የቤትና የልጆቿን ሃላፊነቶች የመከወን ስራ ጭምር ትሰራለች። ለእናቷ የተደረገላት እንክብካቤ አናሳ ነው። በማህበራዊ ህይወት አደባባይ አትወጣም። ቤተክርስቲያን አትሄድም። ስለሆነም ዘፋኟ የቋርቋራ ማርያም እናቷን በስጋም በነፍስም

እንድትጠብቅላት ትማጸናለች፡፡ ከማርያም ውጭ ለእናቷ ማንም እንደሌላት አድርጋ በመቁጠር መልካሙን ትመኛለች፡፡

*128. ሽሪ እናት ሽሪ እናት እናት አለሚቱ*
*በደረቷ ወተት በእጇ ማር ያላቱ፡*
*(አስረበብ አለቤ ካሴት ቁጥር 6)*

ይህ መረጃ ሰኞ 20/05/ 2005 ከወ/ሮ አስረበብ አለቤ የተገኘ ነው፡፡ ከዚህ ቃል ግጥም የምንረዳው የእናትን ልዩነት ምርጥነት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ወይም አንድ ጀግና ገበሬ ከጓሮው እሸት፣ ከማጀቱ ወተት ይኑረው እንጂ እንደእናት ከደረቱ ላይ ወተት አያፈልቅም፡፡ ስለሆነም እናት የተለየች የተመረጠች እና ‹‹ከመደዬው›› ሰው ይልቅ ልዩ ተሰጥኦ ያላት ናት፡፡

እናት በደረቷ ወተት ከአሳደገች በኋላ ከፍ ሲሉም የእናት እጅ ማር ነው፤ ጣፋጭ ነው፤ እንዲሁ ሲሰጥ አይገምትም፤ ወይም አይገመግምም፡፡ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ስንኞች አንደኛው የእናት በህፃንነት በደረቷ ወተት እያፈለቀች ማሳደጓን የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ ከሌማቱ እንጀራ ከወጭቱ ወጥ አጣቅሳ በምትሰጠው ምግብ የእጇን ማርነት ያዘከራል፡፡

*129. እናት እንዲት ሆና ለሰው አስቸገረይ፣*
*እንደ ቤተ ዘመድ ሰላሳ በሆነይ፡፡*
*(አስረበብ አለቤ ካሴት ቁጥር 6)*

ይህ ቃል ግጥም 20/05/ 2005 ከወ/ሮ አስረበብ አለቤ የተገኘ ነው፡፡ በወቅቱ እናትየው እማሆይ ማናሌ ፍቃዱ ጸበል ለመጠመቅ መጥተው አብረው ነበሩ፡፡ ከዋኟ የአቀነቀነችው ቃል ግጥም የእናት ተግባራት በርካታ በመሆናቸው ብዙ ብትሆንልን የሚል ሃሳብ አለው፡፡ አንዲት እናት እና ሰላሳ ቤተ ዘመድ ሲመዘኑ የእናት ሚዛን ይደፋል፡፡እናት ያልሆኑ ሰላሳ ሰዎች ማድረግ የማይችሉት የመጸነስ፣የመውለድና የማጥባት ተግባር በእናት ይተገበራል፡፡‹‹እናት አንዲት ሁና ለሰው አስቸገረይ›› የሚለው ስንኝ ሰዎች እናት አንዲት በመሆኗ ምክንያት እንደሚቸገሩ፣ እንደሚንገላቱ እና ከሚያስጨንቋቸው በርካታ ጉዳዮች ወይም ተፈጥሮዎች መካከል አንዱና ዋናው እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ምክንያት አቀንቃኟ ተፈጥሮን ትሞግታለች፡፡‹‹እንደ ቤተ ዘመድ ሰላሳ በሆነይ›› የሚለው ስንኝም እናት በዚህ አለም

ላይ ብትበዛ ወይም ምትክ ቢኖራት ኖሮ የሰው ልጆች ችግር አሁን ካለበት ሊቀንስ ይችል እንደ ነበር ይጠቁማል፡፡

በጥቅሉ ከላይ ስለ እናት የተገጠሙትን ቃልግጥሞች ስንመለከታቸው፣ተደጋጋፊና ተመሳሳይ አንድምታ አላቸው፡፡ እነሱም ለእናት የሚሰጠው ትኩረት እናት ከምትሰጠው ተግባር ጋር ሲነፃፀር ፍጹም ሊገናኝ የማይችል መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ እናት ህይወት ትስጥ እንጂ ለህይወቷ ብዙም ቦታ የሌላት መሆኗን ከዚህ ይልቅ ለእናት ፈጣሪ ይሁናት ማርያም ትቁምላት እንደሚባል ቃልግጥሞቹ ያስገነዝባሉ፡፡ቃልግጥሞቹ አንድም ባል፣ ልጅ እንዲሁም የአካባቢ ማህበረሰብ ለሴቶች በተለይም ለእናቶች ትኩረት መስጠት እና ማክበር እንደሚገባ የሚያሳስቡ ናቸው፡፡ቃልግጥሞቹ ለማህበረሰብና ለመንግስታዊ አካላት የሚጠቁሙት ስለ አላቸው ፋይዳቸው ከፍ ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ መጠነ ሰፊ ተግባራት ወይም ፋይዳ አላቸው፡፡

## 4.2.2. እርሻ ማረስን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች

*161. ያረሰማ ጉበዝ እርፍ የነቀነቀ*
*ወፍጮው እንዳጉራ መስከረም ዘለቀ*
*ያላረሰ ጉበዝ እርፍ ያልነቀነቀ*
*ወፍጮው የሐምሌ አቦ ተነቅሎ ወደቀ፡፡*
*/ዘመናይ አያናው/ 15-05-2005 ማስታወሻ/*



ፎቶግራፍ 13 ዘመናይ አያናው

( በ15/05/05 መና ዲቅ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

የእብናት ወረዳ ማህበረሰብ 93.5% የሚሆነው ህብረተሰብ የሚተዳደረው በእርሻ መሆኑ ተገልፃል፡፡ዋናው የገቢ ምንጩም እርሻ ነው፡፡ ስለሆነም በእርሻው ላይ አርሶ አደሮቹ ጉልበት ያገኙ ዘንድ ሴቶቻቸው እያዜሙ ያወዳድሯቸዋል፡፡ ከላይ ያቀነቀነችው ሴት በቃል ግጥሙ አማካኝነት በእርሻ ስራ ላይ ጠንካራ ገበሬን እና ዋዘኛ አርሶ አደርን አነፃፅራለች፡፡

የአረስና የአፈስ ጀግና የተያዘው አመት አልፎ ያኛው አዲስ አመት መስከረም እስኪተካ ችግር አይነካውም፡፡ የአካባቢው መኩሪያና መመኪያ በመሆን በሐምሌና ነሐሴ ወራት ውሃው ሲሞላ ያለፈው በአለቀበት፣ ቀጣዩ ባልደረሰበት ጉተራውን ከፍቶ ያበድራል፡፡ ዘር ላጡ ዘር፣ ቀለብ ላጡ ቀለብ ይሰፍራል፡፡ ‹‹ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ›› የሚለው ስንኝ ለዚህ ሀብታም የመሆን ዕድል ያበቃው የበሬው ስኮና እስኪ ቀረና በማረስ፣ እሾህና ጫካ በመጨበጥ፣ በመድፈርና በመመንጠር እንጂ እንዲሁ በዕድል ወይም በአጋጣሚ አለመሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ በአንጻሩ እጁ እርፍ ያልደፈረ፣ ገላው ጸሐይና ውርጭ ያልተቋቋመ ገበሬ ደግሞ ወፍጮው እህል ባለመኖሩ አይፈጭበትም፡፡ ከቤቱ ሊጥ አይቦካም፣ እንጀራ አይጋገርም፤ ለልጆቹ እንጀራ አይቆረስም፡፡ በብድርም ሆነ በሽመታ የመጣችውን ባቄላ እየተካፈሉ ይቆረጥማሉ፡፡ ሰነፉ ግለሰብ እርሻ አለመደፈሩ እና የእርሻ ጦርነት መፍራቱ ቤተሰቦቹን በረሃብ ጀራፍ እንዲገረፉ አድርጓቸዋል፡፡

*156.አራሽ እንዳፍራሽ በሰፊ ድግር*
*ስራው አለም ታየ የይርጋለም አባት የነጠሯ ባል*
*ንጉስ አሳዳሪ*
*አይላትም ሚስቱን በቁጥብ እደሪ፡፡*
*/ነጠሩ አሳዜ/ ካሴት ቁጥር 2*

ይህ ግጥም ከወ/ሮ ነጠሩ አሳዜ ቀን ሀሙስ 09/05/2005 አዲያ ቀበሌ ጭንጫ ጎጥ የተገኘ ነው፡፡በወቅቱ ወ/ሮ ነጠሩ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም ይሁን እንጅ አብረውኝ የሄዱትን አዛውንት አቶ ሞላ ዘገየን በማክበር ‹‹ታቦት እኮነው ይዞብኝ የመጣ›› በማለት መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ (ወ/ሮ ነጠሩ /09/05/2005)



ፎቶግራፍ 14 ወ/ሮ ነጠሩ አሳዜ

( በ07/05/05 አዲያ( ጭንጫ) ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

ወ/ሮ ነጠሩ ማሞገስና ማድነቅ የፈለጉት የባለቤታቸውን የአቶ ሥራው ታየን እርሻ አስተራረስ ነው። እኒህ ጎበዝ ገበሬ ንጉስ ያሳድራሉ። ንጉሥ ሲባል ከወረዳው ለተለያዩ ሥራዎች ተልከው የሚመጡ የመንግስት ሰራተኞች በአካባቢ ከተማ ባለመኖሩ በሀብት የተሻለ አቅም ወዳላቸው ሰዎች የቀበሌው አስተዳዳሪ ይልካቸዋል። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አቶ ስራው ታዬ አንዱ ናቸው። እንደዚሁም ግለሰቡ ከሚጠቀሱባቸው ባህሪያት መካከል ባለቤታቸውን በቁጥብ እደሪ አይሏቸውም። በዚህም የጠገበው ይሄዳል፣ የራበው ይመጣል ይበላል። ለጋስ ናቸው።።

ስለሆነም ለእነዚህ ንጉስ ለማሳደርና ለሚስታቸው ኩራት የመሆንን ማንነት ያለበሳቸው ደግሞ ጉበዝ አርሶ አደር በመሆናቸው ነው። በሰፊ ድግር ጠንክረው በማረሳቸው ምርታቸው ተትረፍርፏል። ምርታቸው በመብዛቱ ሀብታም ገበሬ ከበርቴ ሆነዋል። ሀብታም በመሆናቸው ምክንያት እንግዳ በማስተናገድና ለስጋ ለመሆን በቅተዋል። ስለሆነም ቃል ግጥሙ ሰው ስለሚሆነው ነገር ወሳኝ ራሱ እንደ ሆነ የሚያሳስብ

ነው፡፡ሰው የሚፈልገውን ለመሆን ውሳኔው በእጁ መሆኑን በማጠየቅ ሰው የስራው ባለቤት እና በስራው ልክ ውጤትን፣ ሀብትንና ክብርን እንደሚያገኝ የሚያዘክር ቃል ግጥም ነው፡፡

*146. ሲያርሱ አትረስና ሲዘሩ አትዝራና*
*ሰው ውሎብኝ ነው በል ከጥሳው ዋልና፡፡*
*/አስረበብ አለቤ/ ካሴት ቁጥር 7/*

ይህ ቃል ግጥም በ20/05/2005 ዓ.ም የተገኘ ሲሆን ወ/ሮ አስረበብ በዶሮ ጨኸት ጀምረው ለዓመት በዓል የሚሆን በግምት 25 ኪሎ ግራም የጠላ አሻሮና ከነጋ በኋላ ደግሞ ስንዴ እየፈጩ ነበር፡፡ ሌሊት በመሆኑ ምክንያት ባለቤታቸው አቶ ለገሰ አለሙና እናታቸው እማወይ ማንአሌ ፈቃዱ አብረውኝ ነበሩ፡፡

በዚህ አካባቢ የእርሻ ወቅት ካለፈ ወይም ከተዛባ በቀጥታ ለችግር እንደሚጋለጥ ይታወቃል፡፡ በዚህ ምክንያት በበጋ ወራት፣ በበልግ ወራትና በክረምት ወራት ገበሬው ጠንክሮ ማረስና ነቅቶ መጠበቅ አለበት፡፡ በአንጻሩ የበጋ ሐሩር የክረምት ዝናብ በመፍራት ከዛፍ ጥላ ሥር እየዋለ ቤቱ የሚገባ ከሆነ እጅና እግሩን ድህነት /ችጋር/ አስሮ እንደሚወስደው ጥርጥር የለውም፡፡

የዚህ ዓይነቱ ሰነፍ ገበሬ ለስንፍናው መላ ለሆዱ ሽንገላ ለመፍጠርና ከማህበረሰቡ ሰነፍ የሚል ትችት እንዳይገጥመው በመተትና በጥንቆላ እንደደኸየ በመጠቆም ለማምለጥ ይሞክራል፡፡ ይሁን እንጂ ብቸኛው ፈውስና መድኃኒት ማረስ እንጂ መላ መደርደሩ ተቀባይነት እንደማይኖረው ቃል ግጥሙ ያመለክታል፡፡

*152. ኧረ እረሱ እረሱ ኧረ ስሩ በጣም*
*ሥራ የሰራ ሰው ዋጋውን አያጣም፡፡*
*/አስረበብ አለቤ/ካሴት ቁጥር 3/*


በዚህ አካባቢ ሥራ ማለት እርሻ ነው፡፡ እርሻ ያረሰ ሰው ኑሮውን በተረጋጋ ሁኔታ ይመራ ዘንድ ይቻለዋል፡፡ ይሁን እንጂ እንደተሰራ በስራው ልክ ሁልጊዜ ሙሉ ሁልጊዜ ምርት ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህ አይነት ወቅትና አጋጣሚ በመደናገጥ እርፍን መስቀል፣ ምራንን መጠቅለል፣ እጅና እግርን አጣጥፎ መቀመጥ ተገቢ አይደለም፡፡ ‹‹ሥራ የሰራ ሰው ዋጋውን አያጣም›› የሚለው ስንኝ ከሌሎች አልባሌ ቦታዎች

ከመዋል ይልቅ በሥራ መጠመድንና ሰርቶ መብላትን የሚጠቁም ነው፡፡ ግጥሙ እንደ እብናት አካባቢ ማህበረሰብ የገቢ ምንጭ እኳያ ከማረስ የተሻለ አማራጭም ይሁን አትራፊ ነገር የለም የሚል አንድምታ አለው፡፡

*163. ገበሬው አራሽ ምሳውን ይበላል ፈትፍቶ በእብሽ*
*ከደጃፍ ቁሜ ሁለት አይኔን ባሽ*
*እያለ ሰደደኝ እንደኔ በአረሰሽ፡፡*
*/እስካል ቀለሙ/06/06-2005 ማስታወሻ/*

ይህ ቃል ግጥም ሰኞ 06/5/2005 ወ/ሮ እስካል ቀለሙ አጃ ቀበሌ ጥቁር ውሃ ጎጥ ያቀነቀኑት ነው፡፡ ግጥሙን የአዜሙት ሰነፍ ገበሬ የሚደርስበትን ንቀትና ውርደት እያሰቡ ነው፡፡ ጀግናው ገበሬ በማረሱና በማፈሱ ምክንያት እሸቱ ከንሮ፣ ወተቱ ከማጀት የተትረፈረፈ በመሆኑ እጅ በሚያስቀረጥም ወጥ ፈትፍቶ ምሳውን ይበላል፡፡

ይሁን እንጂ በበጋ ፀሐዩ ያቃጥለኛል፣ በክረምት ዝናቡ ይመታኛል ሲል የኖረ ሰነፍ ሰው በድንገት ከደጃፍ በመቆም ያጎርሰው ዘንድ ሁለት አይኑን ቢያሽ ከጀግናው ገበሬ ስጦታ አያገኝም፡፡ ‹‹እያለ ሰደደኝ እንደኔ ባረሰሽ›› የሚለው ስንኝ ያማረ እንጀራ በአማረ ወጥ ለመብላት መለመን ይሁን ቆሞ ማልቀስ እንደማያዋጣና ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ጠንክሮ ሳይሰለቹና ሳይታክቱ ማረስ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ቃልግጥሙ የሰራ ይበላል ያልሰራ አይበላም በሚል ሰው የስራው ውጤት እንደሆነና የአካባቢው ሰዎች ጠንክረው መስራት እንደሚገባቸው አጽንኦት ይሰጣል፡፡



ፎቶግራፍ 15 እስካል ቀለሙ·

( በ06/05/05 እኛ (ጥቁር ውሃ) ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

## 4.2.3. አገርን የሚያወድሱ ቃልግጥሞች

*178. አዲያ አቦ ከሜዳው ሰው የለም ያሉቱ*
*ልይ ሞላ ዘገዬ ሳለ ነጋሪቱ*
*የተባረከ ነው አዲያ አቦ መሬቱ*
*ሞላልኝ ዘገዬ የበቀለበቱ።*
*/ታከለይ መኩንን/ ካሴት ቁጥር5/*

ይህ ቃል ግጥም ወ/ሮ ታከለይ መኮንን በቀን ረቡዕ 08/05/2005 ዓ.ም ያቀነቀኑት ነው። ታከለይ የአቶ ሞላ ዘገየ ባለቤት ናቸው። በቀረጻው ወቅት አቶ ሞላ ዘገየ ሆነልኝ ደጀኔና ወንድም አገኝ ሞላ አብረውኝ ነበሩ። አቶ ሞላ በደርግ ጊዜ ቆስለው በደረሰባቸው ጉዳት የሚንቀሳቀሱት በበትር ነው። ይሁን እንጂ አራት ወንድ ልጆች ስለሚያርሱላቸው ቤታቸው ሙሉ መሆኑን ገልፀውልኛል። ሙሉ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት የተጣላ በማስታረቅ የታመመ በመጠየቅ ነው። ‹‹ማልዳ እንደወጡ እንዱ ተጣላ ሲባል ሽምግልና ስለሚውሉ እራት እንጂ ምሳ በልተው አያውቁም›› (ታከለይ መኮንን 08/05/2005 ዓ.ም) ወፍጮውን ትፈጭ የነበር ቀን ዕረፋድ ላይ ነው። በዚህ ሰዓት አቶ ሞላ ዘገየ ‹‹ በይ ዝፈኝ አንቺና ይህ አውራ ዶሮ የሌሊት ምኝታ ነስታችሁኝ ታድራላችሁ›› (አቶ ሞላ ዘገየ 08/05/2005 ዓ.ም) አሁን ወግ ደርሶሻል በማለት እኛንም ፈገግ አድርገውናል። ወ/ሮ ታከለይም ስቀው ቆይ አሞግስአለሁ

እስድብህማለሁ በማለት ወደወፍጮው ገቡ ‹‹አዎ ሴቶች እንደፈንዝ አድርገው ባሎቻቸውን ይሳደባሉ›› (አቶ ሞላ ዘገየ ካሴት ቁጥር 1)



ፍቶግራፍ 16 ወ/ሮ ታከለይ መኮንን የሚፈጩበት እጃቸውን እያሳዩ

(በ08/05/05 አዲያ አቦ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

ይህ ቃል ግጥም ሰው በቦታ ቦታ በሰው ሊከብር እንደሚችል የሚያዘክር ነው፡፡ ሞላ ዘገዬ የተባሉት ግለሰብ የአካባቢው ተወላጅና በአካባቢ ሰዎች ዘንድ ትልቅ ተሰሚነት ያላቸው ናቸው፡፡አዲያ አቦ የተባለው ቀበሌ የተጣላ በማስታረቅ፣ የተቸገረ በመርዳት የሚታወቁትን ግለሰብ አስገኝቷል፡፡ ግለሰቡ ባላቸው ተደማጭነት የአገር ቀንድ በመሆናቸው ምክንያት አንደበታቸው የሚጣፍጥ፣ የወሰኑት የሚጸና፣ የመረቁት የሚሰምር በመሆኑ በነጋሪት ተመስለዋል፡፡ ‹‹ነጋሪት›› በቀድሞ ነገስታት ቤተ መንግስት ውስጥ የአዋጅ መንገሪያ ነበር፡፡ በወቅቱ ነጋሪት ሲመታ ሰው ጸጥ ብሎ ያደምጣል፡፡ የሚመጣውን ነገር ለመስማት ይጠባበቃል፡፡ እኒህ ተጠቃሽ ሰውዬ ባላቸው ተሰሚነትና ተደማጭነት ከነጋሪት ጋር ትይዩ ሆነው ተገልጸዋል፡፡

ይህን መሰል ሰው ያስገኘውን አካባቢ ልዩ ቡራኬ ያለው ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ ስውዬው በቦታው በቅለዋል፡፡ ባበቀላቸው ሰውዬ ደግሞ ተመልሶ ቦታው ተባርኳል፡፡ ስለሆነም

ቃልግጥሙ ሰው ከቦታ ቦታ በሰው ሊከብርና ሊባረክ የሚችል መሆኑን ያጸናል፡፡ አገር እና ሰው በአንድ ማእቀፍ ሊተነተኑ የሚችሉበት እና አንደኛው በሌላኛው ላይ ሀልው የሚሆንበት አጋጣሚም ብዙ ነው፡፡

*179. ምነው ባደረገኝ የመኔ ወለደ*
*እንገታቸው መልካም ጥርሳቸው በረደ፡፡*
*/እናት ንጋቱ/ ካሴት ቁጥር5/*



ፎቶግራፍ 17 ወ/ሮ እናት ንጋቱ

(በ17/05/05 አጊሳ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

ግጥሙ አርብ 17/05/2005 ዓ.ም በእናት ንጋቱ የተቀነቀነ ነው፡፡ መና ማለት ጥናቱ ከተካሄደባቸው ቀበሌዎች አንዱ ነው፡፡ አቀንቃኟ እንደነገረችኝ የመና ተወላጆች ላም አርቢ በመሆናቸውና ቅቤና ወተት ስለማይለያቸው ሁልጊዜ ያማሩ ናቸው፡፡(እናት 17/05/2005 ዓ.ም) እናት እንደገለፀችው መልከኛ፣ አንገተ መቃ እና ጥርሰ በረዶ የመኔዎች መለያ ነው፡፡ ይህን ማንነት ሌሎቹ ቡድኖችም አምነው ተቀብለውታል፡፡ ለዚህ ማስረጃው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ የሌላ አካባቢ ተወላጅና ነዋሪ መሆኗ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመኔዎችን መልከ መልካምነት ትናፍቃለች አምና ተቀብላለች፡፡ መኔዎች አይነቶሎ እና ጥርሰ በረዶዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ዘር ወይ ተወላጅ ብትሆን ኖሮ እራሷም እንደነርሱ በመልኳ ውብነት በአንገቷ መቃነት፣ በጥርሷ በረዶነት፣ በአይኗ

የባቄላ አበባነት ትወደድ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ግለሰቧን የሚያረካትና የሚያስደስታት ውበት ነው፡፡

እናት ንጋቱን ከህብት ሁሉ ለውበት ትልቁን ድርሻ ሰጥታለች፡፡ ይህ ሙሉ ውበት ደግሞ ሊገኝ የሚችል የመኔ ተወላጅ በመሆን እንደሆነ ታምናለች፡፡ መና መድኃኒያለምን ወይ ተወልጄብሽ ወይ ወልጄብሽ በሚለው መልኩ ከዚህ አካባቢ የተወለደ ልጅ ብታገባ እሷ ያጣችውን የምትናፍቀውን ውበት ለልጇ በመስጠት በልጇ ላይ የውበት ጥማቷን ለማርካት እና እረፍት ለማግኘት ትጥራለች፡፡ ከዚህ በመነሳት የመኔ ተወላጅ እንድታገባና እንድትዋለድ ፈጣሪዋን ትማጸናለች፡፡

*183. በአፋፉ ሲዘልቁ ይታያል ዋርካው*
*ኧረ አገሬ ደብር ሳቁ ጨዋታው፡፡*
*/ደብሬ አለሜ/ ካሴት ቁጥር 9/*

ይህ መረጃ ከወ/ሮ ደብሬ አለሜ ሰኞ 27/05/2005 ዓ.ም የተገኘ ነው፡፡ በወቅቱ አባቷ አቶ አለሜ ተገኝና እኔ ነበርን፡፡ አቶ አለሜ ተገኝ ልጃቸው የተጠቀሰውን ቃልግጥም በምታቀነቅንበት ወቅት ‹‹አዎ እውነት ነው ደብር ተክለሃይማኖት አቡነ ተክሌ መጥተው እርሻ አርሰውበታል በመስቀል ባርከውታል ከባድ ጠብና ግድያ ሲሆን እርቅ የሚፈፀም ደብር ነው፡፡ በመቀጣዋ፣ በመልዛ፣ በእብናት ምንኩስና የሚሰጥበት ገዳም ይህ ነው፡፡›› (አቶ አለሜ ተገኝ ሰኞ 27/05/2005 ዓ.ም) ግጥሙ ደብር ተክለሃይማኖት የተባለው ቀበሌ ከሌሎች የሚለይበትን በመጥቀስ ይጀምራል፡፡ ከተራራው ሲወጡ ትልቁ ዋርካ ይታያል፡፡ ይህ ቦታ ደብር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዋርካ የትልቅ ሰው ተምሳሌት ነው፡፡ /ለገሰ አለሙ ካሴት ቁጥር 1/

ስለሆነም ደብር ተክለሃይማኖት ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ሰዎች ‹‹ጥቁር ደም›› ሲቃቡ ከ ‹‹ስዕልና መስቀል›› በተጨማሪ ጥቁሩን ደም የሚያደርቁ ሽማግሌ ሰዎች የሚገኙበት ስፍራ ነው፡፡ እንደዚሁም ደብር ተክለ ሃይማኖት በወረዳው ብቸኛው የምንኩስና ስልጣን የሚሰጥበት ገዳም የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ቦታው በዋርካ ተመስሎ ከሌሎች አካባቢዎች የሚለይ እንደሆነ አቀንቃኟ ደብሬ ገልጻለች፡፡

‹‹ኧረ አገሬ ደብር ሳቁ ጨዋታዉ›› የሚለው ስንኝ ደግሞ ደብር ተክለሃይማኖት የሚባለው ቦታ የሰው ልጆች ህይወት ለቁጥር በሚከብዱ ምክንያቶች ይባዝናል፡፡ በዱር በገደሉ ሲባዝን የዋለው ሥጋ ሌሊት እረፍት ሲያደርግ እንኳን በህልም ያንኑ ስቃይ

ሲደግም ሲያድር ይችላል። ቃልግጥሙ ደብርን ከእነዚህ የህማማት ፈውስ ያስገኛል የሚል ሀሳብ አለው። ‹‹ሳቁ ጨዋታው›› የሚለው ስንኝ ህይወትን ቀለል ባለ መልኩ መምራት የሚቻልበት አገር መሆኑን ያዘክራል። ደብር ሳቅና ጨዋታ ደስተኝነት ያለበት ቦታ ነው በማለት ከሌሎቹ በተለየ መልኩ የሚታወቅበትን የትልልቅ ሰዎች መገኛ፣ የሳቅ፣ ጨዋታና የደስታ መፍለቂያ ቦታ መሆኑን ቃል ግጥሙ ያወድሳል።

*203.የሰው አገር ውሃ ብጠጣው መረረኝ*
*እረ አገሬ ደብር መጣሁ ተቀበለኝ።*
*/ደብሬ አለሜ /ካሴት ቁጥር9/*

ማንም ሰው ከበቀለበት፣ ተወልዶ፣ ቦርቆና ተንደርድሮ ከአደገበት አካባቢ ለቆ ወደ ሌላ ቦታ የመሔድን አስከፊነት የሚጠቁም ግጥም ነው። አቀንቃኟ ከተወለደችበት ደብር አካባቢ ለቃ በሰው ቤት ተቀጥራ በሌላ ቦታ ቆይታ ስተመለስ የቆየችበትን ህይወት ታወግዛለች።(ደብሬ 27/05/2005)

‹‹የሰው አገር ውሀ ብጠጣው መረረኝ›› የሚለው ስንኝ የሰው አገር እርሀብ፣እርዛት፣ ንቀት የሚስተናገዱበት የመረረ የሕይወት ጉዞ መሆኑን የሚጠቁም ነው። የአስከፊነቱ ደረጃ የሚለካው በተፈጥሮው ጣዕምና መልክ የሌለው ውሃ እንኳን የወሃነት ባህሪውን ያጣል። ከውሃነት ወደ ኮሶነት ይቀየራል። በመሆኑም የዚህ የውሃው መምረር በሰው አገር መኖር በቀን ከሶስትና አራት ጊዜ ያላነሰ የምሬት ጽዋ መጠጣት ግድ የሆነበትን የህይወት አጋጣሚ ለማዘከር የቆመ ነው።

ከዚህ በመነሳት አገሬ መጣሁ ተቀበለኝ በማለት ‹‹ዞሮ ዞሮ ከቤት፣ ኖሮ ኖሮ ከሞት›› እንደተባለው ምንም ቢሆን አገሯን የሚተካላት እንዳላገኘች ታዘክራለች። ‹‹እረ አገሬ ደብር መጣሁ ተቀበለኝ›› የሚለው ስንኝ የሰው ወርቅ አያደምቅ እንዲሉ ከዋኟ የሰው አገር ኑሮ ስቃይና መከራ፣ ንቀትና ውርደት ስለአሰለቻት አገሯን ይቅር በለኝ በማለት ለመመለስ መወሰኗን ይጠቁማል።

## 4.2.4. የአካባቢ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች

*258. በሪሁን እንደሻው ዘፈፍ እንደዋርካ ከባድ እንደ ዝሆን*
*ዝቅ ብዬ ላንሳህ እችልህ እንደሆን።*
*/ጣባ እንደሻው / ካሴት ቁጥር 5/*

ይህ ቃል ግጥም ወ/ሮ ካባ እንደሻው የተባለችው ግለሰብ አርብ 17/05/2005 ዓ.ም ከቀኑ 3:00 ሰዓት ላይ ክርክሜ ማሽላ እየፈጨች ያቀነቀነችው ነው፡፡ በወቅቱ ከእኔ ጋር ወንድሞቿ በሪሁን እንደሻውና ጥላሁን እንደሻው አብረውኝ ነበሩ፡፡ ‹‹በሪሁን በድሮ ጊዜ በጦር ሜዳ ብዙ ጀብድ የሰራ ነው አሁን ከዚያ ተመልሶ ጥሩ ቤት ይዞ ዘመድ አዝማድ እንግዳ እየሸኘ ይገኛል፡፡›› (ካባ እንደሻው አርብ 17/05/2005 ዓ.ም)

አቀንቃኟ ካባ እንደሻው ተሞጋሹን ግለሰብ ከእጽዋት ክፍል በዋርካ እና ከእንስሳት ወገን ደግሞ ከዝሆን ጋር በማነጻጸር አክብሮት ትሰጠዋለች፡፡ ዋርካ በአካባቢው ማህበረሰብ የትልቅነት መገለጫ ነው፡፡ ዋርካ የቅጠሉ ልምላሜ፣ በፍሬ ወቅት፣ ወፎቹም ሰዎቹም በልተው የሚጠገቡበት እና ከጸሐይ ሀሩር፣ ከዝናብ ውሽንፍር የሚጠለሉበት ነው፡፡ እንዲሁ ተሞጋሹ ሰው በዋርካ መመሰሉ ደግሞ ከቤቱ ለተራቡት ማብላቱ ለታረዙት ማልበሱ እና ለሰዎች ዋስ ጠበቃ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

እንደዚሁ በዝሆን መመሰሉ ደግሞ ዝሆን ከባድ ነው፣ በመሬት ላይ ካሉ እንስሳት ሁሉ እንደዝሆን ትልቅ የለም፡፡ የትልቅነት መገለጫ ደግሞ ዘር ማበደር፣ ማብላት ማጠጣት እና በግብርናው መታወቅ ነው፡፡ የዚህ ግለሰብ መገለጫም ትልቅ፣ ከባድና ጀግንነትን አጣምሮ የያዘ በረባ ባረባው ሰዎችን የማይተነኩል እና ‹‹የትልቅ ሰው ዘር›› መሆኑን ለማዝከር ግለሰቡ በዝሆን ተመስሏል፡፡ ‹‹ዝቅ ብዬ ላነሳህ እችልህ እንደሆን›› የሚለው ስንኝ የግለሰቡን ልዕልና ክብርና ዝና ከፍ ማድረግን ያመለክታል፡፡ እንደዚሁ በእንግዳ ተቀባይነቱ በመጥመቅና መጋገር የታወቀ አርሶአደር በዚሁ አካባቢ የመወደስ ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡


በእብናት ወረዳ የሚሞገሱት ገበሬዎች በዋርካና በታዋቂ ትልልቅ እንስሳት በመመሰል ነው፡፡ በነዚህ እፅዋትና እንስሳት መመሰላቸው የገበሬዎችን ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑ ለመግለፅ ነው፡፡ ቀጣዩ ወ/ሮ አስረበብ የተባሉት ግለሰብ አቶ ለገሰ አለሙን በዋርካ መስለው አወድሰዋቸዋል፡፡

*227.ለገስዬ አለሙ ዋርካዬ*
*ፍሬውን በልቼ ዛፉ ከለላዬ፡፡*
*/አስረበብ አለቤ/ ካሴት ቁጥር 5/*

ይህ ቃል ግጥም ሰኞ 20/05/2005 ዓ.ም ወ/ሮ አስረበብ አለቤ ያቀነቀኑት ነው። አቶ ለገሰ አለሙ በሚኖሩበት ግብጣዊትና ደብር አካባቢ በምርት የታወቁ ናቸው። ‹‹ዛሬ ዛሬ ቀኑ እየከፋ ነው እንጂ ከለገሰ ቤት አራሚው እራት ይበላል፤ ቅቤ ይቀባሉ፤ አራስ ይጠይቃሉ፤ የታመመ ይጎበኛሉ፤ በያመ ፍልሰታ ጊዜ ድሀውን ፆም ያገድፋሉ፤ በነሀሴ እህል ያበድራሉ ምን አለፋህ ለገሰ የሚሸምቱት ጨው ብቻ ነው።›› (ሰኞ 20/05/2005 ዓ.ም አስረብብ አለቤ፣እቴም አንቺ ሲሳይ)

ቃል ግጥሙን ልጃቸው አስረበብ ሲያቀነቅኑት የሰሙት አቶ አለቤ ጥሩነህ ‹‹ገበሬማ መመስገን አለበት‹‹ አላየሽውም ወይ የጥጡን ተለላ፣ የከብቱን ተለላ፣ የማሩን ተለላ፣ እንደቢ.ራቢ.ሮ ባውንዱ ሲፈላ›› በማለት ለልጃቸው ምላሽ ሰጥተዋል። (አቶ አለቤ ጥሩነህ እና ዋናው ደማም ማክሰኞ 20/05/2005 ዓ.ም/ የቡድን ውይይት/ ካሴት ቁጥር 1) ለገሰ አለሙ የተባሉትን የአካባቢ ሀብታምና ታዋቂ ሰው በግብርናቸው ታዋቂነት በዋርካ ተመስለው ይሞግሳሉ። ስለሆነም የዚ.ህ አካባቢ ማህበረሰብ እርሶ ጥጋብ፣ ድሃ የሚረዳ እና እንግዳ የሚሸኝ ከሆነ በዋርካ ተመስሎ ይወደሳል። ሰዎችም ከዋርካ ጋር አመሳስለው ይጠሩታል። /ለገሰ አለሙ ቃለመጠይቅ ካሴት ቁጥር 1/

*216.በጥቋቁር በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል*
*ጥላሁን እንደሻው ክርክሜ አበቀለ ባሀር የሚመስል።*
*/በለጥ ሞላ ካሴት ቁጥር 5/*



ፎቶግራፍ 18 ወ/ሮ በለጥ ሞላ
( በ08/05/05 አዲያ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ በለጥ ሞላ በ08/ 05/2005/ በወፍጮ ላይ ያዘመችው ነው። ጥላሁን እንደሻው የተባለውን ግለሰብ ለማሞገስ የፈለገችው ከግብርና ችሎታው

እና እርሶ ከማፌሱ ጋር በማጣቀስ ነው፡፡ ተሞጋሹ ገበሬ ለእርሻ ልቡ አይሰንፍም፣ ደከመኝ እና ሰለቸኝ አይልም ፡፡ የልፋት ዋጋውን በአበቀለው አዝመራ እና በአመረተው ምርት ተከኗል፡፡ ክርክሜ የሚባለው የማሽላ አይነት የዚህ አካባቢ ዋንኛ እህል ነው፡፡ ተጠቃሹ ገበሬ አዝመራ ከመሰል ጓደኞቹ ላቅ ባለ ሁኔታ አብቅሏል፡፡ የማሽላው አይነት ከባህር ግርማ ሞገስ ጋር ምስል በመከሰት ይፈካከራል፡፡ ይህ አካባቢ ሙገሳን ከሚቸሯቸው ሰዎች መካከል በዋናነት እርሶ የአፌሰ ገበሬ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ‹‹ሁሉም ነገር ያለ ገበሬ አይሰላም›› ብለው ነዋሪዎቹ ያምናሉ፡፡ /ተስፋው ቀለሙ 29-05-2005/ ቪዲዮ ካሜራ/ ስለዚህ ከግብርና ችሎታው ጋር ተያይዞ ግለሰቦች ይወዳደራሉ፡፡ በውድድሩ ብልጫ ያገኘው ገበሬ ይወደሳል፡፡


*230.እየው ከዚያ ማዶ የወጭት ሥባሪ*
*ንጋቱ መኮንን ነጉስ አሳዳሪ*
*ማሳደሩን እማ ሁሉም ያሳድራል*
*ነጋቱ መኮንን ጠጅ ያዘነብላል፡፡*
*/እናት ንጋቱ ካሴት ቁጥር 5/*

የተጠቀሰው ግጥም እናት ንጋቱ አርብ 17/05/2005 ዓ.ም ያቀነቀነችው ነው፡፡ ንጋቱ መኮንን የተባሉት ግለሰብ በቁርቋራ ቀበሌ ባሻየ አቦ ነዋሪ ናቸው፡፡ሰውየው በባሻየ በሃብት ንብረታቸው፣በማርና በእህል ምርት ስመ ጥር ናቸው፡፡(ቄስ ወርቁ ገላየ 17/05/ 2005 ቃለ መጠይቅ)

የዚህ ቃልግጥም አቀንቃኝ እናት አባቷን የምታሞግሳቸው ከአላቸው የእንግዳ አቀባበል ጋር አያይዛ ነው፡፡ ሰውዬው በአካባቢ ባለብዙ ጉተራ፣ ከብትና ፍየል የታወቁ ሲሆኑ፡፡ የመንግስት አካላት ለተለያዩ ሥራዎች እንግዶች ሲመጡ የሚያርፉት ከሳቸው ቤት ነው፡፡ በቤቱ ከሚቀርበው መጠን፣ ከሚታረደው ሙክት፣ ከሚጠጣው ጠላ በተጨማሪ ለየት የሚያደርጋቸው ጠጅ ማዘንበላቸው ነው፡፡ ይህ ችሎታቸው ከአካባቢው ማህበረሰብ እንዲለዩና እንዲወደሱ አድርጓቸዋል፡፡በዚሁ እብናት ወረዳ በአደን ሚታወቁ ሰዎችም የሚሞገሱበት አጋጣሚ አለ፡፡

*242. የድኩላ ሥጋ ሆዴን እያማረው*
*እስኪ ለተኳሹ ለአረጋ ልንገረው፡፡*
*/የሻረግ ታፈሰ 06-05-2005 ማስታወሻ/*

አረጋ አበራ የቁርቋራ ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ነው፡፡በወቅቱ ከኔ ጋር ከወፍጮው ቦታ ሂዷል፡፡ አረጋ የክላሽ ጠመንጃ ያለው ሲሆን አቀንቃኟ የሻረግ የእኅቱ ልጅ ናት፡፡(የሻረግ 06/05/2005)



ፎቶግራፍ 19 ወ/ሮ የሻረግ ታፈስ

(በ06/05/05 አጃ ዘቀልሞቃ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

አንድ ሰው በዚህ አካባቢ ከሚወደስባቸው መንገዶች አንዱ ተኩሶ የሚጥል፣ ጨብጦ የሚያስቀር እና ታግሎ የሚጥል ሲሆን ነው፡፡ ከላይ በስም የተጠቀሰው ግለሰብ እርሶ ባያፍስና ነግዶ ባያተርፍም ተኩሶ የመጣል ተሰጥኦ አለው፡፡ ስለሆነም የድኩላ ሥጋ የአማራት ባለታሪክ ከሰው ‹‹መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት›› እንደተባለው ‹‹አረጋ አበራ›› የተባለውን ግለሰብ መርጣዋለች፡፡ ሽሿን ያገላበጠውን፣ አምሮት ያሰቃየውን ሆዷን የድኩላ ሥጋ ጮማ ብርንዶና እና ጥብሱን የሚያበላት አረጋ ነው፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ የዱር አራዊትን ማደን እና መግደል ክልክል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ አካባቢ ማህበረሰብ ባህል በድምጸ አራዊት፣ በግርማ ሌሊት አድኖና ገድሎ የሚመጣ ግለሰብን አሁንም ድረስ ጉበዝ እያለ ያሞግሳል፡፡ የዱር እንስሳትን ለማደን የሚደረገውን እንቅስቃሴ በዱር በገደል መሮጥና ማምለጠን የሚጠይቅ በመሆኑ እነዚህን አስቸጋሪ ጉዞዎች ተቋቁሞ ግድያ የጠላ ግለሰብ በማህበረሰቡ ዘንድ የመወደስ ዕድል ይገጥመዋል፡፡

## 4.3. ፍቅርን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች እንደማንኛውም ሰው የማፍቀርና የመፈቀር መብት አላቸው፡፡ነገር ግን በፍቅራቸው ላይ ቤተሰብም ሆነ ማህበረሰቡ ጣልቃ የሚገቡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ሴቶቹ ይህንን የፍቅር ጣልቃ ገብነት በቃል ግጥሞቻቸው ሲቃወሙ ይደመጣሉ፡፡ ቀጥሎም የፍቅር ግጥሞች ትንታኔ ይቀርባል፡፡

*323.አበድሽ አበድሽ አሉኝ መቼ ነው ማበዴ*
*ከአምሳ ደብር አገር አንድ ልጅ መውደዴ፡፡*
*/እናት ንጋቱ / ካሴት ቁጥር 3/*

ይህን ቃል ግጥም ያገኘሁት አርብ 17/05/2005 ዓ.ም ከወ/ሮ እናት ንጋቱ ነው፡፡በአብዛኛው በካሴት የቀረጽኳቸው የእናት ንጋቱ ቃል ግጥሞች የፍቅር ብሶትን የሚገልፁ ናቸው፡፡ አባቷ አቶ ንጋቱ መኮንን በአካባቢው ባሻዬ አቦ የታወቁ አርሶ አደር ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ልጅቱ እናት የአቶ ንጋቱን የጎረቤት ልጅ በመውደዷና በማፍቀሯ ምክንያት ግርፋት፣ከቤት መባረርና መንገላታት እንደደረሰባት ከእህቷ ባል ቄስ ወርቁ ገላየ ጋር በወፍጮው እለት አጫውታኛለች፡፡ (እናት ንጋቱ አርብ 17/05/2005)

በበእብናት ወረዳ አንዲት ሴት ልጅ ማፍቀሯና መውደዷ ከታወቀ ‹‹እከሊት እኮ አብዳለች፤ ጨርቋን ጥላ ሄዳለች፤›› የሚል ስም ከነዋሪው ይሠጣታል፡፡የግለሰቧ ወላጆችና ዘመዶችም ቢሆኑ በእሷ ያፍራሉ፡፡ አንገት ይደፋሉ፡፡ ምነው ባልተወለድሽ በማለት ሲቆጧት፣ ሲገርፏት ግፋ ሲልም ከቤት ሊያስወጧት ይችላሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ከላይ የተጠቀሰውን የማህበረሰቡን የቆየ ህግና ልማድ በመሻር፣ በመቃወምና በማሻሻል ጥፋቱ የቱ ላይ ነው? እስኪ ፍረዱኝ ትላለች፡፡ ከአምሳ ደብር አገር አንድ ልጅ መውደድና ማፍቀር ማበዱ የት ላይ ነው?የሚል መሞገቻ ታነሳለች፡፡በእርግጥ በየትኛውም ቤተ እምነት ይሁን ህግ በአደጉበት አገር አንድ ልጅ መውደድና ማፍቀር አያስጠይቅም፡፡ ይሁን እንጂ የአካባቢው ልማድ እስረኛ የሆኑት ሰዎች የዚህ አይነቷን ልጃገረድ ሲያወግዙ፣ ሲረግሙ እና እብድ ብለው ከማህበረሰቡ ሲለዩ ይስተዋላል፡፡

*386. የአንተ እናት አባቶች ሥጋ ነው እርማቸው*
*እንጀት ትበላለህ አንተማ ልጃቸው፡፡*
*/አስረበብ አለቤ/ ካሴት ቁጥር 3/*

አቀንቃኟ ወ/ሮ አስረበብ ቃልግጥሙን የተጠቀመችበት መንገድ ለማምለጥ ወይም ከማህበረሰቡ ትችት ለመዳን ስትል ሁለት ፍቺ /ሰምና ወርቅ/ ፍቺ እንዲኖረው አድርጋ ነው፡፡ ግለሰቧ የፍቅር ህመሟን የልብ ውጋቷን ለመግለጽ ስትል በፍቅር የገደላትን ልጅ የዘር ሀረግ ትመዛለች፡፡ የከብትና የፍየል፣ የበግና የአሳ ወይም ማንኛውንም ሥጋ የተፈቃሪው ወላጆች እንደማይቀምሱ እርማቸው መሆኑን ትገልጻለች፡፡‹‹እንጀት ትበላለህ አንተማ ልጃቸው››የሚለው ስንኝ እንድምታ ደግሞ አቀንቃኟ ልጃገረድ በተጠቀሰው ልጅ ፍቅር ልቧ መቅለጡን እና የምር ፍቅር የያዛት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ የግለሰቡን የፍቅር ደረጃ ‹‹ከአንገት ነው ከአንጀት›› እንደ ተባለው ከግለሰቧ አንጀት ውስጥ ዘልቆ ገብቷል፡፡ አንጀቷ በእሱ የመጣውን ብቻ ይቀበላል፡፡ ለግለሰቡ አድሯል፡፡ ስለሆነም ግጥሙ የልጁ ፍቅር ሥር የሰደደ እና አንጀት የጠለቀ መሆኑን ለማጠየቅ የቆመ ቃልግጥም ነው ማለት ይቻላል፡፡

*361. ፍቅርህና ፍቅሬ በጋን ተጠንስሶ*
*ሳይጠጣ ቀረ ሰባራው አፍሶ*
*መለየቱን እማ ወድጀን ተለየሁ*
*እንደበከር ጊደር ዞሬ ዞሬ እያየሁ፡፡*
*/እርጉዬ ለገሰ / ካሴት ቁጥር 10/*

ይህ ቃል ግጥም የተሰበሰበው በ14/05/2005 ማክሰኞ እለት ከወ/ሮ እርጎየ ለገስ ነው፡፡የምትኖረው መና መ/አለም ቀበሌ ምድርቤት አቦ ጎጥ ነው፡፡ ወፍጮ መፍጨት የጀመረች ሌሊት በ8 ሰአት ነው፡፡‹‹ቀን ሌላ ስራ ስንሰራ ውለን ሌሊት ስንፈጭ እናደራለን፡፡ በጎውንም ክፉውንም ካላንጎራጎርን ደግሞ ስራው አይሄድልንም፡፡››(እርጎየ ለገሰ ካሴት/ ቁጥር 10) እንደዚሁም እርጎየ ያለፈ ህይወቷን እንዲህ ስትል አጫውታኛለች፡፡‹‹የመጀመሪያ ባለቤቴ መላክ ጠጋ ይባል ነበር፡፡አባቴ ወደኛ ቤት ና ተቀመጥ ካልመጣህ ልጅቱን አልሰጥህም አለው፡፡ መላክ እኔን ስለሚወደኝ ወደ እኔ ቤተሰቦች መጥቶ በአንድ ላይ መኖር ጀመርን፡፡ የወላጆቹ ልጅ አንድ እሱ ብቻ ስለነበር ሃይለኛ ጠብ ተፈጠረ፡፡‹‹የለገሰ ገበሬ፤ሎሌ፤አገልጋይ››እያሉ ይሰድቡት ጀመር፡፡በዚህ ምክንያት ያለ ውድ በግድ ተፋታን፡፡እንደተፋታን እሱም ህዳር 20 እለቱ እሁድ 1990

አ.ም በጠፍር ታንቆ ሞተ፡፡ይህንን ድርጊት ሳስብ ሁልጊዜ ያመኛል፡፡››(እርጎየ ለገሰ ማክሰኞ 14/05/2005)

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች ጋብቻ በአብዛኛው ለሌሎች ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ አማትና ቤተዘመድ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ አግቡኞች ማለትም የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች በግል ጉዳያቸው ከተጣሉ ተጋቢዎቹ ወጣቶች እንዲፋቱ ይደረጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ግጥም አቀነቃኝ እርጎየ የአማትና የወላጅ ዱላ ያረፈባትና ከባለቤቷ ጋር ሳይፈቅዱ የተፋቱ መሆናቸውን በምሬት ትገልጻለች፡፡ ‹‹ፍቅርህና ፍቅሬ በጋን ተጠንስሶ ሳይጠጣ ቀረ ሰባራው አፍስሶ›› የሚለው ስንኝ የሚገልጸው የተጋቢዎቹ ፍቅር ገና ውጥን ነው፡፡ ለፍሬ አልበቃም፡፡ ወይም ጥንስሱ ገና ወደ ወይን ጠጅ አልተለወጠም፡፡ ቢለወጥም ለመጠጥ አልበቃም፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ የጋኑ መሰበርና ማፍሰስ ነው፡፡ የተጋቢዎቹ እናትና አባት በጋን ተመስለዋል፡፡ ጋኑ በመሰበሩ የወይን ጠጁ ይደፋል፡፡ በወላጆች መጋጨት የልጆች ትዳር ይፈርሳል፡፡ ስለሆነም ጋኑ እና የተጋቢዎች ወላጆች ትይዩ ናቸው፡፡

እንደዚሁም ‹‹መለየቱን እማ ወድጀን ተለየሁ እንደ በካር ጊደር ዛሬ ዛሬ እያየሁ›› የሚለው ቃልግጥም እንደሚጠቁመው እርጎየ ባሏን ያለፍላጎቷ እንድትፈታ ተደርጋለች፡፡ ‹‹አባቴ አላደርገውም፣ አልሄድም›› ማለት በማህበረሰቡ ህግ የሚያስወግዝ፣ በአባት ልሳን የሚያስረግም በመሆኑ መድፈር አትችልም፡፡ የልማዱ እስረኛ ናት፡፡

ስለሆነም የምታፈቅረውን ልጅ በአካባቢው ልማድ ተጽዕኖ ስትለይ የተሰማትን ሀዘንና ብሶት ለመግለጽ ራሷን ከበካር ጊደር ጋር አነጻጽራለች፡፡ በካር ጊደር ጥጃዋን ሲነጥቋት በደመነፍስ ህልውናዋ የምታደርገው መቅበዝበዝ፣ መሮጥ፣ መጮህና መባከን ለተመልካች አሳዛኝ ነው፡፡ የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ እርጎየም የምታፈቅረውን ባሏን ያለ ምክንያት እንድትለይ ስትደረግ የሚሰማት ሀዘን ዞሮ ይገጥማል፡፡ ስለሆነም የአቀንቃኟ የስሜት ጥልቀት፣ የብሶት ምጥቀት ከበካር ጊደር በላይ ሊያስረዳላት የሚችል የለም፡፡ ጊደሯ ጥጃዋን ማጣቷ እና ግለሰቧ ባሏን መፍታቷ ትይዩ ናቸው፡፡ግለሰቧ በዚህ መልክ በማነፃፀርም የደረሰባትን በደልና ግፍ ጠቁማለች፡፡

372. *በቀይቱ ዶሮን እየተመሀኘ*
*በጥቁረቱ ዶሮ እየተመሀኘ*
*በነጭነቱ ዶሮ እየተመሀኘ*
*የኔስ በሽታዬ ሰው ሆኖ ተገኘ፡፡*
*/ደብሬ አለሜ ካሴት ቁጥር 9/*

ይህ ቃል ግጥም ሰኞ 27/ 05/2005/ ደብር ተ/ሃይማኖት ቀበሌ ወ/ሮ ደብሬ አለሜ ጤፍ እፈጨች የአቀነቀነችው ነው፡፡በወቅቱ አቶ ደጉ አለሜ፣ አቶ ነጋ ሲሳይና አቶ አለሜ ተገኘ አበረውኝ ነበሩ፡፡የዚህ ቀበሌ ነዋሪ ሴቶች የአፈቀሩትን ይሁን የሚሹቱን ሁሉ አውጥተው እንደልብ ለመናገር እድል የላቸውም፡፡ እንደልባቸው መናገር የሚችሉት ሲፈጩ በሚዘፈኑት ነው፡፡(ወ/ሮ ደብሬ አለሜ 27/05/2005) ‹‹የልጆቻችንና ሚስቶቻችን ባለጌነት ይሁን ጨዋነት የምናውቀው በወፍጮ ዘፈን ነው፡፡››(አቶ አለሜ ተገኘ፣ 27/05/2005)

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ደብሬ የአፈቀረችውን ልጅ አፍ አውጥታ ባለመናገሯ ምክንያት ጤናዋ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ወድቋል፡፡ ምቾት አይሰማትም፡፡ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ውላለች፡፡ በጤናዋ የተጨነቁት ወላጆቿ ደግሞ ከተለያዩ መድኃኒት አዋቂዎች መሄዳቸው አልቀረም፡፡ ደጅ የተጠናባቸው ቅጠል በጣሽ፣ ስርማሽ፣ መጽሐፍ ገላጭ ሁሉ አንደኛው ቀይ ዶሮ እሹላት፣ ሌላኛው ጥቁር ዶሮ ባሉለት እንደዚሁም ነጭ ዶሮ አዙሩለት በማለት እንደ ችሎታቸው ታማሚዋን ለመፈወስ ሞክረዋል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ባለ መድኃኒት ለታማሚዋ በሽታ ፈውስ፣ ለስቃይዋ እረፍት ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ‹ቆቅ ወዲያ ምዝግዝግ ወዲህ› እንደተባለው በሽታዋና መድኃኒቷ ተለያይተዋል፡፡

በመሆኑም ልጃገረዷ ‹‹ህመሙን የደበቀ መድኃኒት የለውም›› እንደተባለው በመደበቋ እና ቤተሰቦቿም ባለመገመታቸው ምክንያት ከህመሟ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው በርካታ ዶሮዎች በወንዝ እየተወረወሩ፣ በጆርባ እየዞሩ በከንቱ መስዋዕት ከፍለዋል፡፡ ‹እውነትና ንጋት እየቀደም ይጠራል› እንደተባለው እውነት ሲወጣ ግን የግለሰቧ ህመም ፍቅር እንደሆነ በአንደበቷ ትገልጻለች፡፡ ‹‹የኔስ በሽታዬ ሰው ሆን ተገኘ›› የሚለው ስንኝ የግለሰቧ በሽታዋም ሆነ የበሽታዋ መድኃኒት ያፈቀረችው ግለሰብ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

*407. ለቀይ ልጅ ቢሉኝ በረበሬ በላሁኝ*
*ለጥቁር ልጅ ቢሉኝ ከሰል ቆረጠምኩኝ*
*ኧረ ለጠይሙስ መድኃኒት አጣሁኝ።*
*/ደብሬ አለሜ ሻሴት ቁጥር 9/*

የቃልግጥሙ አቀንቃኝ የተለያየ መልክ ያላቸው ወንዶችን በተለያየ ጊዜያት አፍቅራ እንደነበር ትገልጻለች፡ ይሁን እንጂ መልካቸውን የሚመስል እና ከፍቅር ጅራፍ ግርፋት ለቀዩ የሚያቃጥለውን በረበሬ በመብላት እና ለጥቁሩ ደግሞ ከሰል በመቆርጠም ከፍቅር በሽታዋ ተፈውሳለች። የሆነ ሆኖ አሁን ከበድ ያለው እና መድኃኒት ያጣችለት ለጠይሙ ልጅ ነው። ለጠይሙ ልጅ በፍቅር ከወደቀችለት በኋላ እንደ በፊቱ የተለያዩ አማራጮችን ብትወስድም ከህመሟ ልትድን እና ልታገግም አልቻለችም። ከዚህ ላይ ቃል ግጥሙ እንደሚያስረዳው የፍቅር ሃያልነት ወይ እንደየሰዉ ወይም እንደየ ተመልካቹ ብትሩ ሊለያይ እንደማይችል ነው።

ለሌሎቹ ሴቶች የቀይና ጥቁር የፍቅር ሚዛን ሊደፋባቸው ይችል ይሆናል። ለዚህች ዘፋኝ ግን የጠይሙ ልጅ ፍቅር መድረሻ አሳጥቷታል። ጸበል ይሁን ሀኪም፣ በርበሬ፣ ይሁን ከሰል የተለያዩ መድኃኒቶችን ተጠቅማ መፍትሄ አጥታለች። ስለሆነም በጠይም ልጅ ፍቅር የተለከፈ ሰው ፈውስ ንደማይገኝለት ወይም መድኃኒት እንዳልተሰራላት ታሳስባለች።

## 4.4. ንቀትና ጥላቻን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች የማፍቀራቸውን እና የማሞገሳቸውን ያህል በመልክ፣ በእድሜ፣በወሲብ እና በሃብት የማይመስላቸውን ወንድ በቤተሰብ ጫና በሚያገቡበት ወቅት የመናቅ ስሜት ይታይባቸዋል።ቀጥሎም የንቀት ግጥሞች ተተንትነው ይቀርባሉ።

*501.አሮጌ ሙጉሙ የጎታ መከደኛ*
*በል እስከዚያው ድረስ በኋላዬ ተኛ*
*የሌላም አይደለ የንፋስ መዳኛ።*
*/ታከላይ መኮንን/ ካሴት ቁጥር 5/*

ይህን ግጥም ረቡዕ 8/05/2005 ዓ.ም ከወ/ሮ ታከለይ መኮንን የተገኘ ነው። በአይኔ እንደ አየኋቸው እና እንደነገሩኝ አቶ ሞላ ዘገየ በደርግ ጊዜ እግራቸው በጥይት ተመትቶ በመጎዳቱ ምክንያት የሚንቀሳቀሱት በብትር ተደግፈው ነው። ይሁን እንጂ

ሀብትና ንብረታቸው፣ የአገር ሽማግሌ በመሆን አስታራቂነታቸው በአካባቢው እንዲታወቁ አድርጓቸዋል፡፡ (ታከለይ መኮንን ረቡዕ 08/05/2005 ዓ.ም)

የዚህ አካባቢ ሴቶች ባሎቻቸውን ለመናቅም ሆነ ለመጥላት ወሲብ፣ መልክ እና ሀብት የመሳሰሉ ክስተቶች ዋና ዋና መነሻ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝን ግለሰቡን የምትንቀው ከአለው የአቅም ውስንነት በመነሳት ይመስላል፡፡ በመናቁና ድክመት በማሳየቱ ምክንያት ባል ከሚታወቅባቸው ስርዓቶች ውጭ ይሆናል፡፡ በሚስቱ ፊት ለፊት የመተኛት አይን ጥርሷን የማየት አጐጥጓጤዋን የመጨበጥ እድል የለውም፡፡

‹‹አሮጌ ሙጎን የጐታ መክደኛ›› የሚለውን ስንኝ ስንመለከት እንደ አካባቢው አጠራር ጎታ ማለት ከጭቃ የተሰራ የእህል ማጠራቀሚያ ጎተራ ነው፡፡ ግለሰቡ የሚመስለው በአሮጌ ሙጎን (ምጣድ) ነው፡፡ ምጣድ ሲገዛም ሆነ ሲሟሽ ነጭና አይናማ እንጀራ ለመጋገር ታስቦ ነው፡፡ ከአገልግሎቱ ሲወጣ ግን ያለ ባህሪው የጐታ መክደኛ በመሆን ያገለግላል፡፡

የዚህች አቀንቃኝ ባል የሆኑት ግለሰብም ደካማ በመሆናቸው ምክንያት ባል ከሚታወቅበት ባህሪ ወጥተው ከኋላ በኩል ይተኛሉ፡፡ ሰብአናቸውን ይቀማሉ፡፡ ወደቁስነት ተቀይረው የንፋስ መከላከያ ብርድልብስ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ባሎቻቸውን የሚንቁ ሴቶች ነገሩ እየከረረ ሁኔታው እየመረረ መጥቶ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ቀጥሎ የሰፈረው ቃል ግጥም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡

*495.እስኪ ውሃ ስጡኝ ሆዴን ልለቅልቀው*
*የዚህን ከዚያኛው እንዳልደባልቀው፡፡*
*/ወ/ሮ የሻረግ ታፈሰ 07-05-2005 ማስታወሻ/*

ይህ ቃል ግጥም ከየሻረግ ታፈስ ማክሰኞ 07/05/2005 ዓ.ም የተገኘ ነው፡፡ የሺ አረግን ቀን ላይ ስንዴ እየፈጨች ከአረጋ አበራ እና ወንድሟ ከመላሽ ታፈስ ጋር በመሆን ነበር፡፡በቤቷ የተመለከትናት፡፡ እሷም ዲያቆን ፈለቀ በየነ የተባለ ግለሰብ አግብታ እንደነበርና ከኮቧ አልገጥም ብሎ እንደፈታችው አጫውታኛለች፡፡(ወ/ሮ የሻረግ 07/05/2005)

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ የሻረግ ከዚህ በፊት ሌላ ሰው እንደውም ዲያቆን አግብታ እንደነበር ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ባለ መደሰቷ እና በመናቋ ምክንያት ፈትታዋለች፡፡

አሁን የሚሆናትን እና ደስ የሚላትን ሰው አግኝታለች፡፡ ቢሆንም የቀደመው ህይወቷ ያስጠላታል፡፡ ግለሰቧ ያሳለፈችውን የቀድሞ ግንኙነት እንደ ኃጢአት ወይም መጥፎ የስም ቁስል አድርጋ ተቀብላዋለች፡፡ ይህ ቁስሏ ሁልጊዜ እየናቆረና እየመረቀዘ እንዲያስቸግራት አትፈልግም፡፡ ዘላለማዊ ፈውስ ትሻለች፡፡ የሻረግ የቁስሏ ይሁን የህመሟ ፈውስ አድርጋ የወሰደችው በውሃ መታጠብን ነው፡፡ ‹‹እስኪ ውሃ ስጡኝ ሆዴን ልለቅልቀው›› የሚለው ስንኝ በውሃ መታጠቧ የግለሰቧን የአለፈውን ታሪኳን ይሁን ስሟን ለመቀደስና አዲስ ልደት ወይም አዲስ ህይወት መጀመሯን ይገልጻል፡፡ ስለዚህ በውሃ መታጠቧ ያለፈውን ታሪኳን ለመቀደስና አዲስ ልደት ወይም አዲስ ህይወት መጀመሯን ለማዘከር ነው፡፡

ብሉዩን ከህዲሱ ወይም በናቀችው ሰው የረከሰ ህይወት፣ ከአሁኑ ከምትወደው ሰው ቅዱስ ህይወት ጋር ማደባለቅና ማስቀጠል አትፈልግም፡፡ የውሃው እጥበት ያለፈን የተናቀ ሰው ትቢያና አቧራ በማንጻት ዳግም የመወለድ፣ የመቀደስና የመባረክ ተምሳሌት ነው፡፡ ቃልግጥሙ በውሃ በመታጠብ መንጻትን፣ በመንጻት አዲስ ህይወት መጀመርን የሚያዘክር ነው፡፡ አንዳንዶቹ ሴቶች በመናቅ ምክንያት ትዳራቸውን ፈትተው ሌላ ያግቡ እንጂ በግልባጩ ደግሞ የመጀመሪያ ትዳራቸውን በሌላ ተፅዕኖ በመፍታት ቀጥሎ ያገቡትን ሲንቁ ይስተዋላሉ፡፡

*486.ብሩን ቀለበቴን ለውጨው በመዳብ*
*በቀይም ቢሆን በጥቁር አመዳም፡፡*
*/አስረበብ አለቤ/ካሴት ቁጥር3/*

ይህ ግጥም ወ/ሮ አስረበብ አለቤ ሰኖ 20/05/2005 ዓ.ም በወፍጮ ላይ ያቀነቀነችው ነው፡፡ ወ/ሮ አስረበብ አባቷ አቶ አለቤ ጥሩነህ ሀብታም ስለነበሩ ለመሰላቸው ሰው ለበሽር አየለ ልጅ ለካሳው በሽር ድረዋታል፡፡ 6 ሙክት ‹‹ግጥግጥ›› በሚል በልተዋል፡፡ ግለሰቡ ለአቅማዳም የደረሰ በመሆኑ የጭን ገረድ አግብቶ 3 ልጆች ወልዷል፡፡ በዚህና በመሰል ጉዳዮች አቶ አለቤና አቶ በሽር ተጣልተው የልጆቹ ትዳር ፈርሷል፡፡ አስረበብም ‹‹የመጀመሪያዬ ሁኖ ነው መስል ካሳውን እወደዋለሁ››ብላኛለች (አስረበብ አለቤ 20/05/2005 ዓ.ም)፡፡

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ወ/ሮ አስረበብ የመጀመሪያ ባሏን ያለ ፍላጐቷ እንደተፈታች በመጠቆም ኋላ የገጠማትን እጣ ፈንታ ገልፃለች፡፡ የቀደመውን ባሏን እና የአሁኑን ባሏን በማወዳደር እና በማመሳሰል ታነፃፅራቸዋለች፡፡ አስረበብ ትዳር መመስረቷን ለመግለጽ ቀለበት የሚለውን ምልክት በዘፈን ትጠቅሳለች፡፡ ቀለበት ትዳር የመመስረቷ ምልክት ነው፡፡ የቀድሞ ባሏ የብር ቀለበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አቶ አለቤ ጥሩነህና አቶ በሽር አየለ ባደረጉት እሰጣ ገባ ምክንያት ከምትወደው ሰው ጋር የነበራት የትዳር ህይወት አልሰመረም፡፡ አሁን ሌላ ሁለተኛ ባል አግብታለች፡፡ ይህ ባሏ ግን ልቧን ሊመታት፣ ቀልቧን ሊስባት አልቻለም፡፡ ለዚህ ዋናው ተጠቃሽ ምክንያት ደግሞ የመልኩ ማነስ ነው፡፡ ይህ ባሏ መልኩ 'ጥቁር' ነው፡፡ ጥቁር እሷ አትወድም፡፡ ቀይ ደስ ይላታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የመጀመሪያው ባሏ እንደሚጸጽታት የአሁኑ ደግሞ እንደሚያስጠላት ትገልጻለች፡፡ ንቀቷን ለመግለጽ ‹‹በቀይም በሆነ በጥቁር አመዳም›› በማለት ቀይና ጥቁርን፣ ብር እና መደብን በማነጻጸር ለቀደመ ባሏ ‹‹ብርና ቀይን›› ለአሁኑ ባሏ ደግሞ ‹‹መደብና ጥቁርን›› በመስጠት በንጽጽር የጥላቻና የንቃቷን ደረጃ ጠቁማለች፡፡

*510.ሊያበቅለው የለ ሰኔና ግንቦት*
*አክ እንትፍ እናቱ ምኑን በላሁት፡፡*
*/እርጎዬ ለገሰ/ 14-05-2005/*

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ሴት እርጎዬ ግለሰቡን በስም ባትጠራውም፣ በአካል ባትገልጠውም ጥላቻዋ የከፋ ነው፡፡ ‹‹ሊያበቅለው የለ ሰኔና ግንቦት›› የሚለው ስንኝ ሰኔና ግንቦት ዝናብ የሚዘንብበት የበልግ ወራት በመሆኑ ስንዴና እንክርዳድ፣ እሾህና አሜከላ፣ ጥሩና ጥሬ በአንድ ላይ ይበቅሉበታል፡፡ አዝርዕት አረም እንደሚበቅልበት ሁሉ አገርም ቢሆን ጠይሙ፣ ቀዩ፣ ጥቁሩ፣ አጭሩ፣ ረጅሙ፣ ወፍራሙ፣ ቀጭኑ ሰው ሁሉ የሚወለድበትና በአንድነት በቅሎ የሚኖርበት ነው፡፡

ከእነዚህ ጉራማይሌ ሰዎች መካከል ለባለ ታሪኳ የደረሳት ጓደኛ ደግሞ በእሷ ዓይን ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ‹‹አክ እንትፍ እናቱ ምኑን በላሁት›› የሚለው ስንኝ አንድም ግለሰቡ ከባለታሪኳ ስጋና ደም ጋር አልተዋሃደም፡፡ ወደ ውስጧ አልዋጠችውም፡፡ ተፍታዋለች፡፡

ከግለሰቡ ጋር ዓይንና ናጫ፣ ሆድ እና ጀርባ ናቸው። ለእናቷ ይህን ጥላቻ መንገሯ ደግሞ እናት በመሆኗ ብቻ ሳይሆን የሴቶችን ችግር አጥርቶ የሚያውቅ ከእሷ በላይ በጉዳናው የተመላለሰ፣ በጉዳዩ የበሰለ ሰው የለም ብላ በማሰብ ነው።ከማይወዱት ወንድ ጋር መኖርን ለሆድ ከማይስማማና ከሚያቅር ምግብ መብላት ጋር በማመሳሰል ጥላቻዋን ገልፃለች።

## 4.5. ክፋትና ደግነትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች በወፍጮ ስራ ላይ በሚያንጎራጉሯቸው ቃል ግጥሞች ሰውን በክፋትና ደግነት ይፈርጁታል።እንደነእሱ አጠራር ጎባንን ደግሞ በባላንጣነት ያዩታል።ቀጥሎም የሰውን ክፋትና ደግነት፣ የጎባንን ክፋነት የሚመለከቱ ግጥሞች ተተንትነው ይቀርባሉ።

### 4.5.4. የሰውን ክፋትና ደግነት የሚገልፁ ቃልግጥሞች


*527.ሰው ያለ ወገኑ ከብት ያለ መንጋው*
*እንቅፍ ያለ ለታ ደጋፊም የለው።*
*/አስረበብ አለቤ ካሴት ቁጥር 6/*

ይህ ግጥም የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር መሆኑን በመግለጽ ሰው ከሰው ውጭ ሊቆም ብሎም ህልውና ሊኖረው እንደማይችል የሚገልጽ ነው። አይደለም የሰው ልጅ እንስሳ እንኳን ከመንጋው ጋር በመሆን ከደራሽ ጠላት ይጠበቃል በማለት ያነጻጽራል።‹‹እንቅፍ ያለ ለታ ደጋፊም የለው።›› የሚለው ስንኝ የሰው ልጅ ህይወት በደስታና በመከራ ጠገግ ያለ በመሆኑ ምክንያት ሰው ብቻውን ወይም እርቃኑን መቆም አይቻለውም። በመከራ ጊዜ ለሰው ደራሹ ሰው ነው። ሰው ይታመማል፤ ያጣል፤ ይነጣል፤ ይታሰራል፤ በእነዚህ አስቸጋሪ የህይወት ጉዞዎች ሁሉ ከገባበት ረግረግ፣ ከወረደበት ማጥ መሰላል ሆኖ ሊያወጣው የሚችለው ራሱ ሰው ነው። ስለሆነም ሰው ያለ ሰው መኖር እንደማይችል አውቆ ሰው ለሚባለው ፍጡር ትልቅ አክብሮት መስጠት ያለበት መሆኑን የሚያዘክር ቃልግጥም ነው። ሰው ያለ ሰው ተልጦ እንደሚያልቅ ቀይ ሽንኩርት ልብስ የሌለው እርቃን ነው። ስለዚህ ሰው ለሰው ኃፍረትና ሚስጥር ደባቂ፣ መከለያና መጠጊያ እምባ ነው የሚል አንድምታ አለው።

545. እረ ሰው እረ ሰው እረ የሰው ነገር
ልቤ ይዟል ተንኰል አፌ ባይናገር።
/ቦሴ ውብሸት /08-05/ 2005 ማስታወሻ/

የቃልግጥሙ አቀንቃኝ ቦሴ ከሰው አይን እና እይታ ለማምለጥ ይሁን ሰው የሚለውን ነገር ለማወቅ ለመመርመርና ለመረዳት ከብዷታል፡፡ ‹‹እረ ሰው እረ ሰው እረ የሰው ነገር›› የሚለው ስንኝ በውስጡ ሰው ሊታወቅ እና ሊመረመር የማይችል ፍጡር መሆኑን ያዘክራል፡፡ የሰው ነገር ሰው በልቡ ምን እንዳለ፣ ምን እንደሚያስብ ማወቅ አይቻልም፡፡ ሰው አይደለም ለሌላው ለሩቅ ሰው ይቅርና ለራሱም ባዕድ ነው ይባላል፡፡ስለዚህ ከሰው ሀሜትና ነገር ለመዳን እና ለመከለል መወሰድ ያለበት መፍትሄ ግቢ ከማጠር፣ በር ከመቆለፍ ይልቅ የአንደበት በር መዘጋት አማራጭ እንደሆነ የሚመክር ቃልግጥም ነው፡፡በሰዎች ልሳን የተገረፈችው ግለሰብ ብሶቷን በልቧ ይዛ የአፏን በር ቆልፋለች፡፡ ይህንም እንደ ብቸኛ መፍትሄ በመውሰድ ከደረሰባት በደል ለመዳንና ለመፈወስ ጥረት ስታደርግ ይስተዋላል፡፡

532. አዳራሹ ቤቴ ጠምበለል ማገሩ
ሰተት ብለህ ግባ የሸበር መንደሩ
ምን ያሸብረዋል የመንደሩ ሰው
የመጣውን እዳ እኔ ልችለው።
/ክቴ ደመቀ/ካሴት ቁጥር3/




ፎቶ ግራፍ 20/ ወ/ሮ ክቴ ደመቀ
( በ07/05/05 አዲያ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ክቴ የሰውን ጣልቃ ገብነት ትሞግታለች። ሰው በግለሰቦችና በተፈጥሮአዊ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ መግባት የለበትም፣ሴቶች የማፍቀር እና የመፈቀር መብታቸው መጠበቅ አለበ፣ይሁን እንጂ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ያለጉዳያቸው እየገቡ፣ ያለ ምክንያት እየታደሙ፣ ነገሮችን መፈትፈት የለባቸውም በማለት የሰፈሩን ጣልቃ ገብነት ትተቻለች።

የአከባቢዋ ሰዎች ፍቅረኛዋ ወደ መንደር ዘልቆ ሲገባ ይሸበራሉ፤ ይጨነቃሉ፤ ሲፈልጉ ያሚታል፤ ጥሬ ስጋዋን ይበሏታል፤ በዚህ ሁኔታ የተማረረችው ክቴ ‹‹ምን ያሸብረዋል የመንደሩ ሰው የመጣውን እዳ እኔ ልችለው›› በማለት ለቀቀ እንዲያደርጓት ታሳስባለች። እንደዚሁም የሴቶች የማፍቀርና የመፈቀር ነጻነት በግለሰቦች እንጂ በማህበሩ ሰዎች እጅና በጉ ፈቃድ ላይ መውደቅ እንደሌለበት ታሳስባለች።

*525. እንግዲህ ለባዕዳ እንግዲህ ለሰው*
*አፌም አይናገር ሆዴም አይረሳው።*
*/ማሚት እሸቱ/ካሴት ቁጥር 2/*



ፎቶግራፍ 21/ ወ/ሮ ማሚት እሸቱ

(በ06/05/05 አጃ ዘቀልሞቃ ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)

ማሚት እሸቱ የተባለችው የቃል ግጥሙ አቀንቃኝ ከበደል ሁሉ ሰው ያደረሰባት በደል ሚዛን ደፍቷል። እንደበቷን ለጉሟል። ሆዷን ዘልቆ በቅሏል። የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ሰውን በማመን የሆዷን ሚስጥር አውጥታ በመናገር ምክንያት ችግሯን ከመረዳት፣ ብሶቷን ከመጋራት ይልቅ ሚስጥር ‹‹የሽምብራ ወፍጮ›› ሆኖ ለአደባባይ ተዘርቷል። በዚህ ምክንያት ሰው ለሚባለው ፍጡር ከዚህ በኋላ እንደበቷ እንደማይከፈት በመጠቆም የደረሰባት በደል ከሆዷ እንደማይወጣ ትጠቁማለች።

የቃልግጥሙ አንድምታ ሲታይ ሰው ለሰው ባዕድ እንደሆነ ያዘክራል። በዚህ ምክንያት ቃልግጥሙ ሰው የሚባለው ሊመኩበት የማይችል መሆኑን ማወቅ እንደሚገባ ያስገነዝባል። ከዚህ ይልቅ ‹ቀድሞ የተናገረን ሰው ይጠላዋል፤ ፊት የወለደን ወፍ ይበላዋል› እንደተባለው ሁሉን ነገር ከመናገር መቆጠብን ነገሮችን በሆድ መያዝን መልመድ እንደሚገባ ቃልግጥሙ ያመለክታል።

*526. ኧረ ሰው ኧረ ሰው ሰው አስቸገረኝ*
*ሲናገሩ አፈኛ ዝም ሲሉ ሞኝ።*
*/እርጎዬ ለገሰ/ካሴት ቁጥር9/*

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ሴት እርጎየ ሰው የሚባለው ፍጡር አስተሳሰብና አመለካከት መረዳት የአስቸገራት ይመስላል። የሰው ፍላጎት ይሁን ባህሪ በየወቅቱ ሊቀያየር የሚችል በመሆኑ ምክንያት ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለማወቅና ለመረዳት አዳጋች ነው።የልጅቱ ብሶት ሁለት መልክ አለው። ዝምታን በመምረጥ እንደበቷን ቆጥባ፣ ሰምታ እንዳልሰማች አይታ እንዳየች በምታልፍበት ወቅት ሰዎች ከ‹‹ቂል››ና ከሞኝ ተርታ ይመድቧታል።

በአንጻሩ ደግሞ በጠየቋት ልክ ስትመልስ፣ ባየችው መጠን ሁሉ ስትናገር ደግሞ ‹‹አፈኛ›› ‹‹ምላሰኛ›› ይሏታል። በዚህም ከሰው ትችት ማምለጥም ሆነ መዳን አለመቻሏን ሰው በሚባለው ፍጡር መቸገሯን ነው የገለጸችው።

### 4.5.2. የጉባንን ክፋት የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

ጉባን ጣውንት የሚለውን ቃል የሚወክል ሲሆን ጉባን ማለት ባሏን የነጠቀች ሴት ለተነጣቂዋ ጉባን ስትሆን ተነጣቂዋም ለነጣቂዋ ጉባን ናት።ሁለቱ ሴቶች መካከል የሚደረግ ፉክክር ጠብና ግጭት ይኖራል።

*563.በሞቴ አትቆጭ እቴ ባልንጀራ*
*እንዴት ይጣፍጣል የስርቆት እንጀራ።*
*/ውብነሽ ታከለ /ካሴት ቁጥር8/*

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ግለሰብ በአንድ ሌማትና ዕዋ እየበላይና እየጠጣይ የምትኖረውን የጓደኛዋን ባል በድብቅ ይዛባታለች። ለዚህ ስህተት ደግሞ እንደ ምክንያት የምትጠቅሰው የተሰረቀና የተከለከለ ነገር በጣም ጣፋጭ መሆኑን ነው። ሰዎች አታድርጉ የተባሉትን ነገር ሲያደርጉ ደስታ እንደሚሰጣቸው የሚገልጽ ቃል ግጥም ነው።

የግጥሙ አቀንቃኝ ጓደኛዋን ለመበደል ይሁን ለመጉዳት አስባ ሳይሆን። ከእሷ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት የተነሳ ድርጊቱን እንደፈጸመች ግጥሙ ይጠቁማል።ይህም አዩኝ አላዩኝ፣ ሰሙኝ አልሰሙኝ ተብሎ የሚፈጸም ድርጊት እንካችሁ ተብሎ ከተፈቀደውና ማህበረሰቡ ከተቀበለው በላይ ብልጫ ያለውና ጣፋጭ እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷል።የግጥሙ ተናጋሪ ተበዳይ ጓደኛዋ ባትቀበላትም በሽሙጥ ይሁን ይቅርታ አድርጊልኝ ድምጸት ጓደኛዋን ትማጸናለች።

*561.ምነው ገለፈጥሽኝ ከጓዳ እንደወጣ*
*ከየት ሂደሽ ኖሯል አጋድምሽ ሲመጣ።*
*/ውብነሽ ታከለ/ካሴት ቁጥር8/*

ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ግጥም ያዜመችው ግለሰብ የቤቱን ሚስት ንቆና ደቅድቆ ወደ እሷ በመሄዱ ኩራት ተሰምቷታል።የዚህ አካባቢ ማህበረሰብ በሚስቱ ላይ ውሽማ መያዝን በይፋ ያወግዛሉ። ነገሮቹ ሰፋ ሲሉም በነፍስ አባት የሚገዘትበት አጋጣሚም ሊኖር ይችላል። የግጥሙ አቀንቃኝ ግን በጥፋቷ ራሷን መውቀስ ወይም ኃላፊነት መውሰድ አልፈለገችም። ከዚህ ይልቅ ስህተትና ችግሩ ከቤት ያለችው ሚስት እንደሆነ አጽንኦት ትሰጣለች።

‹‹ከየት ሂደሽ ኖሯል አጋድምሽ ሲመጣ›› የሚለው ስንኝ የጉባዷን ሰብእና የሚፈታተን አነጋጋሪ ነው። ሌባ የሚባለው ቤት ሰብሮ፣ ግድግዳ ሰርስሮ፣ በዱርና በገደል አጥምዶ ሊወስድ የመጣ እንጂ የመጣውን የበላ ጥፋተኛ አይደለም የሚል አንድምታ በግጥሙ ይንጸባረቃል። አቀንቃኟ ጎባዷን አንቺ አንድም እንቅልፋም በመሆንሽ ምክንያት ንቆሻል በግርማ ሌሊት በድምጸ አራዊት እንደ ዕቃ አጋድሞሽ ሄዷል እያለች ሰብእናዋን ታወርደዋለች።

*586.እውነቱን መሰለሽ እኔን ትቶ ካንቺ*
*ያላየውን አይቶ ሊመጣ ነው እንጂ ።*
*/አስረበብ አለቤ/ ካሴት ቁጥር 7/*

በዚህ ማህበረሰብን ሚስትን ወደ ጐን በመተው ወንዶች ሁለተኛ ሴት በሚይዙበት ወቅት ቤት ውስጥ ያለችው ሴት አንዳች ነገር እንደጐደላት ተደርጐ ይወሰዳል። ይህን አስተሳሰብ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው የድርጊቱ ተጠቂ ባለቤት የሆኑት ሴቶቹም ቢሆን ከመልካቸው ይሁን ከሙያቸው አንድ ነገር እንደሚጐላቸው አምነው ይቀበላሉ። በዚህ የተነሳ እንደልባቸው ወንዝ ወርደው ውሃ መቅዳት፣ አደባባይ ወጥተው ቤተክርስቲያን መሳምና ማህበር መጠጣት አይችሉም። ይህች ባሏን ያስነጠቀች ተብሎ በሽሙጥ ይጎነትላሉ። በመሆኑም እንደልብ ነጻ ሁነው መናገርም ሆነ መንቀሳቀስ አይችሉም። ድርጊቱ የደረሰባቸው እንደ ፍላጻ ይወጋቸዋል። ከላይ የቃልግጥሙ አቀንቃኝ ሴት ባሏን በጉባን ሌባ የተነጠቀች ናት። ስለሆነም በማህበረሰቡ ከሚደርስባት የመናቅና አንገት የመድፋት እጣ ፈንታ‹‹እውነት መሰለሽ እኔን ትቶ ካንቺ፣ ያላየውን አይቶ ሊመጣ ነው እንጂ›› በማለት ራሷን ታጽናናለች። ነገሩና ድርጊቱ ‹‹እውነት›› ሆኖ አይቀርም በጊዜና በነገሮች መለዋወጥ ተመልሶ ይመጣል። እኔ ከአንቺ አላንስም የመልክም ይሁን የሙያ ችግር ኖሮብኝ አይደለም፤ በማለት ለባሏ መሄድ ምክንያት ራሷን ከማድረግ ይልቅ ‹‹ያላየውን አይቶ ለመምጣት›› ያለውን ፍላጐት እንደማምለጫ ተጠቅማለች። ራሷን በመሸንገል ከህመሟ ለመፈወስ ከውጥረቷ ለመተንፈስ ጥረት ማድረጓ ይታያል።

*568.ከቤታችን በላይ ያለች ጥቁር ዶሮ*
*እባክህ አምራ ውሰድልኝ ቶሎ።*
*/አስረበብ አለቤ/ ካሴት ቁጥር 5/*

ይህን ቃል ግጥም የሰበሰብኩት በ20/05/2005 ዓ.ም ከወ/ሮ አስረበብ አለቤ ነው። ስለ ግጥሙ ከሳቸው ታሪክ ጋር አያይዘው ሲያጫውቱኝ ‹‹ከቤታችን በላይ ጠርዜ አበራ የተባለች ሴት ነበረች። አብረን እየበላን እየጠጣን ባሌን በድብቅ ያዘችው ይባስ ብላ ልጅ ወለደች ልጅቱም 10 ዓመት ሆኗታል። ዛሬ ግን በነፍስ አባታችን ተገዝቶ ቆርበናል።›› (አስረበብ አለቤ 20/05/2005 ዓ.ም) በወቅቱ ተጠቃሿ ሕፃን አብራ ሱፍ እየደቆሰች ነበር።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በጠላትነት ከሚፈረጁበት እና በባላንጣነት መንገድ እንዱ ጉባን ነው፡፡ ወንዶች ከሆኑ ቦታ ጠብቀው ቀን ቆጥረው ጉባናቸውን አካሉን ሲያጉሉ ነፍሱን ሊነጥቁ ይችላሉ፡፡ በሴቶች በኩል ደግሞ የመግደያ መሳሪያውም ሆነ የማህበረሰቡ ልማድ ስለሚገድባቸው እንደ ወንዶቹ ግድያ አይፈጽሙም፡፡ የአስረብብ አለቤ ጎባን እንደዚሁ ከቤቷ በላይ ጎረቤት መስላ ተቀምጣ ባሏን ነጥቃታለች፡፡ ‹‹ከቤታችን በላይ ያለች ጥቁር ዶሮ እባክህ አሞራ ውሰድልኝ ቶሎ›› በማለት ጉባኗን በጥቁር ዶሮ፣ ሞትን በአሞራ መስላ ፈጣሪ ቶሎ እንዲገድልላት ትማጸናለች፡፡ ሁለቱንም ቃልግጥሞች ስንመለከት ጉባን በዚህ ማህበረሰብ ምን ያህል ለሴቶቹ ትዳር መፍረስ፣ ኑሮ መዛባት ችግር ፈጣሪ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

560.እራሴን ልሰራ ቀጭን አፈሳሰ
ጉባኔ ሙታብኝ ልሄድ ነው እለቅሶ፡፡
(ክቴ ደመቀ/ካሴት ቁጥር3)

በዚህ ማህበረሰብ ሰው ሲሞት ራስ ይላጫል፣ ፊት ይነጫል፡፡ ነግ ለራሴ በማለት ይታዘናል፡፡ ነጠላ ይዘቀዘቃል፣ ደረት ይደቃል፡፡ ይሁን እንጅ ጉባን የሞተች ዕለት ግን ለቅሶው ለቅሶነቱን ይለቃል፡፡ ወደ ክብረ በዓል ይሁን ወደ ደስታ ተለውጦ ይውላል፡፡ ለዚህም ነው ጸጉር በመላጨት ፈንታ ጉባን ስተሞት ‹‹ቀጭን አፈሳሶ›› የሚሰራው፡፡ ‹‹ቀጭን አፈሳሶ›› ሴቶች የሚሰሩት ልጃገረድ ስትዳር እንደዚሁም ጥምቀትና ትንሳኤ የተባሉ በዓሎች ሲመጡ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የጉባን ሞት ከበአላቱ የማያንስ ሆኖ ይገለጻል፡፡ ግለሰቧ ከተዋረደችበትና ከሞተችበት የምትነሳ ጉባን ስትሞት ነው፡፡ የረከሰው ስሟ፣ የተናቀው ገላዋ የሚቀደስ በጉባኗ የሞት ጥምቀት ነው፡፡ ለዚህ ነው የግለሰቧ ጉባን መሞት ከጥምቀት እና ትንሳኤ ጋር የተማሰለው፡፡የተጠቂዋ ግለሰብ ባል በቁስ ተገዝቶ፣ በንደኛ ተመክሮ ተው ቢባል እንኳን ከዕለታት አንድ ቀን ተመልሶ ሊያገረሽበትና ሊሄድ ይችላል የሚለው ብሂል በግለሰቧ ዘንድ ‹እባብ ያየ በልጥ ደነገጠ› እንደተባለው የዘወትር ስጋት ነው፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ስጋት ነጻ፣ ከዘወትር ህመም ፈውስ ለማግኘት የሚያስችለው እና ጥርጥር የሌለው አማራጭ ወይም መድኃኒት የጉበኗ ሞት ብቻ ነው፡፡

## 5.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ‹‹በእብናት ወረዳ በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና›› በሚል ርዕስ ተጠንቶ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ ዓላማ አድርጐ የተነሳው በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞችን በመተንተን የሴቶችን የህይወት አመለካከት መግለፅ ነው፡፡ ወፍጮ በሚፈጭበት አውድ ላይ በቦታው በመገኘት በተፈጥሮ መቼት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቃል ግጥሞቹ እንደ መረጃ ሰጪዎቹ ፍላጐት እና ይሁንታ የተለያዩ የመረጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሜአለሁ፡፡ እነሱም ቪዲዮ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ፣ መቅረፀ ድምፅ እና የማስታወሻ ደብተር ናቸው፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች በመጠቀም በቀጥታ የቃል ግጥሙ ባለቤት ከሆኑት ሴቶች 612 ቃል ግጥሞች ተሰብስበው 55ቱ ተተንትነዋል፡፡

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች በአብዛኛው በሌሊት ወቅት ወፍጮ ሲፈጩ ያድራሉ፡፡ ለምን በመኪና ወፍጮ አታስፈጩም ለሚለው ጥያቄ ደግሞ አይበረክትም የሚል እምነትና የገንዘብ እጥረት መኖሩን በምክንያትነት ያነሳሉ፡፡ ወረዳዋ ነዋሪ ሴቶች በኑሮአቸው ላይ ህይወታቸውን የመረረ የሚያደርገው የስራ ጫና መብዛት በተለይም የወፍጮ ስራ መኖር፣ በልጅነት መዳር እና ሴት በመሆናቸው የሚደርሱባቸው በደሎች ናቸው፡፡ በወፍጮ ስራ ላይ የሚያቀነቅኗቸው ግጥሞች የወፍጮ ስራና በልጂነት መዳር እንዳማረራቸው የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

የእብናት ወረዳ ሴቶች የመማረራቸውን ያህል ሲያወድሱና ሲያሞግሱ ይደመጣሉ፡፡በአብዛኛው የሚያወድሱት እናትን፣የወረዳዋ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውን እርሻ ማረስን፣አገርን፣በግብርና ሙያ እና በአደን የታወቁ የአካባቢ ግለሰቦችን ነው፡፡ የእነዚህ ሴቶች የወፍጮ ስራ ግጥሞች በርካታ የፍቅር ስሜትን የሚገልጹ ናቸው፡፡ እነዚህ የፍቅር ግጥሞች በሴቶች ላይ በቤተሰብ ይሁን በማህበረሰቡ ጣልቃ እንደ ሚገባባቸው ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በእድሜ፣በመልክ እና በሃብት ከማይመስሏቸው ሰዎች ጋር ግቢ እንዲፈጽሙ ይደረጋሉ፡፡ በተጽእኖ የተፈጸመው ጋብቻ ደግሞ ከመጽናትና ከመግባባት ይልቅ ለንቀትና ለጥላቻ ይዳርጋቸዋል፡፡ ንቀታውንና ጥላቻቸውን በወፍጮ ግጥሞቻቸው ላይ ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡

የሰውን ክፋትና ደግነት፣የጎባንን ባላንጣነት የሚጠቁሙ ግጥሞችም እነዚሁ ሴቶች በወፍጮ ላይ ያቀነቅናሉ፡፡

የጥናቱ ግኚት የእብናት ወረዳ ሴቶች ደስታ፣ ብሶት፣ ፍቅርና የህይወት ጉዞ ምን እንደሚመስል ተንትኖ ያሳየ ነው፡፡ ሴቶቹ ወፍጮ መፍጨት ብቻ ሳይሆን ልጅ ወልዶ ማሳደግ፣ እንጨት መልቀም፣ ውሃ መቅዳት የመሳሰሉ አሰልቺ ስራዎችን ከጠዋት እስከ ማታ ያከናውናሉ፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የአካባቢው ነዋሪ ሴቶች ከደስታ ህይወታቸው ይልቅ የመረረ ህይወታቸው ሚዛን የሚደፋ መሆኑ በጥናቱ ተገኝቷል፡፡ የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች ከወረዳዋ መልአምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ የቴክኖሎጂ እጥረት፣ በባህላዊ እና ማህበራዊ ተፅኖዎች ምክንያት አኗኗራቸው ፈታኝና ውስብስብ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ችግሮቹን ውስብስብ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ደግሞ ሴቶቹ በሥራ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ ግንኙነቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ከአለፉት ጊዜያት የተወሰነ ለውጥ ቢኖርም ችግሩ አሁንም ድረስ የዘለቀ መሆኑ ነው፡፡ የወረዳዋ ሴቶች በልጅነት መዳር፣ የትምህርት ዕድል ከወንዶች እኩል አለማግኘት፣ የእርግዝና መቆጣጠሪያ በወንዶች ፍላጎት መሆን እና የቤት ውስጥና የውጪ ሥራዎች ጫና መኖር ኑሮአቸውን ፈታኝ ከአደረጉት ችግሮች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በወረዳዋ የቤት፣ የሃብት፣ አደባባይ የመዋል የመነገድ፣ የማዘዝ እና የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው በአብዛኛው ለወንዶቹ ነው፡፡ ይህን ማህበራዊ አደረጃጀት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሴቶች ጭምር አምነው የተቀበሉት ስርዓት ነው፡፡ ስለሆነም የሴቶቹ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ አደረጃጀት በወንዶች እጅ የወደቀ መሆኑ በጥናቱ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በወፍጮ አውድ ላይ የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን በመተንተን የአካባቢው ነዋሪ ሴቶች የሚወዱትን፣ የሚጠሉትን፣ የይወታቸውን ውጣ ውረድ እና የኑሮ ዘይቤአቸው ምን እንደሚመስል አሳይቷል፡፡ እንዲሁም የወፍጮ ቃል ግጥሞች ለማን፣ለምን እና መቼ የከወናሉ ለሚሉት የምርምር ጥቄያቄዎች መልስ አስገኝቷል፡፡

## ይሁንታ

ጥናቱ በእብናት ወረዳ በወፍጮ አውድ ላይ የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞች ትንተና በመስጠት የተጠና ሲሆን በጥናቱ ግኝት ላይ ትኩረት አድርጌ ቢስተካከሉ ይበጃል ያልኳቸውን ነጥቦች አነሳለሁ፡፡

የእብናት ወረዳ ነዋሪ ሴቶች በሥራ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ ግንኙነቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ሚዛናዊ ተሳትፎ የአላገኙ በመሆኑ የቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ የስራ ጫና እንደሚበዙባቸው ጥናቱ በግኝቱ ጠቁሟል፡፡ ይህም በወረዳው ቀድሞ የተሰራ ስራ ቢኖርም እንኳ አፈጻጸሙ ላይ የሚቀር ነገር ያለ መሆኑን ማወቅ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ተጽኖ ለማቃለል እና ከወንዶች ጋር እኩል ማሰለፍ ይቻል ዘንድ ከዚህ ጥናት በመነሳት የሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በእነዚህ ማህበረሰቦች ላይ የተሻለ ስራ መስራት አለባቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡

የወረዳዋ ነዋሪ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸው አመለካከት ይስተካከል ዘንድ መንግስታዊ አካላት ከሃይማኖት አባቶች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከአባወራዎችና ከሴቶች ጋር ውይይት በማድረግ ያመለካከት ለውጥ ስራ ቢሰራ መልካም ነው፡፡ በዋናነት የእብናት ወረዳ አስተዳደር፣ ወጣቶችና ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣ የደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዚህች ወረዳ ያሉ ሴቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ መልካም ነው እላለሁ፡፡

እንደ እብናት ወረዳ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ለመስከኛ ተፅኖ ቢኖረውም እንኳ ነዋሪዎቹ ሕዝቦች እንግዳ በመቀበልና መረጃ በመስጠት የሚመሰገኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ችግሮቹን እንዳሉ አውቀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በእንደነዚህ ያሉ ቦታዎችና ሕዝቦች ላይ ጥናቶች ቢሰሩ ከላይ የተነሱት ችግሮች ሊቃለሉ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ህዝብ አዳም ገላ፡፡ ‹‹የደጀን ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ይዘታዊ ትንተና›› የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1986 ዓ.ም፡፡

ሮማን ገብረ አምላክ፡፡ ‹‹የአድዋ አውራጃ የስራ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ቀለመ ወርቅ ተክሌ፡፡ ‹‹የሀድያ ሴቶች የስራ ላይ ዘፈኖች ትንተና፣›› የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የአማርኛ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2004 ዓ.ም፡፡

ብርሃኑ አሳየ፡፡ ‹‹የባንጃና በአንካሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊኛ የሚያዜሟቸው የሥራ ላይ ዘፈኖች ጭብጥ ገለጻና ትንተና፣››የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999 ዓ.ም፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ ‹‹የስነቃል ምንነት፣ ዘውጐችና አተናተን፣›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሰነ ጽሑፍ ክፍል 1995 ዓ.ም፡፡

አመነ ወርቁ፡፡ ‹‹በቸኻ አካባቢ የሴች የስራ ላይ ግጥሞች የይዘት ትንተና፣›› የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1993 ዓ.ም፡፡

አቢይ ጌታሁን፡፡ ‹‹በመስቃን ብሔረሰብ የሴቶች ማህበር /ዳዶ/ ክዋኔና በክዋኔው ወቅት የሚቀርቡ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1993 ዓ.ም፡፡

ዘሀራ ሰይድ፡፡ ‹‹የደሴ ዙሪያ ሴቶች የስራ ላይ ግጥም ይዘት ትንተና፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ ጽሑፍ መሰረታውያን አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት 1992 ዓ.ም፡፡

የኔአለም አረዶ፡፡ ‹‹በጥዩ አካባቢ የሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ይዘት ትንተና፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997 ዓ.ም፡፡

ያዜ ወርቁ፡፡ ‹‹የደንቢያ አውራጃ የስራ ላይ ዘፈኖች ይዘት ትንተና፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1984 ዓ.ም፡፡

ደመቀ ቢያዝን፡፡ ‹‹የሙቀጫ ግጥሞች በሁለት እጁ እነሴ ወረዳ፣››የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ዲማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1997 ዓ.ም፡፡

ድርቤ ቀንዓ፡፡ ‹‹በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ጭሮ ወረዳ አካባቢ የድኮና ሾብዶ ዘፈን ክዋኔና ግጥሞች ይዘት ትንተና፣››የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የስነ ቃል መምሪያ፣ አዲስ አበባ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991፡፡

Bascom,William R.''Four functions of Folklore''. Hand Book of American Folklore.(ed) Richard M. Dorson;Bloomington: Indiyana University Press 1965.

Bauman,Richard. Verbal Arts as Performance.Long Grove Il; Wave Land Press, 1977.

…….Towards New Perspectives in Folklore. Austt in and London; Texas University Press 1987.

........Cultural Performance and Popular Entertainments.New York: Oxford University press 1992.

Ben Amos, Dan. Folklore In context. New Delhi; Madras South Asian Publishiers,1982.

Dorson M, Richard (Ed) Folklore and Folk Life; An introduction Chicago: University press, 1972.

Fekade, Azeze.Unheard voices Drought, Famine and God in Ethiopian Oral Poetry. Addis Ababa University Press, 1998.

........... "The State of Oral Literature research in Ethiopia;" Journal of Ethiopian studies JES Vl. 34.1 2001.

Fetterman, David. Ethnography Applied Social Research Methods Series Volume 17, London; SAGE Publications Inc: 998.

Finnegan, Rut. Oral Literature in Africa. Nairobi: Oxford University Press 1970.

...........Oral Poetry its nature significance and social context. Cambridge: University Press, 1977.

........... Oral Traditions and the Verbal Arts. A Guide to Research practices, London; Alan Barnard and Anthony Good (Academic press). 1992.

Goldstien, Kenneth "Ridding Tradtions in North Eastern Scotland;" Journal of American Folklore;. 76: 330-336; 1963.

..............A Guide for Field Workers in Folklore. Pennsyuania:Hatboro, Folklore Associates, Inc:1964.

Gomm,Roger. Social Research Methodology A Critical Introduction. Published by Palgrave MacMillan; Printed and bound in Great Britian Cromwell Press, 2008.

Gray David. Doing Research in the Real world.London:SAGE Publication,Thousands Oaks New Delhi 2004.

Jackson, Bruce. Field Work. Urban and Chicago ILLINOS Press; 1987.

Mccormick, and White; K.K. (eds)"Folklore". An Encyclopedia of Beliefs Custms, Tales, Music and Art," 2011: 973-980.

Okpewho, Isidore. African Oral Literature. Back Grounds Character and Continuity.Bloomington: Indian University Press ,1992.

Orign, Elliot. "Three functions of Foklore." Traidtional Functionalism as in Folklore . The journal of American Folkore. 1976: 67-80.

Philip M. Peek, and Kwsi Yankah (eds), Dan, Ben Amos; Ruth Finnegan (Board of Editorial consultants) African Folklore Encyclopedia. New York; London Published, 2004.

Punch, Keith. Introduction to Social Research. Quantitative and Qualitative Approaches. London: SAGE publication Thousand Oaks New Delhi: 2004.

Shoemaker, George. H. The Emergence fo Folklore in Every day Life. A Field Guide and Source Book,1990.

Sims M.C and Martihe M Stephen. Living Folklore. An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan:Utah state University Press. 2005.

## አባሪ አንድ፡-ሀ/ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ፣ቁ | ስም | ፆታ | ሃይማኖት | ዕድሜ | አድራሻ | ሥራ | የት/ ደረጃ | መረጃ የተሰበሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ቀበሌ | | | |
| 1 | ወ/ሮ ማሚት እሸቱ | ሴ | ኦርቶዶክስ | 38 | አጃ ዘቀልሞቃ | የቤት እመ ቤት | የለ ም | ሰኞ-06-05-05 |
| 2 | ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ጠጋው | ” | ” | 55 | ” | ” | ” | ሰኞ-06-05-05 |
| 3 | ወ/ሮ ረህመት መኩ | ” | ሙስሊም | 34 | አዲያ ቁርቋራ | ” | ” | ረቡዕ-29-05-05 |
| 4 | ወ/ሮ በለጥ ሞላ | ” | ኦርቶዶክስ | 55 | ” | ” | ” | ረቡዕ-08-05-05 |
| 5 | ወ/ሮ ባነቻለም አየነው | ” | ” | 42 | መና መ/ዓለም | ” | ” | ሐሙስ-16-05-05 |
| 6 | ወ/ሮ ታከለይ መኮነን | ” | ” | 60 | አዲያ ቁርቋራ | ” | ” | ረቡዕ-08-05-05 |
| 7 | ወ/ሮ ነጠሩ አላዜ | ” | ” | 60 | ” | ” | ” | ሐሙስ-09-05-05 |
| 8 | ወ/ሮ አስረበብ አለቤ | ” | ” | 52 | ግብፃዊት | ” | ” | ሰኞ-20-05-05 |
| 9 | ወ/ሮ አስካል ቀለሙ | ” | ” | 60 | አጃ ዘቀልሞቃ | ” | ” | ሰኞ-06-05-05 |
| 10 | ወ/ሮ አንሻዬ ደሴ | ” | ሙስሊም | 62 | ቁርቋራ | ” | ” | አርብ-10-05-05 |
| 11 | ወ/ሮ እርጐዬ ለገሰ | ” | ኦርቶዶክስ | 31 | መና መ/ዓለም | ” | 3ኛ | ማክሰኞ-14-05-05 |
| 12 | ወ/ሮ እናት ንጋቱ | ” | ” | 38 | አጊሳ | ” | የለ ም | አርብ-17-05-05 |
| 13 | ወ/ሮ እናንዬ አበበ | ” | ” | 17 | አዲያ | ” | ” | 07-05-05 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | እማሆይ ካባ አሻግሬ | " | " | 60 | ግብፃዊት | እማ ሆይ | " | ረቡዕ-22-05-05 |
| 15 | ወ/ሮ ካባ እንደሻው | " | " | 55 | አጊሳ | የቤት እመ ቤት | " | አርብ-17-05-05 |
| 16 | ተማሪ ክቴ ደመቀ | " | " | 18 | አዲያ | ተማ ሪ | 5ኛ | ማክሰኞ-07-05-05 |
| 17 | ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ | " | " | 38 | ቁርቋራ አዲያ | የቤት እመ ቤት | 4ኛ | ረቡዕ-08-05-05 |
| 18 | ወ/ሮ ዘቦ አየለ | " | " | 33 | መና መ/ዓለም | " | የለ ም | ረቡዕ-15-05-05 |
| 19 | ወ/ሮ ደብሬ አለሜ | " | " | 17 | ደብር ተ/ሃይማኖት | " | " | ሰኞ-27-05-05 |
| 20 | ወ/ሮ ፋሲካ ሞላ | " | " | 57 | መና መ/ዓለም | " | " | ማክሰኞ-14-05-05 |
| 21 | ወ/ሮ ፍቅሬ አለሙ | " | " | 19 | ደብር ተ/ሃይማኖት | " | " | ሰኞ-27-05-05 |

## አባሪ አንድ ለ/ አጋዥ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ሃይማኖት | ዕድሜ | አድራሻ ቀበሌ | ሥራ | የት/ ደረጃ | መረጃ የተሰበሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | *አቶ ለምለሙ መንግስቱ | ወ | ኦርቶዶክስ | 52 | 01 ቀበሌ | የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መ ምሪያ የባህል እሴቶች እና ተቋማት ጥናት ልማት አጠቃቀም የስራ ሒደት አስተባባሪ | ቢ.ኤ ዲግሪ | ረቡዕ-06-06-05 |
| 2 | አቶ ለማ ጠዳ | ” | ” | 46 | መና መ/አለም | አርሶ አደር | የለም | ማክሰኞ-14-05–05 |
| 3 | ተማሪ መልካሜ በሪሁን | ሴ | ” | 18 | አዲያ | ተማሪ | 5ኛ | ሀሙስ-09-05-05 |
| 4 | ወ/ሮ መሪየም አብደላ | ” | ሙስሊም | 27 | ” | የቤት እመቤት | የለም | ቅዳሜ-25-05-05 |
| 5 | አቶ ሞላ መንግስቱ | ወ | ኦርቶዶክስ | 72 | መና ዲቀ | አርሶ አደር | ” | ረቡዕ-15-05-05 |
| 6 | አቶ በቃሉ ዋለ | ” | ” | 27 | እብናት 02 | የመ.ኮ.ጉ. ጽ/ቤት ህዝብ ግንኙነት ባለሙያ | ቢ. ኤ ዲግሪ | ሀሙስ-02-05-05 |
| 7 | ወ/ሮ ቦሴ ውብሸት | ሴ | ” | 30 | መና ዲቀ | የቤት እመቤት | የለም | ረቡዕ15-05-05 |
| 8 | አቶ ተስፋው ቀለሙ | ወ | ” | 56 | አጃ | አርሶ አደር | ” | 05/05/05 |
| 9 | አቶ ተሻሜ አከለ | ” | ” | 47 | አዲያ ቁርቋራ | አርሶ አደር | ” | እሁድ/12/05/05 |
| 10 | ወ/ሮ አለምነሽ | ሴ | ” | 47 | ግብየዊት | የቤት | ” | ሰኞ/20-05- |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ምህረት | | | | | እመቤት | | 05 |
| 11 | አቶ አለነ ገደፋው | ” | ” | 58 | እብናት 02 | የስርዓተ ፆታ እና ወጣቶች የስራ ሒደት አስተባባሪ | ዲፕ ሎማ | ረቡዕ-02-05-05 |
| 12 | ወ/ሮ አረጉ እሸቱ | ሴ | ” | 35 | አጃ | የቤት እመቤት | የለም | ሰኞ-06-05-05 |
| 13 | አቶ አረጋ አበራ | ወ | ” | 38 | አዲያ ቁርቋራ | የቀበሌ አስተዳዳሪ | 3ኛ | አርብ-10-05-05 |
| 14 | አቶ አስቻለው ፈጠነ | ” | ” | 26 | እብናት 02 | የባህል ልማት | ቢ.ኤ ዲግሪ | አርብ-03-05-05 |
| 15 | አቶ አሻግሬ ገሳዬ | ” | ” | 81 | አዲያ ቁርቋራ | አርሶ አደር | የለም | እሁድ-12-05-05 |
| 16 | ተማሪ አበባ አዳነ | ሴ | ” | 16 | ግብየዊት | ተማሪ | 4ኛ | ረቡዕ-22-05-05 |
| 17 | ወ/ሮ አበብ ጌታው | ” | ሙስሊም | 32 | አዲያ ቁርቋራ | የቤት እመቤት | የለም | ረቡዕ-08-05-05 |
| 18 | አቶ አብቦ ሹመት | ወ | ኦርቶዶክስ | 38 | እብናት 02 | የእብናት ወረዳ አስተዳዳር ጽ/ቤት ኃላፊ | ቢ.ኤ ዲግሪ | አርብ-03-05-05 |
| 19 | ወ/ሮ አንችንአሉ መስፍን | ሴ | ” | 42 | አጊሳ | የቤት እመቤት | የለም | ሀሙስ-16-05-05 |
| 20 | ወ/ሮ አዱኛዬ ተሾመ | ” | ” | 44 | ” መናዲቅ | ” | ” | ረቡዕ-15-05-05 |
| 21 | ወ/ሮ ክርክም አዳነ | ” | ” | 55 | ” ግብየዊት | ” | ” | ረቡዕ-22-05-05 |
| 22 | ወ/ሪት ወርቂ ለገሰ | ሴ | ” | 30 | ” አዲያ ቁርቋራ | የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ | ሰርት ፊኬት | እሁድ-19-05-05 |
| 23 | ወ/ሮ ወይኒቱ መርሻ | ሴ | ” | 41 | ” | የቤት | የለም | እሁድ-19- |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | " | እመቤት | | 05-05 |
| 24 | አቶ ዋጋው አወቀ | ወ | " | 49 | " ግብፃዊት | አርሶ አደር | " | እሁድ-21-05-05 |
| 25 | ወ/ሮ ውብአገኝ ፍቃዶ | ሴ | " | 37 | " አጊሳ | የቤት እመቤት | " | አርብ-17-05-05 |
| 26 | ተማሪ ዘመናይ አያነው | " | " | 13 | " መናዲቅ | ተማሪ | 5ኛ | ረቡዕ-15-05-05 |
| 27 | ወ/ሮ የሻረግ ታፈስ | " | " | 40 | አጃ ዘቀልሞቃ | የቤት እመቤት | የለም | ሰኞ-0-05-05 |
| 28 | አቶ ደመቀ ውብት | ወ | " | 35 | አጊሳ | የአጊሳ ት/ቤት ዘበኛ | 9ኛ | አረብ-17-05-05 |
| 29 | ተማሪ ጊዜሽ አስማረ | " | " | 16 | " አጃ ዘቀልሞቃ | ተማሪ | 3ኛ | ማክሰኞ-07-05-05 |
| 30 | ተማሪ ጠጅ ደስታው | ሴ | " | 12 | " | ተማሪ | 2ኛ | ማክሰኞ-07-05-05 |
| 31 | አቶ ጥላሁን እንደሻ | ወ | " | 45 | አዲያቁርቋራ | አርሶ አደር | 4ኛ | እሁድ-19-05-05 |

* ወረዳ ደብረታቦር

## አባሪ አንድ ሐ/ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ሃይማኖት | እድሜ | አድራሻ | ስራ | የት/ደረጃ | የመረጃ ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሆነልኝ ደጀን | ወ | ኦርቶዶክስ | 55 | አዲያ | አርሶ አደር | የለም | 12/05/05 |
| 2 | አቶ ለገሰ አለሙ | ” | ” | 60 | ደብር | ” | ” | 21/05/05 |
| 3 | አቶ ሞላ ዘገዬ | ” | ” | 75 | አዲያ | ” | ” | 12/05/05 |
| 4 | አቶ ቡላድ አየለ | ” | ” | 57 | ግብጻዊት | ” | ” | 21/05/05 |
| 5 | ቄስ ተሾመ ነጋሽ | ” | ” | 48 | አዲያ | ቅዳሴ | ” | 19/05/05 |
| 6 | አቶ አለሜ ተገኘ | ” | ” | 77 | ደብር | ” | ” | 21/05/05 |
| 7 | አቶ አለቤ ጥሩነህ | ” | ” | 78 | ግብጻዊት | ” | ” | 21/05/05 |
| 8 | አቶ አረጋይ ድሌ | ” | ” | 42 | ቁርቋራ | ” | ” | 12/05/05 |
| 9 | ቄስ አሰፋ ይግዛው | ” | ” | 46 | ደብር | ቅዳሴ | ” | 21/05/05 |
| 10 | ወ/ሮ አበባ ፍስሀ | ሴ | ” | 39 | አዲያ | የቤት እመቤት | ” | 19/05/05 |
| 11 | ቄስ ወርቁ ገላዬ | ወ | ” | 40 | አዲያ | ቅዳሴ | 8ኛ | 19/05/05 |
| 12 | አቶ ወንድማገኝ ሞላ | ” | ” | 38 | ቁርቋራ | አርሶ አደር | የለም | 19/05/05 |
| 13 | አቶ ዋናው ደማም | ” | ” | 50 | ግብጻዊት | ” | ” | 21/05/05 |
| 14 | ወ/ሮ ዘርፌ ታደሰ | ሴ | ” | 55 | ቁርቋራ | የቤት እመቤት | ” | 12/05/05 |
| 15 | ወ/ሮ ዝይን አበጀ | ” | ” | 57 | ቁርቋራ | ” | ” | 12/05/05 |
| 16 | ቄስ ደረጀ አያናው | ወ | ” | 44 | አዲያ | ” | ” | 19/05/05 |

## አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ ሰጭዎች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች

## አባሪ ሁለት ሀ/ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች

1. 1.ያአቀነቀንሽው ቃል ግጥም ከአንቺ ህይወት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
2. በግጥሞቻችሁ ደጋግማችሁ የምታነሷቸው አቶ ሞላ ዘገዬ እና አቶ ስራው ታየን በምን ምክንያት ነው?
3. ትምህርት ለመማር ያልቻልሽው በምን ምክንያት ነው?
4. በኑሮሽ ውስጥ በጣም የሚያማርርሽ የትኛው ነው?
5. እህል እየፈጨሽ ስታቀነቅኒ (ስትዘፍኒ) ምን ይሰማሻል?
6. የወፍጮ ግጥሞቹን በሌላ ጊዜና ቦታ ታቀነቅኗቸው አላችሁ ወይ?
7. ቃል ግጥሞቹን ከማን እና እንዴት ተማራችኋቸው (አወቃችኋቸው)?
8. በግጥሞችሽ ውስጥ በብዛት የጥላቻና የንቀት ጉዳዮችን ታነሻለሽ፡፡ለምን?
9. ሴት መሆንን የሚያማርሩ ግጥሞችን የአቀነቀንሽው ከምን አኳያ ነው?
10. ፍቅር ብለሽ የአዜምሻቸው ግጥሞች በአብዛኛው ስሜት የሚነኩ ናቸው፡፡ ለምን?
11. የሰው ቤት እንጀራን እንዴት ትገልጭዋለሽ?
12. “መኔዎች” በምን ከሌላው ይለያሉ?
13. ስንት ጊዜ ባል አግብተሻል እንዴትስ ትገልጭዋለሽ?
14. የአቀነቀንሻቸው ግጥሞች የሚያነሷቸው ሃሳቦች አሁንም ድረስ የሚፈጸሙ ናቸው?
15. ጎባንን የሚመለከቱ ግጥሞች በብዛት አዚመሻል፡፡ ስለ ጎባን ምን የምታውቂው ነገር አለ?
16. 16.ልጅ ሁነሽ ልጅ በመውለድሽ እንደከፋሽ በግጥሙ ገልጸሻል፡፡ ለምን የእርግዝና መከላከያ አልተጠቀምሽም?
17. ለምን በመኪና ወፍጮ አታስፈጪም? እና
18. ወፍጮ የሚፈጭበት ጊዜያት በአብዛኛው መቼ ነው? የሚሉ ናቸው፡፡

## አባሪ ሁለት ለ/ ለአጋዥ መረጃ ሰጭዎች የተዘጋጁ መሪ ጥያቄዎች

1. የእብናት ወረዳ አጠቃላይ ዳራ ምን ይመስላል?
   1.1. የወረዳዋ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ምን ይመስላል ?
   1.2. የወረዳዋ የአየር ንብረት ምን ይመስላል?
   1.3. የወረዳዋ አሰያየም እና የሕዝብ ስርጭት ምን ይመስላል?
   1.4. የወረዳዋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አደረጃጀት ምን ይመስላል?
2. ከወረዳዋ ቀበሌዎች በብዛት ወፍጮ እየተፈጨባቸው ያሉት ቦታዎች የትኞቹ ናቸው?
3. በወፍጮ ላይ የሚዜሙት ቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ?
4. የወፍጮ ላይ ዘፈኖች የሴቶቹን ጉዳይ ብቻ ነው የወንዶችንም ጭምር ያነሳሉ?
5. የወፍጮ ላይ ቃል ግጥሞች ምን ምን ጠቀሜታ አላቸው?
6. ለምን መቅረጸ ድምጽ እና እና ቪዲዮ ካሜራ ፈራሽ?
7. ሁል ጊዜ ነው ስለእናትሽ የምታቀነቅኝ? እናትን እንዴት ትገልጪታለሽ?
8. ለምን እና በምን ምክንያት ባሎቻችሁን ትፈታላችሁ?

## አባሪ ሁለት ሐ/ ለቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የቀረቡ መሪ ጥያቄዎች

1. “ዋርካ” የሚለው ቃል በግብጻዊት እና ደብር ቀበሌዎች የምን ተምሳሌት ነው?
2. የበረሃ ሎሚ ምን ትርጉም አለው? ለምን መድሃኒት ይውላል? ከእናት ጋርስ እንዴት ይመሳሰላል?
3. በእናንተ ቀበሌ ሊወደስና ሊመሰገን የሚችል ሰው ምን ምን ተግባራትን የፈጸመ ነው?
4. በወፍጮ ስራ ላይ የሚያቀነቅኑት ሴቶች ናቸው። ይሁን እንጅ ለጥናቱ መረጃ እንዲሰጡ ቅድሚያ የሚጠየቁ ወንዶች ናቸው። ለምን?
5. ሴቶች በወፍጮ ላይ የሚያዜሟቸው ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ?
6. ደብር ተክለ ሃይማኖት ከሌሎቹ ቀበሌዎች በምን ይለያል?
7. አቶ ለገሰ አለሙ እና አቶ ንጋቱ መኮነን በአዲያ እና ባሻዬ አቦ ምን መገለጫ አላቸው?
8. በእናንተ ቀበሌ ከማህበር፣ ከእድር እና ከመሳሰሉ ጉዳዮች የምትለዩአቸው ምን ጥፋት የተገኘባቸውን ሰዎች ነው?
9. በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው የስራ ክፍፍል ምን ይመስላል0?

## አባሪ ሶስት - ከመስክ የተሰበሰቡ ቃልግጥሞች

### 1.ምሬትን የሚገልጹ ቃል ግጥሞች

#### 1.1 የፍጮ ስራን የሚመለከቱና የሚያማርሩ

1. እጄን ለብር አምባር ስመኘው ስመኘው
እግዜር ክፉ ሰው ነው ከወፍጮ አቆራኘው

2. ወፈጮው ውረድውረድ ቋቱ ሙላ ሙላ
እንደልብ አይገኝ የሰው ቤት እንጀራ

3. ዱር ውዬ ስመጣ በላኝ ረማጫው
ከቤቴ ስገባ ግርድፍ ስልቅ ወፍጮው
ከእንግዲህ አልሰላም መሄዴ ነው ትቸው

4. ወፍጮው ውረድ ውረድ ቋቱ ሙላ ሙላ
የተገመገመው የሰው ቤት እንጀራ
ከሰው ቤት እንጀራ ከተገመገመው
የናት ቤት ይሻላል ከወጭት ያደረው

5. እባክህ ጌታዬ ጤናዬን ስጠኝ
እንድፈጭ እንዳርም ሰው እነዲወደኝ

6. እሜቴ ይሙቱ አስቸግረውኛል
ቶሎ ቶሎ ስፈጭ ሸረከትሽ ይሉኛል
አልሜ ስፈጨው ከምን ዋልሽ ይሉኛል
የዘንድሮን እንጂ ከርሞን ያገኙኛል

7. እሽም ይላል ወፍጮ ይከተላል መጅ
የወፍ አዘንተኛ የድንቢጥ አርጋጅ

8. ከጤፍ ጥሬ ብሶ ተከክቶለት
እግዚአብሔር አይበለው አንተን ለሁለት

9. እኔማ ዘንድሮ ምን ያለሆንኩት አለኝ
አለሁሽ እያለ ከወፍጮ ሲያውለኝ

10. ሊምን ወዲያ ማዶ ቡንኝ ዘርተሽኝ
ከጠባብ አውድማ አስወቅተሽኝ
ሚስትህ አበጥራ ገረድህ ፈጭታኝ
እናትህ አንጉታ ላንተ ሰጠችኝ
በለስላሳ ጥርስህ አንተ በልተሽኝ
እንዴት ሰው ጉድ ባለ ከሆድህ ስገኝ

11.እቴ የእሜቴ ልጅ ባለ ሁለት ቁንጮ
የሙያሽን ነገር አየሁት በወፍጮ

12.ከወፍጮው ወርጄ ከመደቆሻው
ከመደቡ ትኂን ከላይ ጥቅርሻው
ይሄ ነው ወይ ቀኑ የመጨረሻው

13.ሰው በእጁ አልገደልኩኝ
በጥርሴ አልገደልኩኝ
ሰው በአይኔ አልገደልኩኝ
እድሌ ሆነና ለወፍጮ ታደልኩኝ

14. አወራ ቢዘሩት ተመልሶ አወራ
አንቺ ከወፈጮ ስር ባልሽ ከእኔ ጋራ

15. የማሽላ ወፍጮ የማይልመውን
እንዳመሌ ልብላ ያን ዘንጋዳውን

16. ፈጭቼ ፈጭቼ ቋቱን ሞልቻለሁ
ብቅ በል ያገር ልጅ ከእንግዲህ ሙቻለሁ

17. እሽም ይላል ወፍጮ ይከተላል መጅ
ልጅ ከወለዱ አይቀር እንዳንተ ነው እንጂ

18. ውራንታ እህል ፈጭተሽ ውራንታ ደፍተሽ
ከዓመት እኩሌታ መች ትደርሻለሽ

19. ባሰጣው ሰው አየው ብፈጨው ገረጣ
ባቦካው ቀጠነ ብጋገረው ሳሳ
ብበላው ብበላው ጕኔም አልተነሳ

20. ፈጭተው ካላኖሩ ከዱቄት እቃው
ጉባኤ ይሙቱ አይለምድም ባለዎ

21. ስፈጭም አዝዬ ስበላም አዝዬ
ከመሞት መሰንበት ይሻለኛል ብዬ

22. እንደ ሳሊ ጊደር መልኳን አሳምራ
ወፍጮዋን አትወቅረው ቧኗ እንጀራ አይበላ

23. ተቀብተሽ ተኩለሽ ብትቁለጨለጪ
ድስት አታንጋልሊ እቢላ አትፈጪ

24. እንደዚህ ነው እንጂ የቤት አያያዙ
አንድ ቋት ሳይፈጩ እንድ ክር ሳይመዙ

25. በእርሻው የበረታ እርሻውን ያወቀ
ወፍጮ እንዳጎራ መስከረም ዘለቀ

26. እግሬን ረማጫ እጄን ወፍጮ በላኝ
የቁርቋራ ኑሮ እንደምን አስጠላኝ

27. ባሏ ጓሮ ያርሳል ሚስቱ አርጎዬ ፈጭታ
አይጣል አይድረስ ነው እንዲህ ያል ጨዋታ

28. ሰው ያለአማኑኤል ሸቀጥ ያለአጣሪ
አውጣኝ ከዚህ ወፍጮ እባክህ ፈጣሪ

29. የሸርፋ ባለቤት የጠገት ባለቤት ነው አሉ ባልሽ
ከግርድፉ ወፍጮ ከስልቁ ወፍጮ እስኪ ተሙነሽነሽ

30. የባላባት ልጅ ናት የባለመሬት
አትፈጭም ወፍጮ አትይዝም እንዝርት

31. የአሽከሬቱ እናቷ ውጪ ተጠየቂ
አትፈጭም ልጅሽ አትለቅም ልቃቂ

32. አራሽ አንደፋራሽ ዝናብ የማይፈራ
ሌቱን ሙሉ ያድራል ወፍጮው እንዳጐራ

33. ከሰው ተራ ወጣሁ አልስቅ አላወጋ
አንተን ሚሉ መልካም አንተን ሚሉ ሸጋ
እንደ ድሃ ወፍጮ ጉሮሮህ ይዘጋ

34. መፍጨቱንስ ፍጪው ማቡካቱንስ አቡኪው
ይወጣ ከሆነ እስኪ እንጀራ ጋግሪው

35. ከወፍጮ ስር ውዬ ከወፍጮ አድራለሁ
የእግዜር ስጦታ ነው ከየት እደርሳለሁ

36. ወፈጮውን አቁተሽ ሁልጊዜ ንትርክ
እኔስ እሄዳለሁ ከአለቃ ምኒልክ

37. ማእረጉን አስትቶ መፍጨት ካማረሽ
አቡዬ ጻዲቁ ቅባይዚ ያግባሽ

38. እድያ ነው እንጂ ሰው አይወቀስም
ሚስትህ ልትፈጭ ቀርቶ ተልባ አትደቁስም

39. እንደ ወፍጮ ከፉ እንደ እንጀራ መልካም
ከፉውን ካልወጡ ደስታ የለም ለካም

40. ገና ጨቅላ ሳለሁ እናቴ በጣለሺኝ
ለሀብታሙ ቤት ወፍጮ ወልደሽ የሰጠሽኝ

41. ከወፍጮ እግር ውለሽ ከወፍጮው እደሪ
ለፍተሽ ነይ ብሎሻል ሲሰራሽ ፈጣሪ

42. አንተ ወፍጮ ውረድ ውጣ አንተ ሙቀጫ
እህ ልበልበት ከባሌ ግልምጫ

43. እጄን ደነዘዘኝ እግሬን ቆረጠመኝ
ኧረ ከዚህ ወፍጮ እግዜር ይፋረደኝ

44. ዱከትም አላረግ ድሪም አልቦ አላስር ጥርሴም አይገለጥ
ደግሞ ለዱቄቱ ምን ያስፈልጋል ጌጥ

45. አንቺ ሳሙን በቅሎ ያለሽው ከጋጡ
አንተም አውራ ዶሮ ያለኸው ከቆጡ
ቀስቅሰኝ እንድፈጭ ባሌ እንዳይቆጡ

46. ወርቅ አለም አሻግሬ ሃምታሙ እድላሙ
ሲደልቅ ያመሻል ወፍጮው እንዳታሞ

47. እንግዲህ ጀመረሽ ሊያፎሻሽግሽ
እንዝርቱ እና ወፍጮው አሻግሮ ሲያይሽ

48. እስቲ ልነሳና ወፍጮየን ልቋት
ምን ያስቀምጠኛል እንደ ሞላለት

49. ቢወቅሩት አይሰላ ወፍጮየ ነኳላ
ባሌ መናጢ ነው ራቱን ካልበላ

50. ወፍጮው ስላ ስላ ቋቱ ሙላ ሙላ
እንደሁ አይገኝም የሰው ቤት እንጀራ

51. መጁ የባህር ልጅ እናቱ ድንጉር
እህል ይፈጫለኝ ካገኘ ልባም

52. ወፍጮው ስላ ስላ ቋቱ ሙላ ሙላ
እንዳጌጡ መኖር አይገኝምና

53. የሴቷ ወፍጮ ታስታውቃለች
ሰኞ እስኪመጣ ትቸኩላለች

54. ያረሰ ሰው መልካም እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳጕራ መስከረም ዘለቀ

55. በሻሽ መቀነቷ ሸበክ አርጋ ታጥቃ
ወፍጮዋ ስድ ነው ያህላል ማጎቃ

56. ስፈጨው አድሬ ሲነጋ እወቅጣለሁ
የኑሮውን ጣጣ እታገለዋለሁ

57. ወፍጮዬን ወቅሬ አበጃጅቻለሁ
ሌሊት ዶሮ ጩኸት እፈጭባታለሁ

## 1.2 ሴት በመሆን የሚደርሱ ምሬቶችን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

58. አንተ ላይ ደመና አንተ ላይ ሰማይ
የልጃገረድ ቀን አልተገኘም ወይ

59. ምነው በጨለማው ምነው በሌሊቱ
ጅብ አይበላሽም ወይ ልጃገረዲቱ

60. በሰባራ ቪላ የቀናል በርበሬ
አንተም ወደ ቤትህ እኔም ወደ አገሬ

61. የዋርካ ጉልጭማ አይነቃነቅም
ጀግና ትወልዳለይ ሴትም አትናቅም

62. እሳት ሲያዳፍኑት ይመስላል የጠፋ
ጅል መስየዋለሁ አንገቴን ብደፋ

63. አንገቴን ደፍቼ ከጉልበቴ ላይ
ቀን የሚያሳልፍ ሰው ጅል የባላል ወይ

64. አንጎራጓሪ ናት አመሏ ነው ሴት
ልጇ ሲያለቅስባት ባሏ ሲቆጣት

65. እናቴ በድሌ ምን ያሳዝንሻል
ሴትነቴን እንጂ ሀብቴንን ወልደሻል

66. አህያ ተጭና አትንከባለልም
የሰጎን እንቁላል ወድቆ አይሰበርም
እንዝርት ያለወልቆ አይሽከረከርም
ሴትነት ነው እንጂ መልክ አያሳድርም

67. ልጅነቴ መልካም ልጅ መውለዴ ክፉ
የመናት እመጫት እያሉኝ አለፉ

68. የእኔ ባልንጀሮች እንደኔ ያልሆኑ
አጅባር ተማሪ ቤት ደብረ ታቦር አሉ

1.3 በልጅነት መዳርንና የዕድልን እጣ ፈንታ የሚያማርሩ ቃል ግጥሞች

69. ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ ጨርቁ ወጣ
ከእንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ

70. እንዴት ያደርጉታል የሆድን ህመም
ማጭድ አይገባበት በጅ አይታረም

71. አስለምደዋለሁ እግሬን ያለጫማ
እንዳጌጡ መኖር አይገኝምና

72. በል እንባዬ ውረድ ደረቴን አልብሰው
ጊዜ ያመጣውን ጊዜ እስኪመልሰው

73. ከትልቁ ዋርካ ከግንቡ ደርሼ
ያለ እድል አይሆንም መጣሁ ተመልሼ

74. እንዲህ ወደማታ ደም እየነሰረኝ
ድሮ ባልወለድ ነበር የሚሻለኝ

75. እህህ ነው እንጂ ያከሳው ደረቴን
መች ሳልበላ አድራለሁ አንድ እንጀራ ራቴን

76. ቀን ይወጣል ብዬ ሽቅብ ሽቅብ ሳይ
ቀኑ እንደጨለመ መቅረቱ ነው ወይ

77. ከአንተ ወዲያ ሽጋ ከእኔ ወዲያ ልጅ
እድያችን ሆኖ ባይገጥም ነው እንጂ

78. በል ተወው በል ተወው በል ተወው አይጎዳም
አንተ የሚሉህ ጭምት እኔ እሚሉ ሆዳም

79. አስመራን ዘነበው ደሴን ጉም ዋጠው
አሳብና መንገድ ማለቂያም የለው

80. ክፉና በጎውን መልሶ ከልሶ
መምጣት መልካም ነበር የልብን አድርሶ

81. አሙኝ አሙኝና እንጨት ሰበሩኝ
እንጨት ሰበሩና በጉሮ ጣሉኝ
ከጉሮው አንስተው እሳት ጨመሩኝ
እሳት ጨመሩና አመድ አረጉኝ
አመድ አረጉና በቅርጫት ዛቁኝ
በቅርጫት ዛቁና በጉሮ ደፉኝ
ኧረ ዋሽ አህያ እንዳትቅሚኝ
ምን አልባት ሰው ብሆን ቀን ቢወጣልኝ

82. አለም ተዛዋሪ እንደገንቦ ጠጅ
ያገኘው ሲደሰት ያጣው ሲበሳጭ

83. አላመሰገኑኝ አላሉኝ ደህና ሰው
የበሮ ባር ውሀ ጉልበቴን ጨረሰው

84. ባወርደው ቢቀለኝ የተሸከምኩት
ቢናገር አይጠቅም ሰው ያለወራት

85. እሄዳለሁ እንጂ ምነ አለመሄዴ
ክፉና በጎውን እያወቀው ሆዴ
የኔ እናት አባቶይ የገደል ምሳና
እኔ ነኝ ልጅቱ እድሌ የጠና

86. አንጀቴና ሆዴ ተጣልተውብኝ
አንተም ተው አንተም ተው እንዳልላቸው
አንጀቴም አንጀቴ ሆዴም ሆዴ ነው

87. ምን ዓይነት አሞራ ከዛፍ ይሞገታል
ከሚወዱት ጋራ ማን ሲኖር አይቶታል

88. በል አንተ ደህና ሁን እኔም ደህና ልሁን
እንገናኛለን እድል ያለ እንደሆን

89. እረጅም መቀነት ሳይስቡት ይጠብቃል
አትሸበር ሆዴ መድኃኔአለም ያውቃል

90. ተመስገን ጌታዬ አላማርርህም
ይብስ ታመጣለህ አንተ አይቸግርህም

91. ኧረ ተወኝ ልቤ እንዳልኩህ እደር
ይችን ሁለት ሰንበት ይችን ሁለት ወር

92. እንዲህ ብዬ ብዬ የቀረሁ እንደሆን
የጓሮ ማሽላ ወፍ የበላው መሆን

93. እናቴ በድሌ ምን ያሳዝንሻል
ልጅነቴን እንጂ ሀብቴንን ወልደሻል

94. እሄድ እሄድና እላለሁ እንቁም
ያሳዝናል እንጂ ይህስ አያስቅም

95. ነገር ከላይ ከታች እያመላለሱ እያቅጠፈጠፉ
ውሻና ቀበሮ አርገውን አረፉ

96. ነጋዴነሽ አሉኝ እኔስ አልነግድም
ወረቱ ካለቀ ሰው አይወደድም

97. እድሌ ነው እንጂ የተልከሰከሰው
በሰባራ ምጣድ በገል የታመሰው

98. ወይ እድሌን ባርከው ወይ ሞቴን በልከው
ሆዴ ተቀደደ ሲነደኝ የማከው

99. የአህያ ልጅ በቅሎ በብር ተሸልማ
እድሌ ነው እንጂ እኔ ሰው አላማ

100. እድሌን አየኒት አመድ ስትነፋ
እኔ ምን ጨነቀኝ አብረን ልንለፋ

101. የሰቀላው ቤቴ ዝናብ አፈሰሰ
ከማገሩ ይሆን ከሳሩ ያነሰ
ከማገሩም አይደል ሳሩም አላነሰ
ከመቋጠሪያው ላይ ከውሉ ፈረሰ

102. እግሬም ግፋ ግፋ አይኔም ሰው ለመድ
እራሱን ካልቻሉት አይወድም ዘመድ

103. ወንጭፍ ተጠቅልሎ ይውላል ከማማ
ከአገር ሆድ ይሰፋል ላስቻለው ሰውማ

104. አባታለም እየ ወልደህ የጠላኸኝ
ሰው ያልበላው ቅጠል ስበላ አየኸኝ

105. ባጥፊው ደነዘዘኝ ምላሴን እንደ እግር
ወገን አይደለም ወይ የልብ የሚያናግር

106. ለሊት ተነስቼ ስፈጨው አድራለሁ
ጧትም ተነስቼ ስወቅጥ እውላለሁ
ቀንመ ተነስቼ ስወቅጥ እውላለሁ
እድሜዬን በሰው ቤት እጨርሰዋለሁ

107. ከውሃ ቢዶሉት አይሚሟም ብረት
አይመሰገንም የድሃ ጉልበት

108. ያለ ዕድሜ ጋብቻ ያለ ገንዘብ ኑሮ
በጨለማ ጉዞ ዝናብ ተጨምሮ

109. የገብስ እንጀራና ጥቁር ሰው አልወድም
እየተናነቀ ከጉሮሮ አይወርድም

110. አጭር ባል አግብቼ የሚሃል ሽንኩርት
ወለል ብሎ ጠፋ ሳይገባ ከቤት

111. ያባይ ጥቁር እንጨት ያብባል ያፈራል
ያለኩያት መውደድ እንዴት ያሳፍራል

112. ምድጃ ለምድጃ ይገፋል ወተት
ከቁመቱ ማጠር ያመሉ መክፋት

113. አረጀህ መሰለኝ ውቃቤ እራቀህ
አንተ ከእህል በቀር ሰው አይናፍቅህ

114. አገልግል ሰፍቼ መለጐሚያው ጭራ
ጐድ አይቼ መጣሁ አጭር ሰው ሲኮራ

115. የትንሽ ወጠጤ የዝምብ አራስ ነብር
እንደ አንተ ያለ ሰው ያባቴ አሽከር ነበር

116. እኔማ ዘንድሮ ምን ያለሆኩት አለኝ
ሳገኝ አላውቅበት ሳጣ ዘመድ የለኝ

117. አግኝቶ ያጣና ቀን የጐደለበት
ቢናገር ወዝ የለው ቢስቅ አያምርበት

118. ጓዜን ክውን ክውን እስካደርግላችሁ
ለምን ገፋ ገፋ ታደርጉኛላችሁ

2. ውዳሴን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

## 2.1.እናትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

119. አሞራ በሰማይ ትርገበገባለይ
እናት አለሚቱን ብላ ትሆናለይ

120. ጸሐይ በታች ወጥታ በላይ ትገባለይ
የእናት ሁለተኛ ከየት ትገኛለይ

121. እንጀራም ይበላል ከራራ መሳይ
ጨርቅም ይለበሳል አሮጌ መሳይ
እኔስ የምቀና እናት ያለው ሳይ

122. እናት አለም አልኳት ስሟን አሳንሼ
ዘጠኝ ወር አርግዛኝ ስጋዋን ለብሼ
ሶስተ ዓመት አጥብታኝ ክንዷን ተንተርሼ

123. የቁርቋራ ማርያም ቀስተ ደመናይቱ
በይ አንች ቁሚላት ለናታለሚቱ

124. አባይ ውሃ ሞልቶ ዳርዳሩ ይፈሳል
አሁን በምን መላ የእናት ሞት ይረሳል

125. እናት አለሚቱ ስደጂልኝ ጭፍቆ
ልበላውም አይደል ናፍቄ ነው እኮ

126 እበላለሁ ስጋ እጠጣለሁ ጠጅ
እናት አለሚቱ ትኑርልኝ እንጂ

127. እናት ውድማ ናት የተለቀለቀ
ቢበሉ ቢጠጡ አትልም አለቀ

128. ኧረ እናት ኧረ እናት ኧረ እናት ማሪቱ
በደረቷ ወተተ ብእጇ ማር ያላቱ

129. እናት አንዲት ሆና ለሰው አስቸገረይ
እንደ ቤተዘመድ ሰላሳ በሆነይ

130. ከሰው ቤት እንጀራ ከተገመገመው
የእናት ቤት ይሻላል ከወጭት ያደረው

131. አለት ለአለት ሲሄድ አገኘሁ መግላሊት
እናት አለሚቱ የራቤ መድኃኒት

132. እናት አለሚቱ ረሃቤን ተቆጪው
አንቺን ይፈራሻል ስትገላምጪው

133. ትንሽ ጤፍ አለሽኝ ያችን ሰላልቄ
እናቴ ልበልሽ በፈፋ ዘልቄ

134. እናት አለሚቱ የበረሃ ሎሚ
እኔ ለሙትልሽ አንች አትታመሚ

135. አሞራይቱን አርጉኝ ቅጠል በለይቱን
አይቻት በመጣሁ እናት አለሚቱን

136. ሸበክ አርጋ ታጥቃ በሻሽ መቀነቷ
የወፍጮው ባላባት ያች ናት ሴቷ

137. እባክሽ እናቴ አውሽኝ ነጠላ
ጡቴ እንዲያጕቸጕች ደረቴ እንዲሞላ

138. የዳጉሳ ጠላ ሲጠጡት ይጣፍጣል
እናት አለም ምክሯ ከማር ይጣፍጣል

139. ነጭ ጤፍ እንጀራ ስስቱ ስስቱ
የማትሰላቸው እናት አለሚቱ

## 2.2.እርሻ ማረስን የሚያወድሱ ቃል ገጥሞች

140. ይታረሳል እንጂ አይጫንም በሬ
ነጋለሜ ሲሳይ ሃሊሙ ገበሬ

141. ምንኛ ደስ ይላል የገበሬ ኑሮ
ወተቱ ከማጀት እሸቱ ከጓሮ

142. እህል ከመበደር ተቀምጠህ ከጥላ
ምን ያደርግልህል አርሰህ ብትበላ

143. እያለደለደ የወርዳል እንዶድ
ለችግርም ማረስ ለሞትም መውለድ

144. መቶ ማድጋ ጤፍ ካንድ ውድማ ማፈስ
ከእሱ ጋር ተኝቶ ከእሱ ጋር መተንፈስ

145. ምንም ቢቸግረው ጅብ አይበላም ጥሬ
ደጉ አለም አለቤ ሃሊሙ ገበሬ

146. ሲያርሱ አትረስና ሲዘሩ አትዝራና
ሰው ውሎብኝ ነው በል ከጠላው ዋልና

147. መቀናጆው በሬ በሚዜዋ የሚያርሰው
በችግርም መጫኛ የተተበተበው
እንቅልፉ አያልቅበት ቢተኛው ቢተኛው

148. ኧረ ዋሊያ ዋሊያ ደበኔ ደበኔ
አርመሽ ና አርሰሽ አትበይም እንደኔ

149. አርሼና እርሜ ከበላሁ እንዳንቺ
መች ዋልያ እባል ነበር እሜቴ ነው እንጂ

150. ግብርናው የሰላ እርሻው ትልመ ሙሉ
በጣም ደስ ይለኛል የአጊሳ ልጅ ሲሉ

151. እቴ በዝናርህ በዚያ ላይ ባንዲራ
እንደ ሰርቶ መብላት የለም የሚያኮራ

152. ኧረ እረሱ እረሱ ኧረ እረሱ በጣም
እረሻ ያረሰ ሰው ዋጋውን አያጣም

153. ተው በላይ ተው በታች ሲል እየሰማሁት
የጠመደበትን ስፍራውን አጣሁት

154. መሬት እንደ እንጀራ እየቀረሳችሁ
ሃሊሙን ገበሬ ታደኸያላችሁ

155. ሃሊሙ ገበሬ የደኸየ እንደሆን
የባህር ዳር ‹‹ሽቃጭ›› ምን ትበላ ይሆን

156. አራሽ አንደፋራሽ በሰፊ ድግር
ስራው እየታየ የይርጋለም አባት የነጠርዋ ባል

157. እንጀራው ተጋግሮ ከድምድሙ ደርሷል
ጥላሁን እንደሻው በስንት ያሳርሳል

158. እንኳን ከድምድሙ ቢነካ ሰማይ
ጥላሁን እንደሻው ሊከፋው ነው ወይ

159. ደጉ አለም አለቤ በጥቋቁር በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ቆርቆሮ አለበሰ ባህር የሚመስል

160. እርሻ አሳርስ ብሎ ልቦናን ማስነፍ
ድህነት ነው እንጂ ሌላም የለው ትርፍ

161. ያረሰማ ጉበዝ እርፍ የነቀነቀ
ወፈጮው እንዳጉራ መስከረም ዘለቀ

162. ያላረሰ ጉበዝ እርፍ ያልቀነቀ
ወፍጮው የሐምሌ አቦ ተነቅሎ ወደቀ

163. ገበሬው አራሽ ምሳውን ይበላል ፈትፍቶ በአብሽ
ከደጃፉ ቆሜ ሁለት አይኔን ባሽ
እያለ ሰደደኝ እንደኔ ባረስሽ

164. ያላረሰ ጉበዝ እርሻ ያለወደደ
ልጆቹን ሰብስቦ ነገላ ወረደ

## 2.3. አገርን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች

165. የተባረከ ነው ዱርቅ አዝባ መሬቱ
ሞላልኝ ዘገየ የበቀለበቱ

166. አገር አገር አለይ ይች አገረ ብርቁ
የኛም አገር አለን ግብጣዊት ሲዘልቁ

167. የአገሬ ልጅ ቢሆን ይህን አይሰራኝም
የሰው አገር ልጅ ነው ቢሄድ አይቆጨኝም

168. አዙረህ አዙረህ እንደቤት ማገር
ትጥለኝ አለህ ወይ እንዴት ከሰው አገር

169. እወቀረዋለሁ ጥርሴን በሲሚዛ
የጀግኖቹ ቦታ እስኪ ልሂድ መልዛ

170. እንደዛሬው ሳይሆን ቆሻሻው ሳይበዛ
እንዴት ነው ስላምቤት የነበረው ለዛ

171. ኧረ ላስታ ላስታ ላስታ እንደምን ይቅር
እንደናት አንጎቻ የሚለው ቅር ቅር

172. የአገሬ ልጅ ሞረሽ የወንዜ ልጅ ሞረሽ
ማን ብሎ ይጠሯል የሚወዱት ሲያመሽ

173. የአገር ልጅ በየሌ ይለወጣል ወይ
ሲሞቱ ሚቀብር ሲታመሙ የሚያይ

174. የአገር ልጅ የአገር ልጅ የአገር ልጅ ዘመዱ
ቢያገኝም ያበላል ቢያጣም ያዝናል ሆዱ

175. እሄዳለሁ ጎጃም አድራለሁ ቢቸና
የተሰራልኝን ዓሣ ወጥ ልበላ

176. የአገሬ ልጅ ነው ወይ በዚህ የወረደው
የወንዜ ልጅ ነው ወይ በዚህ የዘለቀው
ተጣልቼው ነበር እስኪ ልታረቀው

177. እወቀረዋለሁ ጥርሴን በመስታወት
የጀግኖቹ ቦታ እንዴት ነው ሳምራዊት

178. አዲያ አቦ ከሜዳው ሰው የለም ያሉቱ
ሞላልኝ ዘገየ ሳለ ነጋሪቱ
የተባረከ ነው አዲያ አቦ መሬቱ
ሞላልኝ ዘገዬ የበቀለበቱ

179. ምነው ባደረገኝ የመኔ ወለዶ
አንገታቸው መልካም ጥርሳቸው በረዶ

180. አንተ ያገሬ ልጅ እንደምን ከርመሀል
ሽምተህን በላህ እራቡን ገሎሀል

181. እንዴት ነው ግብጣዊት የጭንጫ ፎረፎር
ሳይቀቡ መውዛት ሳይበሉ መወፈር

182. እንዲያምርብሽ አለም እንድትወደጂ
እንደኛ ግብጻዊት በተወለድሽ እንጂ

183. በአፋፉ ሲዘልቁ ይታያል ዋርካው
ኸረ አገሬ ደብር ሳቁ ጨዋታው

184 አይወለወልም ምጉጉ በኩበት
የሸጋጉች አገር እንዴት ነው እብናት+

185 ስምሽ ይጣፍጣል እንደ እናት እንደ አባት
እኔም ሳወድስሽ ሳመስግንሽ ሳምራይት

186 አጊሳን ሳስታውስ ስሟን ስጠራ
ሁሌም ትዝ ይለኛል የሰራሁት ስራ

187 የአንበጤ ስንዴ እንክርዳደ ብዙ
እንዴት ነው አገሬ ዳባት ወንዛወንዙ

188 እንደ እናት እንደ አባት ውሃም ይስማማል
እንደ እህት እንደ ወንድም ነፍሷም ይስማማል
ለምለሚቱ አጃ ካንቺ ማን ይደርሳል

189 ፍየል አትረዱ እኔ አልበላም ጉበት
እንዴት ነው አገሬ የተወለድኩበት

190 እርግፍ እርግፍ አለ የግራሩ ፍሬ
መጡ እነ ቁርቋሮች እነ ሞት አይፈሬ

191 እኔስ ከቅድሙ አሁን ደስ አለኝ
የቁርቋር ልጆችች መጡ መሰለኝ

192 አይሸከሽክም በርበሬ በዋንጫ
እኔስ እሄዳለሁ ወደ ንፋስ መውጫ

193 ስድስት ሰዓት ሲሆን ይግላል መሬቱ
ኸረ አገሬ መና ሸጋ ያለበቱ

194 አዘዞ እና ጎንደር አንድ ነው ግዛቱ
አዘዞ ይበልጣል አንተ ያለህበቱ

195 ደብር ተክለ ሃይማኖት ክበቡ ክበቡ
እንኳንስ ሰዎቹ ያጫውታል ካቡ

196 ወይ አገርህ ይራቅ ወይ ስምህ ይለወጥ
ያለህበት አገር ሸተተኝ እንደወጥ

197 ነጭ አሞራ ዙሮ ይገባል ከዋሻ
እንደምነው ደብር የወኔው መነሻ

198 አንት ከንፈረ ጤዛ አንት ከንፈረ ሙዝ
ያለሽው መናዲቅ ከመልካሙ ወንዝ

199 አጊሳን በሙሉ እሳት በላው አሉ
አጃንም በሙሉ እሳት በላው አሉ
ወይኔ ብርሌዬ ብርጭቆዬ ሁሉ

200 ሳሊ ገበያ ውዬ ሳሊ ገበያ ልደር
መጠጫው ብርሌ መቀመጫው ወንበር

201 እኔ ከሰው ሀገር ሀገሬ ለሌላ
ከሰው የበለጠ እንጀራ ሳልበላ

202 እንዲህ ወዳጊሳ መልክት ቢልኩኝ
የሸኂር አቀበት ደከመኝ ባላልኩኝ

203 የሰው አገር ውሃ ብጠጣው መረረኝ
ኧረ አገሬ ደብር መጣሁ ተቀበለኝ

204 ዱርቃዝባ ሚካኤል የጭንጫ ለምለም
ያለጥርሰ መልካም ያለውብ የለም

205 ኧረ ላስታ ላስታ ድህና መንዲሱ
ክትት አርጎት ሄደ ከነመትረየሱ

206 የሰማይ ደመና የተረገረገው
የአንተን መና መሄድ ለእኔ ባደረገው

## 2.4 የአካባቢ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚያወድሱ ቃል ግጥሞች

207 አድናለም ሞላ የሩቅ ሰው የሩቅ ሰው
ላኪልኝ ለአሞራው ለሚመላለሰው

208 አሞራ ቢልኩት መች ያደርሳል ለሰው
የእናት ልጅ ነው እንጂ የልብ የሚያደርሰው

209 አይነ መልካም ብዬ ጥርስ መልካም ብዬ ተወራርጃለሁ
ብቅ በይ ፋንታለም እረታብሻለሁ

210 ኩታው ሸር ያለ ነው ጥይቱ ድፋው
ሳይደፋውም አይቀር ሳይከነችረው

211 የሰንደል ሳሙና የገዛው ባልሽ
ማንን ሊያጥብበት ነው አንቺም ወርቅ ነሽ

212 በቻለ በቻለ ይቀናል በርበሬ
ይላል ክምብል ደፋ የዛ ልጅ ጉፈሬ

213 አንዲት ናት አንዲት ናት እንደ መድኃኒት
ባንቻለሜ ጠጋው የአንደበቱ እህት

214 አርፌ ነበረ እስኪ ልሂደው
መላሽ እየታፈስ የብር አለንጋው

215 አጭር ነው ይሉታል እድሜያቸው ይጠር
ኮረሪማ አይደለ ወጥ የሚያሳምር

216 በጥቋቁር በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ጥላሁ እንደሻው ክርክሜ አበቀለ ባህር የሚመስል

217 ውቢቱ አሻገር የእኔ የብቻዬ
ከጆሮዬ ላርግሽ እንደ ጉትቻዬ

ከትከሻው ግድም ከኪሱ ባምባ አለው
ሞላልኝ ጥላሁን የሚነካው ማነው

218 አቤት አቤት ይላል ሲሄድ አስካርባው
ምን እናት ወለዱት ምን ወንዝ አፈራው

219 መገን የአራዳ ልጅ ጠጅሽን ኮምሪ

መላሹ ንጉሴ አይጠጣም ቅራሪ

220 ደሴ ግራር እንጂ አያበቅልም ቡን
ወገቡ ሚመስለው ረጅም አልቤን

221 በል ግባ በል ግባ በል ግባ ወደ ቤት
ነጋለም ሲሳይ የሳሙን ባለቤት

222 ደረጀ ደመቀ ደህና ሁንልኝ
የቀኑ ጨለማ እንዳይሆንብኝ

223 ሙገጎይቱ ጥቁር ታወጣለች ነጭ
ገነትዬ አዲሱ ከሴቶች ብለጪ

224 እኔስ የምወደው ሁለቱ ባይሞቱ
ታደሰ ጸጋዬ ከነ ባለቤቱ

225 አዲያ ከሜዳው የበቀለው ዋርካ
ቅጠሉ የማይደርቅ ስሩ እማይነካ

226 ለገስዬ አለሙ ዋረካዬ ዋርካዬ
ፍሬውን በልቼ ዛፉ ከለላዬ

227 ቀጭን ኩታ ለብሶ ሲሄድ ባቀበት
ቄስ ወርቁ ገላዬ ትልቁ ታቦት

228 ዱባ ሳር አይበላም ፈርሱን ምን አበዛው
ሆነልኝ ደጀኔ ይምጣ ባለለዛው

229 እየው ከዚያ ማዶ የወጭት ስባሪ
ንጋት መኰንን ንጉስ አሳዳሪ
ማሳደሩንማ ሁሉም ያሳድራል
ንጋቱ መኰነን ጠጅ ያዘነብላል

230 ከትክሻው ግድም ከኪሱ ባምብ አለው
ነጋለሜ ሲሳይ የሚነካው ማን ነው

231 አበርዬ ንጋት ሞሰበ ጉድጓዳ
እሷ ታውቀዋለች በራብ የተጉዳ

232 ይተኩሳል እንጂ አሊሙ እስኪበላ
አዲያአበ ነው ቤቱ ያ ዘገየ ሞላ

233 የደደሆ ፍሬ የማይበላው
ኩታው ሸረብራባ ጥይቱ ድፋው

234 ፈሪና ተራራ ሁልጊዜ ይኖራል
ጀግና ብርሌ ነው ወድቆ ይሰበራል

235 የደገኛ ልጅ ነህ የአዛባ ዛቂዉ
ጥርስህ የሚመስለው የእርጉ ፍላቂው

236 ከቅመሙ ሁሉ ይበልጣል ጤናዳም
ፋንታነሽ ለገሰ የሴት ረገዳም

237 ላኪልኝ ደብዳቤ ሁለት ወረቀት
አንዱን የትዝታ አንዱን የናፍቆት

238 አውራ ቢዘሩት ተመልሶ አወራ
ዝንፍልፍል ያለ ነው እንደ ዘላን አውራ

239 እስነጠቃለሁ ቁሜ እንደ ግራምጣ
ደጉ አለም አለቤ ሸንቅጡ ሲመጣ

240 እቴ እንዴተ ዋላቸሁ ካንድ ቤት ሁለቱ
ፋንታነሽ ለገሰ ሰብልዬ ልጂቱ

የድኩላ ስጋ ሆዴን እያማረው
241 ኸረ መሸ መሸ ጅብ አንኮሻኮሸ
እስኪ ለተኳሹ ለአረጋ ልንገረው

242 እንኳን የስፌቱ የጭቃው መልክ አለው
አስረበብ አለቤ ወደረኛሽ ማን ነው

243 ከላይ ቤት ከታች ቤት ወጪት የጣዳችሁ
ቀኑብሽ የማታ ትመጥንላችሁ

244 የእሜቴ አበዙ ልጅ በስምቡል የታሸ
ሊመጣ ነው መሰል በጓሮ የአመሸ

245 ከአንድ እንጀራ በላይ ምን ይበላል ሰዉ
ወገቡ እንደ ጭራ የመነመነው

246 ጠይም ዘለግ ያለ ጉራዴ ታጣቂ
ሲመጣ ተጫዋች ሲሔድ ተናፋቂ

247 የሰቆጣ ልጆች የገደል ሳር ናቸው
አይገኙም እንጂ ሲገኙ ማር ናቸው

248 እረሻ ካረሱ አይቀር ከጠመዱ በሬ
ዘር እንደ ምትኩ ቡቃያ እንደ ማስሬ
በማለዳ ጠምዶ ሲያስመስለው አውሬ

249 ገድፉኝ የሚለው አንገቱ በባላ
የጐበዝ ወንድም እምርዬ ሞላ

250 ቢሰጥ እና አዲሱ ምንና ምን ናቸው
የጆሮ ጉትቻ የአንገት ማተብ ናቸው

251 አነሳሳዋለሁ አልለውም ችላ
አበበ ፍቃዱ የአንበሳ ቡችላ

252 የምንሽር ጥይት አስመስሎ ጣቱን
ያስመዘግን የለ እናት እና አባቱ

253 እንዴትነህ በሉልኝ ቀኝ እጁን ይዛችሁ
መቼም የኮራ ነው አያናግራችሁ

254 አዲስ ዘመን በታች ግራዋ ነው ዛፉ
ምን እየበሉ ነው የሚዝለፈለፉ

255 ስራው እየታየ ንጉስ አሳዳሪ
አይላትም ሚስቱን በቁጥብ እደሪ

256 ቤቷ ከመንገድ ዳር ሞሰበ ጉድጓዳ
የራበው ታውቃለይ የስራዬ ሚስቱ ጎኑ የተጐዳ

257 በሪሁን እንደሻው ዘፈፍ እንደ ዋርካ ከባድ እንደ ዝሆን
ዝቅ ብዬ ላንሳህ እችልህ እንደሆን

258 ምን ይመጣብኛል ካለቱ ብተኛ
በሪሁን እንደሻው ‹‹አረመኔው›› ዳኛ

259 ተኮሶ ተኩሶ እጁ መነመነ
በሪሁን እንደሻው ፈረንጆቹን ሆነ

260 ሞሰብ አይነሳም ያለ ፍርፋሪ
የጎበዞይ አባት ሞላልኝ ተፈሪ

261 ፈንታለሜ ሞላ አውሺኝ ዣንጥላ
አንቺ ተሄጃለሽ በጐፈሬሽ ጥላ

262 ካስኮላው ተማሪ ከሰባ ስምንቱ
ከቶ እንዴት ያለ ነው መላሹ ያሉቱ

263 ደግሞ ከሰው ጣት አለ ወይ ረጅም
ጥላሁን እንደሻው የበለጤ ባሏ የእነ ወርቁ ወንድም

264 ገድፉኝ የሚለው ወገቧ በባላ
የበለጥዬ እህት ዘውድ አንችአለም ሞላ

265 በለጥዬ ሞላ ሙጉጉሽ አይውጣ
የጠገበው ሲሔድ የራበው ሲመጣ

266 ዳዊተቱን አድርጎ ከጉልበቱ ላይ
አዝመራው ቢደግም ሰው አይገልም ወይ

## 3. ፍቅርን የሚመለከቱ ቃልግጥሞች

267 ትመጣ እንደሁ ልምጣ ትቀር እንደሁ ልቅር
ሰው ለኬ ሰው ልከህ ሊሆን ነወይ ፍቅር

268 የአገው ‹‹ስደተኛ›› ቅል ያንጠለጠላል
የደህና ልይ ፍቅር እድሜ ይቀጥላል

269 እናትክን አትውደድ ለዘጠኝ ወር ዕድሜ
እኔ አርግገፄሃለሁ እስከ ዘላለሜ

270 አፋፍ ላፋፍ ስሄድ አገኘሁ እንኮይ
ከረመጡ ላይ ቆምኩ አንተን አንተንሳይ

271 ሱባሱብ ጨዋታ አታውቅም ሚስትህ
ቶሎ ና ከእኛ ቤት እናሞናሙንህ

272 አንተን አንተን ብዬ አንተን ካላገኘሁ
እኔ ሞቴን እንጂ ሌላም አልተመኘሁ

273 አንተን ባየሁበት ሌሎችን ሳያቸው
ይመስሉኛል ቅጠል ንፋስ የጣላቸው

274 ወደ ታች ዳሰኝ ከአንገቴ ይዘህ
ሀመሜን ዝቅ ብለህ ታገኘዋለህ

275 ሀገሩ ወዲያ ነው ወደ ግራር አቦ
አንገቱ ሚመስለው ጠጅ የያዘ ገንቦ

276 እሞትለሃለሁ ሞቴን ከወደድከው
ረጅም ምንሽር ቤልጂግ ለመሰልከው

277 እኔ እወድሃለሁ አንተ እንደው እንደው
እንደ ቆረቆንዳ ወፍ እንደበላው

278 ብወድህ ነው እንጂ ቢያደላልህ ሆዴ
እንደ ነፍስ ገዳይ ዱር ለዱር መሔዴ

279 እኔማ ስወድህ አለኝ አማርኛ
ያንቀጠቅጠኛል እንደ በሽተኛ

280 ሽጋ የእኔ ሙሉ ሙሉ ብየሃለሁ
የጉደልክ እንደሆን ጠጅ እሞላሃለሁ

281 ሽጌ ያንተን ነገር ስቋጥር ስፈታ
አዲሱን ቀሚሴን እሳት ፈጀው ማታ

282 አንዱን ልቤን ሸዋ ልኬ ሰድጀው
አንዱን ልቤን ቦንጋ ልኬ ሰድጄው
ክረምቱ ደረሰ ሳልሰበስበው

283 በመኪናው መንገድ በወላሊማዉ
አንተን ተከትዬ ይብላኝ አሞራዉ

284 የአዲስ አበባ አውሬ ስሙ ነው አሳማ
ተብረከረኩልህ ድምጽህን ብሰማ

285 አልተብረከረኩም ውሽቴ ውሽቴ
እንደው በደፈናው ወክ አለ አካላቴ

286 መላ በለኝ እና እኔ መላ ልጣ
እንደምንም ብዬ ካለህበት ልምጣ

287 አይወዱ ወድጄ የጉረቤት ልጅ
እራቴን ስበላ ልቤ ወደ ደጅ

288 ሽጋዬ እንደ ካርታህ እንደ ዝንጉርጉሩ
ትረሳኝ ይሆናል እየበዛ ቀኑ

289 ያንን ላይ አቀበት እንደምን ልውጣው
ጠይም ልይ አርግዤ ከነ ውጅግራው

290 ውጅግራውን ይዞ የሚለው ፊት ፊት
ልቤን አርጉት ሔደ ዘርዛራ ወንፊት

291 የዳገት አባሎ ንፋስ ያቦለለው
የማትሆነኝ እንደሁ ልቤን ተው ልበለው

292 ከጉድጓዳ ስፍራ ይቆረጣል ሚዛን
ያንተው ልብ እንዴት ነው የኔው ይናውዛል

293 ብርቱካን በልቼ ሎሚ ሎሚ አስገሳኝ
ያንተው ልብ እንዴት ነው የእኔው ጤና ነሳኝ

294 ኧረ ደሴ ደሴ ኧረ ቦሩ ቦሩ
ካንተ ጋር አርፍጄ ደከመኝ መንገዱ

295 እሄደላሁ እንጂ ምነ አለመሔዴ
መጥላቱን  መውደዱን መች አወቀው ሆዴ

296 እሄድ እሄድ እና እላለሁ ታከተኝ
መውደድ በጉራዴ እያነካከተኝ

297 ጣቱ ይመስላል የቻይና ጥይት
ጉፈሬው ይመስላል የሐር ዝምዝማት

298 ጥርሱ የሚመስለው የጊደር ወተት
ካንተ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት
ላፈር አይደለም ወይ የተሰራሁት

299 ካንተ ጋራ ሆኜ ሁዳዴን ልጡመው
እነኳንስ ሁዳዴን የሁለት ወሩን
ልጡም አርብ ሮቡን የዘላለሙን

300 እንደ አዘዞ ጠዳ ወለል ያለው ገላህ
ሃብታም በገንዘቡ ደሃ በዓይኑ በላህ

301 ካልሆነ ሰው ጋራ ፍቅር መደርደር
ውሃ በብርሌ ወዝቶ ማደር
ብረት ምጣድ ጥዶ ቅቤ መጋገር

302 ነገ እህን ጊዜ ቁርጡን አውቀዋለሁ
ወይም ትመጣለህ ወይም እመጣለሁ

303 የጉፈሬው ጥላ ዝናብ የሚያስጥለው
የጥርሱ ፈገገን ወንዝ የሚያሻግረው

304 አንተን ይስጡኝና ሁዳዬን ልጡመው
እንኳንስ ሁዳዬን የሁለት ወሩን
ልጡም አርብ እሮብን የዘላሙን

305 አርገኝ ከጐፈሬህ ከድምድሙ ላይ
ከከዘራው በትር ልከብድህ ነወይ

306 ከከዘራው ብትር መይ ትከብጀኛለሽ
አገሬ በረሃ ትቀልጭብኛለሽ

307 አባይና ጣና መገናኛው ዳሞት
ምን ትጠቀማለህ አንተን ብዬ ብሞት

308 አላማጣ ውዬ መልሼ አላማጣ
ከአንተ የተሻለ ፍቅር ሳላመጣ

309 ትልቁ መኪና ባለ ሃምሳው ወንበር
ሰኞ ደብረ ታቦር ማክሰኞ ጐንደር
ከሚወዱ ልጅ ጋር በዚያ ነው መብረር

310 አርግዤአለሁ መሰል ሆዬ ይላወሳል
እንዲህ ሲል እነዲህ ሲል ቀኑ ይዳረሳል

311 እኔስ አለሁ አለሁ እኔስ አለሁ አለሁ
ፍቅር አመላላሽ አውቶብስ ሆኛለሁ

312 እኔማ ዘንድሮ እከርምን ብለኸኝ
ከስራዬ በላይ አንተ እየታየኸኝ

313 አሁንም ቅድምም ይናገረኛ እሱ
ከንፈሩ እየሸሸ የሚታየው ጥርሱ

314 እንደምነው ዓይንህ ጥቁርና ነጬ
አይመቸኝ ብሏል ከአንድ አገር ሁለቱ

315 ጅብ እግር የለውም ይወጣል ተራራ
እገሬ ባይራመድ ልቤ ካንተ ጋራ

316 የጬርቁ ማጠቢያ ሊምን ላይ ነው ወንዙ
እመጣልሃለሁ ለማጠማዘዙ

317 ካላጉረመረመ አይበላም ነብር
ደሞ እንደ ዝናርህ በሽንጥህ ልዙር

318 ደሞ እንደ ዝናሬ በሽንጤ ዙረሽ
እህል እንዳልበላ ታደርጊኛለሽ

319 እህል እንዳተበላስ እኔ አላደርግህም
መድኃኒት ነው እንጂ መውደድ አይገልህም

320 አበባው አበበ ንቡ ገባልህ
እንግዲህ የአገር ልይ ማር ትበላለህ

321 እንኳን ማር ልበላ አላገኘሁ ሰፈፍ
እኖራለሁ እነጂ ባንተው ስም ስለፈፍ

322 አበድሽ አበድሽ አሉኝ መቼ ነው ማበዴ
ከአምሳ ደብር አገር አንድ ልጅ መውደዴ

323 ትመጣ እንደሁ ልመጣ ትቀር እንደሁ ልቅር
ሰው ልከህ ሰው ልኬ ሊሆን ነው ወይ ፍቅር

324 ከመቀጠዋ ልይ አንዱ ከደረሰኝ
አጠረ ቀጠነ አልልም አነሰኝ

325 ዘር ዘር ያለ ነው ጥርሱ እንደ በለሴ
እሞትልሃለሁ አልሳሳም ለነፍሴ

326 አንተን አለኩኝ እነጂ መች ብዬ ሌላ ሰው
እንደ ሽል በሆዴ የምትላወሰው

327 ሰርክ አዲስ አበባ ሰፊው አገር ሳለ
ከዚህ ከጠባቡ ከሆዴ ሰው አለ

328 የፍቅር ዘበኛ ከሆንኩ እኔ ብቻ
አንሳልኝ ፍቅርህን ሳልሆን መተረቻ

329 አንሳልኝ ፍቅርህን እኔ አልፈልገውም
መንገላታት እንጂ ሌላ ትርፍ የለውም

330 ይኸ ሽማኔ ልይ ‹‹የቁጢት ቆራጭ››
ልቤን አርጐት ሔደ ቋሚ ተቀማጭ

331 በሶስቱ ስላሴ በአርባ አራቱ ዳኛ
ስደድልኝ ልቤን በጐኔ ልተኛ
332 ነጋሪት ከጐንደር ቱልቱላው ፎገራ
ከዚህ ተቀምጮ ልቤ ካንተ ጋራ

333 ደገኛ በሬውን ይለዋል ቢለው
በዓይኑ ገርፎኝ ሔደ ሰንበር በሌለው

334 አንጥረኛው አሽከር ውበቱ ውበቱ
ስራኝ እንዳገርህ እንደ ቀለበቱ

335 በዓይንህ አላይበት በጥርስህ አልበላ
እመጣልሃለሁ ዓመትም አልሞላ

336 ስራኝ እንዳሰኘህ እንደ ሰበከተህ
አፍርሶ መስራቱ አንተን ካልታከተህ

337 ከፋህን ደስ አለህ ስታጣኝ ካገሩ
ፍቅር ይቀንሳል ከዋሉ ካደሩ

338 እኔ ዶሮ ሆኜ በጓሮ ስጭር
አንተ አሞራ ሁነህ ይዘኸኝ ብረር

339 ውሃ እኮ የወርዳል አረንጓዴ ለብሶ
አንታረቅም ወይ የበደለው ክሶ

340 መበደሉንማ አንተ በድለሃል
የአገር ሽማግሌ ያደላድልሃል

341 የጎፈሬህ እንኳን አለው እርከን እርከን
ያንተ እናት ይውለዱ የበቀረው ይምከን

342 እቴ እንዴት ዋላችሁ ባይናገር አፌ
ደጅ ጥናቴ እኮ ነው በደጅህ ማለፌ

343 እያረገረገ አይላጥም ዛና
እመጣለሁ እኔ እምብዛም ቢጠና

344 እኔ እወድሃለሁ ያንተን መውደድ እንጃ
ወዳለህበቱ ያደርገኛል ወንጃ

345 እኔማ ዘንድሮ ሁኛለሁኝ ከንቱ
ቢጠሩኝ አልሰማ ጨርቄን ካልጐተቱ
346 እንዴት ነሽ እያለ እየላከብኝ
ተሽሎኝ የነበር አገረሸብኝ

347 ከዚህ ተቀምጬ ከዚያ የታየኸኝ
ስንቱን ጐራ ዙራ ትመጣ ብለኸኝ

348 ያን ማዶ ተራራ በመርፌ እንረሰው
አላሳየኝ ብሏል የምወደውን ሰው

349 በላሽ በላሽ አሉኝ መብላቴን ሳላውቀው
እስኪ ጉሮሮዬን ሆዴን ልጠይቀው

350 ሆዴን ሆዴ ወጋው ጐኔን ጐኔ ወጋው
አንተ አለኸኝ ብዬ ሳልሸምት በበጋው

351 ዝናብ ሲዘንብ ይለበሳል ገሳ
አሁንም ቅድምም ያንተው ወግ ይነሳ

352 ጐንበስ ቀና በዬ የተሳለምኩት
አይደለ በተስኪያን አይደለ ታቦት

353 ኧረ ዋልያ ዋልያ ከማሽላው ላይ
ጠይም ዘለግ ያለ አላየሽም ወይ

354 እንዴት ነህ በዝና እንዴት ነህ በወሬ
ጥጃው እያደገ የሚሆነው በሬ

355 ገና ሙጫ ሳለሁ ጥጥ ፍሬ ሳህል
አስለምደውኛል ፍቅር እንደ ኩል

356 የጎንደር አገልግል ሐር ነው ሰበዙ
ባንተ የተነሳ ሰማሁ ብዙ ብዙ

357 አሸር ባሸር በልቶ ሆዴን ከማለት
ጦም ውሎ ጦም አድሮ ሺጋ መሸመት

358 እወድህ ነበረ ዛሬስ ጠላሁህ
ሰው ያልበላው ቅጠል ስትበላ አይቸህ

359 ሰው ያልበላው ቅጠል አስተናግር ነው
እኔን ካልመረረኝ ብበላው ምነው

360 ፍቅርህ እና ፍቅሬ በጋን ተጠንስሶ
ሳይጠጣ ቀረ ሰባራው አፍሶ
መለየቱን እማ ወድጀን ተለየሁ
እንደ በካር ጊደር ዞሬ ዞሬ እያየሁ

361 ኧረ ፍቅር ፍቅር ፍቅር አለባሶ
ሲጀምሩሽ ማር ነሽ ሲጨርሱሽ ኮሶ

362 በአፋፉ ዘልቄ ስጠራህ ወይ በለኝ
ካላንተ ማን አለ ከሰው ሰው የለየኝ

363 የራያ ማሽላ ውስጣ ውሰጡ መንገድ
ተወኝ አላልኩም ወይ ካንድ በላይ መውደድ

364 መላ ተመልምሎ ሲበላ ደርሼ
ሙቼልህ ነበረ አንድ ጊዜ ጉርሼ

365 አንተን ያገባ እና ነጭ ላም ያረባ
ሁል ጊዜ ይኖራል ገነት እንደገባ

366 ራሴን አመመኝ ወገቤን ጨምሮ
ያንን ጠይም አሽከር ካላመጣሽ ብሎ

367 ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም አትውደዱ
ጠይም ወድጄ ነው የጠፋኝ መንገዱ

368 አሻግሬ እያየሁ ማዶ ማዶውን
ዓይኔ ዝሃ አዘጋ ያልፈተለውን

369 አይሸከሽክም በርበሬ በጥዋ
እንደምን ነህልኝ አይጠገቤዋ

370 ትመጣለህ ብዬ ሳይ በሩን ሳይ በሩን
የቀረህበትን ንገረኝ አበሩን

371 በቀይቱ ዶሮ እየተመሃኘ በጥቁሪቱ ዶሮ እየተመሃኘ
የእኔስ በሽታዬ ሰው ሁኖ ተገኘ

372 እመጣለሁ ብለህ ምነው የቀረህ
ብቅልና ጌሾ ከሆዴ ከተህ
አሁንም ቶሎ ና ገነፈለልህ

373 ሲያምህ አመመኝ ሲያግሙህ ደም ወጣኝ
ብትሞትስ አልሞትም እኔ ምን በወጣኝ

374 እንኳን አንተን አንተን የምወድህን
አስረው ያሽከሙኝ ዘመዶችህን

375 ዝናብ ዘንቦ ዘንቦ ቁልቋል የለው ጤዛ
አንተን አስወደደኝ ወንጀሌ ሲበዛ

376 ላስታና ነገላ ማዶ ለማዶ ነው
ፍቅር ያለቦታው አባጨጓሬ ነው

377 ሰርክ አበባ ሆኖ ሰርክ አበባ መውደድ
በረጅም ጐዳና ስንቅ የሌለው መንገድ

378 እኔ ወዲህ ማዶ በነጭቱ ፈረስ
አንተ ወዲያ ማዶ በቀይቱ ፈረስ
አንገናኝም ወይ አዲስ ዘመን ድረስ

379 ኧረ ደሴ ደሴ ውድመን ውድመን
እህል እየበሉ ሰው ወዶ መመንመን

380 ፍየል ባቆልቁለት ይመስላል ሰርገኛ
እንዴት ነው ከንፈርህ የጥርስህ ዘበኛ

381 በአፋፉ ሲዘልቁ ይታያል ቤታቸው
ወይ ልጃቸው በሆኩ ወይ ጐረቤታቸው

382 ሮቢላ ሲሄድ ይላል ባየር ባየር
የሚወዱትን ልይ ባይን ነው መዘየር

383 አገሩ ወዲያ ነው ወደ ቀኝ ጣምሮ
ለቤን ይዞት ሄደ ባገልግል ለጉሞ

384 የአገው ምድር ስንዴ ወደ ደሴ ዘሟል
እንኳን የቀመሰህ ያየህ ዓይኑን ታሟል

385 ያንተ እናት አባቶይ ስጋ ነው እርማቸው
አንጀት ትበላለህ አንተማ ልጃቸው

386 ቁጭ ብዬ ከማስብ ተቀምጬ ማስብ
ከደረቴ ላርግህ እንደ ልሳነ ሰብ

387 አንተን አልኩኝ እንጂ መች ብዬ ሌላ ሰው
እንደ ሽል ከሆዴ የምትላወሰው

388 መሽ ደህና እደሩ ብርቱ ስራ አለብኝ
ግንብ እገነባለሁ ፍቅር ተንዶብኝ

389 ማሽላ በእሸቱ ጤፍ በወለዳው
ይቀጥላል ገና የእኔና ያንተው

390 ለሰው ሙቼ አላውቅም ላንተስ ልሙትልህ
አዲያ አቦ ከሜዳው አጥንቴ ያውልህ

391 እናት እና አባትህ አይወዱም እንግዳ
ሳመኝ እና ልሂድ በሳንቃው ቀዳዳ

392 ዓይንህ ኳላ ኳላ የትምባሆ ፍሬ
አንተን የወለዱ መልካም ሽማግሌ

393 አንተ የረገጥከው ምድሩ ያስታውቃል
እሱን እየሳምኩኝ ሰው ሁሉ ይስቃል
የመገኛህ ነገር ከሰማይ ይርቃል

394 በህልሜ እየመጣህ እንቅልፍ አጣ ልቤ
በፈጠረህ አምላክ ላክልኝ ደብዳቤ

395 አንተ እብናት ሁነህ እኔ የዝሁር
ስልኩን ደውልልኝ እንነጋገር

396 አጥንቴ በቁና ይለቀምልህ
ደሜ በብርሌ ይንቆርቆርልህ
ቶሎ ብለህ ጠጣኝ እንዳልጐሽብህ
የጐሽሁ እንደሆን ጤናም አልሆንህ

397 ገላህ አይጠገብ ትዝታህ አይጠፋ
ምነው ላንተ ሲልስ ሞት ካገር በጠፋ

398 ምን ተማሪያም ብዬ ለስምን በደጅህ
ተዘካሪ መስሎ ቢነካኝ እጅህ

399 የሰራተኛ ልጅ "የብረት አንጣሪ"
የሽማኔ ልጅ ነው "የዝሃ ቆጣሪ"
አፍርሶ የሰራኝ ደግሞ እንደፈጣሪ

400 ለምን ታየኛለህ እገሬን እንደ ውሻ
መመልከት ነው እንጂ ዳሌና ትክሻ

401 አንተ እኔን በማለት እኔ አንተን በማለት
ገንዘባችን ሁሉ አለቀ በስለት

402 አንተም ብትል እኔን እኔም ብል አንተን
በከንቱ ነው እንጂ መች ተገናኘን

403 አስገዝተዋለሁ ዓይንህን በቄስ
ከእኔ በቀር ሌላ እንዳይላወስ

404 አንተ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ
አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ

405 ገደሉማ ሲናድ ይጫነን የለም ወይ
ወለል ባለው ሜዳ አንገናኝም ወይ

406 ለቀይ ልጅ ቢሉኝ በርበሬ በላሁኝ
ለጥቁር ልይ ቢሉኝ ክሰል ቀረጠምኩኝ
ኧረ ለጠይሙስ መድኃኒት አጣሁኝ

407 ትምህርት ቤት ሁኜ ትዝ ብትለኝ
በአማርኛው ደብተር ሂሳብ ሰራሁኝ

408 ኧረ አንተ መኪና ጐማው ይፈንዳብህ
ብጠራህ አትሰማ ብሮጥ አልደርስብህ
የምወደውን ልይ ይዘኸው በሆድህ

409 ምን ዓይነት መኪና ሞተረ ገብጋባ
የምወደውን ልይ ደሴ ይዞት ገባ

410 በሰባራ ማውራ ውሃ አይጠለቅም
እኔ ወድሃለሁ ያንተን ግን አላውቅም

411 በመኪናው መንገድ ሂደሃል መሰለኝ
የጐማው ቁርጥራጭ አንተን አንተን አለኝ

412 ለምን ትመጣለህ ሌሊት ሌሊት በህልሜ
ቀን አትመጣም ወይ እያየሁህ በዓይኔ

413 ንብ ሆነህ ብትመጣ አደይ እሆናለሁ
አንተ ብረር እንጂ እኔም እበራለሁ

414 ይለቀማል እንጂ ጥጥ አይመነሽም
እመጣለሁ ብሎ ሸጋ ልይ አይዋሽም

415 የፈለገው ይሁን ያበጠው ይፈንዳ
ሸሼጌ ልምጠጥህ እንደ ቆላ አገዳ

416 እመጣለሁ ብለህ የማትመጣውን
ደጁ ክፍት አደረ የምዘጋውን

417 ካንድ አልጋ ተኝተን ታማኛለህ አሉ
ስጭኝ አትለኝም ያማረህን ሁሉ

418 የወፍ ስጋ በላሁ በቅመም ተሰርቶ
ፍቅር ሊገለኝ ነው በደሜ ስረ ገብቶ

419 በቆላው በደጋው አይጠፋም ቀልጣፋ
የት አገኝህአለሁ ህይወቴ ቢጠፋ

420 የነጭ ጤፍ ዛላ የጌቹ ቀለብ
የት አገኝህአለሁ አይኔ ቢቅለበለብ

421 የኔና ያንተ ፍቅር በጋን ተጠንስሶ
ሳይጠጣ ቀረ ሰባራው አፍሶ

422 እንደ እንጀራ ለኔ መድኃኒቴ ነህ
ሁል ጊዜ የሰው ፊት ታሳየኝ አለህ

423 ከወፍጮ ላይሁና ታሽካካለች ዶሮ
ወይ አንዴ አይመጣ ሁልጊዜ ቀጠሮ

424 አንተ ነህ ወይ እኔ የከዳነው በፊት
ስራ ቡቃያ ነው ይለያል ወደፊት

425 የቆላ ደረባ ይመረጋል በበት
ጉፈሬው ይመስላል ንብ የሰፈረበት

426 አይናማው በኔሞት እኔ አፈር ስሆን
አንዴ ሳቅና ልየው ጥርስህን

427 በሽታየ አንተ ነህ ምን በሽታ አለብኝ
እመጣለሁ እያልክ እየቀረህብኝ

428 አሽም ይላል ወፍጮ ይከተል መጅ
ያወዛውዛል የልብ ወዳጅ

429 ዳግባ ካፋፉ ላይ ተኝቻለሁ አሞኝ
በሌላም አይደለ ያንተ ናፍቆት ገሎኝ

430 ፎቶህን ላክልኝ ለገበያተኛ
አብሮማ ለመኖር መቼ እድል አለኛ

431 ግቢው ታጠረ አሉ በሩ በዘበኛ
ሽጌ መቼ ይሆን የኛው መገናኛ

432 አይሮፕላን ሲሄድ ይላል ታኮ ታኮ
ልቤ አልተመለሰም ወደ አንተ ተልኮ

433 በሮዝ አበባ ላይ አሞኝ ተኝቻለሁ
አንተን የመሰለ ፈልጌ አጥቻለሁ

434 የአገሬን ተራራ ወጣሁት ተጉገ፩
በጀርባዬ ስንቄን በልቤ አንተን ይገ፩

435 አውራ ዶሮ ገብቶ እህሉን ሲበላው
እሺ አለማለትህ ከምን የመጣ ነው

436 የሰማይን ኮከብ ብቆጠረው ሰላሳ
ምን ቅጠል በበላሁ አንተን የሚያስረሳ

437 የደረቀ ሎሚ አይጠመጥም
ፍቅር የያዘው ሰው ሩጦ አያመልጥም

438 እስኪ መርፌ ስጡኝ የምመረኮዘው
አቀበት አይወጣም ፍቅር የያዘው ሰው

439 ብርቱካን ነህ አሉኝ የምትላመጥ
ከሆዴ ገብተሃል አርፈህ ተቀመጥ

440 እራሴን ብቆረጥ እንዴት አማረብኝ
እመጣለሁ እያልክ እየቀረህብኝ

441 ከባህር ላይ ሆኖ ይደንሳል አሳ
ምኑ ቅጠል ልብላው አንተን የሚያስረሳ

442 ገና ወጣት ለጋ የደስደስ ያለህ
መቃ አንገትህን በድንገት ሳይህ
የልቤን ያንጀቴን መጻፌን ላኩልህ

443 አንተን ካገኘሁስ መፃፌን ልጀምር
ብዕርና ወረቀት በአንድ ላይ ላጣምር

444 እስኪ በስማም ብየ ልጀምር ሰላምታ
ለቤ ለሚያስብህ ጧትም ሆነ ማታ

445 ጉም እግር የለውም ይወጣል ተራራ
ሰውነቴ ከዚህ ልቤ ካንተ ጋራ

446 እንባየን በዋንጫ ልቤን በሙዳይ
ልኬልህ ነበረ አልደረሰም ወይ

447 ያለህበት ቦታ ይታኛል ዛፉ
አልስማማኝ አለ ጐኔ ከምንጣፉ

448 ጠይም አለኩኝ እንጂ የውሃ ፊለፊል
ቀይማ ሞልቶልኝ የበርበሬ ዘር

449 ዝንጀሮ በገደል ይላል አጎምጃኔ
የጥርሱ ውቅራት ያስለውጣል በሬ

450 እመጣለሁ ብሎ የማይመጣውን
ልቤ ክፍት አደረ የምዘጋውን

451 የአስመራ ነጋዴ ነጠላ ለባሹ
ማተብ ስደድልኝ ለተመላላሹ

452 አጋም ፍሬው ጣፋጭ እሾሁ መርዘኛ
ጨነቀኝ ጠበበኝ ያንተው መገናኛ

453 ጤፍ እነጀራ በርጐ ስበላው አነቀኝ
አንተ የአጊሳ ልጅ ጨዋታህ ናፈቀኝ

454 የራበው ዝንጀሮ አይበላም መሬት
መኝታውን ትቸ አይኑን ባየሁት
455 ካንተ ወዲያ ጉበዝ ከኔ ወዲያ ልጅ
ኮከብህ ኮከቤ ባይገጥም ነው እንጂ

456 ኮከብህ ኮከቤ የገጠመ ለታ
በአቡነ ተክሌ ሱሪ ለጊዮርጊስ ኩታ

457 እምም ህምም ይላል ወፍጮ ይከተላል መጅ
ባፉ ማር ይዘንባል በከንፈሩ ጠጅ
ሌላ ስራን አለኝ እሱን ሳበጃጅ

458 እሱን ማልዳ ማልዳ እየጠጣሁት
መስከሬ ነው መሰል ልቤን አጣሁት

459 እስኪ አስጠይቁልኝ ያንን ልጅ ሰው በሰው
ልቤን ማልዶ ወስዶ ከምን አደረሰው

460 እንጨት ልሰብር ነው ብዬ ስነግረው
ድግር ልቆርጥ ነኝ ብሎ አይመጣም ሰው

461 ጨርቄን ልጨፈጭፍ ብዬ ስነግረው
ውሃ ሳጠጣ ነኝ ብሎ አይመጣም ሰው

462 እባክህ አካሌ ዋልልኝ አሙስ
እንደ መሔድ በለህ እንደ መመለስ

463 እባክህ አካሌ ዋልልኝ አርብ ቀን
ጌታችን በሞተው በተሰቀለው ቀን

464 እባክህ አካሌ ዋልልኝ ቅዳሜ
ከፍቅር ላይ ፍቅር ጀማሪ ነኝ እኔ

465 እባክህ አካሌ ዋልልኝ እሁድ
ወትሮም የጨዋ ልጅ በሰንበት አይሔድ

466 እባክህ አካሌ ዋልልኝ ሰኞ ቀን
ደምህና ደሜ በተጋጠመው ቀን

467 እንዴት አደርጋለሁ የማክሰኞን ነገር
እናቱም አይሰጡኝ እኔም አልናገር

468 ደናዋል አካሌ በልደና ሰንብት
መቼም ልቦናህን አላገኘሁት

469 ይመራል እያሉ ኮሶ መጠጣት
እኔን የመረረኝ ሰው ወዶ ማጣት

470 ሒድ ብዬ ሰድጀው አሁን ቀረቀረኝ
ቆየኝ ብየው ቢሆን ጨዋታ ነበረኝ

471 እስኪ መርፌ ስጡኝ አይኔን ልሰፋው
አሻግሮ እያየብኝ ያለ ሰበካው።

473. የጣዝማ ወለላ የደህና ከንፈር
አዙሮ ይጥላል እነደ መቾ አደር

474. ድንጋይ ብወረውር ደረቱን መታሁት
ምነው ኩላሊቱን ልቡን ባገኘሁት

475 . ቆላ ልውረድልህ ይቀዳልህ ደሜ
እንዴት እሆናለሁ በፍቅርህ ታምሜ

476. ከሰው በታች አርጎ ቀልቤን ያሳነሰው
አቡየ ጣዲቁ ብድሬን መልሰው
እሱንም እንደኔ ብድሩ ይድረሰው

477. ሁሉንም ታግሸ ልበል ዝም ጥርቅም
መውደድ የያዘው ሰው መቸም የለው አቅም

478. ማሽላ ጠባቂ ሁነሃል መሰለኝ
ዱር አውላጡ ሁሉ አንተን አንተን አለኝ

479. አንተ ላም እረኛ ያለሽው ባርቃይባ
ደጁ ክፍት አደረ ሰተት ብለህ ግባ

480. ቆይማ ቆይማ አንት የልቤ ሌባ
ሌሊት ተደብቄ ከቤትህ ሳልገባ

481. ይሰድቡሃል አሉ አስረውህ በድሪ
ልቤን የገደልከው አንተ ክፉ ሰሪ

482. ምን ያሳፍርሃል ሊታይ ነው ጉድህ
እስከ ዛሬ ድረስ እነሱ አሳደጉህ

483. ደግሞ እንደታች አምናው ዘንድሮን አይቸ
ገዳም እገባለሁ ቆቤን አሰፈቸ
እንዴት እሆናለሁ ከአንተ ተለይቸ

484. ተቀብቶ አለ መውዛት እየበሉ ድካም
ነፍስ ገዳይ የለም እንደ መውደድ ለካም

4. ንቀትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

485. እርመድ እርመድ እንጂ የምን ትርኩም ትርኩም
ደገዛ ነው ብሎ ያነሳሀል እርኩም

486. ብሩን ቀለበቴን ለውጨው በመዳብ
በቀይም በሆነ በጥቁር አመዳም

487. ሲሄድ አውራ ዶሮ ሲቀመጥ እንቧይ
ሰው ያለ እኩያው ይጠመዳል ወይ

488. ሰውን ያለኩያው እየጠመዳችሁ
ያቺ ልጅ አበደች ታሰኙኛላችሁ

489. የመጀመሪያዬን ስጥቼ ለሰው
አርጎዬ እበላለሁ ግምል ያነሰው

490. አንተን አልኩኝ እንጂ አንተን ሽንቅጡን
ይገቨው አይደለም ወይ ከቤቴ ጅሉን

491. አንተ የኔን ነገር ስትቋጥር ስትፈታ
ጥንድ በሬ ይዘህ ሁልጊዜ ሸመታ

492. ዘወር ብለህ ተኛ ወደ ግድግዳው
ከጭኔ ላይ ብትሞት የማን ሆነ እዳው

493. እኔ ሰው መስለኸኝ ቁመናህን ሳይ
የደጋው ባቄላ ታምቡሬ ነህ ወይ

494. ዝናብ ዘንቦ ዘንቦ ጠፈጠፉ ባሰኝ
እንዳው ዝም ብለህ ከኩታህ አልብሰኝ

495. እስኪ ውሃ ስጡኝ ሆዴን ልለቅልቀው
የዚህን ከዚያኛው እንዳልደባልቀው

496. ጅል የወደደና ፎረ ፎር ያረሰ
ዘላለም ይኖራል ደም እንዳለቀሰ

497. አባይ ውሀ ሞልቶ ግንድ ያገላብጣል
ከተለዩ ወዲያ ምን ያቅበጠብጣል

498. አጭር ምን ያረጋል የክራር ገበታ
እረጅም ነው እንጂ ተቋጥሮ ሚፈታ

499. እንኳን የአንተው ጎጆ የኑግ አገዳው
ቆርቆሮ ይፈርሳል ጣሊያን የሰራው

500. አባይ ውሀ ሞልቶ ዳር ዳሩ ይፈሳል
እንኳን ያንተው ጎጆ የእናት ሞት ይረሳል

501. አሮጌ ሙጎጎ የጎታ መክደኛ
በል እስከዚያው ድረስ በጎላዬ ተኛ

502. ካልሆነ ሰው ጋራ ተኝቶ ከማደር
የሽጋ ልጅ ኩታ ተንተርሶ ማደር

503. የጎንደር አገልግል መጠምጠሚያው ሹራብ
ጅል ይዞ ከመጥገብ ደና እያዩ መራብ

504. እንዳልበላ ፁሜ እንዳልያም ገድፌ
እንዲህ ብዬ ቀረሁ ባንተ ተለክፌ

505. ቀይማ ቀይነህ የበርበሬ ፍሬ
ኮሰኮሰከኝ እንጂ እንደ አባ ጨንሬ

506. እራሴን አመመኝ ጥርሴን ቁርጥማቱ
የአሮጌ በግ ሥጋ የበላሁበቱ

507. ቁልቋል ስረ ብዙ ላው ቅጠል የለው
ጅል የወደደ እንደሁ መላቀቂያም የለው

508. ምስጥ የበላው ጎመን መቀጠያም የለው
አቡዬ ፃዲቁ ትዳርህን ያብነው

509. ቢጠሩት አይሰማ ቢጠቅሱት አያይ
ይህማ ዳንግሌው በጉ አይደለም ወይ

510. አያበቅለው የለ ሰኔ እና ግንቦት
አክ እንትፍ እናቴ ምኑን በላሁት

511. ሸጋ ልጅ አልኩ እንጂ አጥፌ ምለብሰው
ጅልማ መች አጣሁ የማንከረፍፈው

512. ይህንን አድርገው ማማቱን ተውና
ዝም ብለህ ተቀመጥ ስሙ ባል ነህና

513. የበርበሬ ጥላ አያስጥልም ጸሐይ
እኔስ ሰው መስለኸኝ ሰገባህን ሳይ

514. ባል እስከዚያው ድረስ እንሁን ጓደኛ
አንተም ባሌ አይደለህ እኔም ልቤ አይተኛ

515. እስከዚያው ነው እንጂ እስኪነጋ ሌቱ
ስፍራዬም አይደለ የተኛሁበቱ

516. እንደ ደና ጉበዝ ሱሪውን ከፍ አረጉ ሲወጣ ከቤቱ
ዛሬ ሰው አይተርፍም ትላለች እናቱ

517. አዳራሹ ሰፊ መሀሉ ቆርቆሮ
ሳጫውተው አደርኩ ያገርን ደንቆሮ

518. አዳራሹ ሰፊ መሀሉ ከርፋፋ
አስማርኮኝ ነበረ ቁሞ እያንቀላፋ

519. ይኸ ነው ሰውየው ግልድም የታጠቀው
እንደ እመጫት ማልዶ እሳት የሚሞቀው

520. ድሮ ነበር እንጂ እኔ ምወድህ
የወፍጠጪ መፋቂያ ሳይመስል ድድህ

521. እንዝርት ያለ ወልቆ አይሽከረከርም
ይዘገያል እንጂ እኔ ለአንተ አልቀርም

522. ጎብለል ጎብለል ቢል ጎብላሌ በበሩ
ጎመን ጎመን አለኝ የቤቴ ሰው ሁሉ

523. ፍየሊቱን አርደው ይሏታል ብራና
የቤቴን አስጠላኝ ጡር አይበለኝና

524. ማሽላ ዘርቼ ጥንቅሽ አልዘራሁም
ልቤን የሚመታ ሰው አላገኘሁም

## 5.ክፋትና ደግነትን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

### 5.1 የሰውን ክፋትና ደግነት የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች

525. እንግዲህ ለባዳ እንግዲህ ለሰው
አፌም  አይናገር ሆዴም አይረሳው

526. ኧረ ሰው ኧረ ሰው ሰው አስቸገረኝ
ሲናገሩ አፈኛ ዝም ሲሉ ሞኝ

527. ሰው ያለወገኑ ከብት ያለ መንጋው
እንቅፍ ያለ ለታ ደጋፊም የለው

528. ኧረ እኔስ ሰውን ሳምነው በቀረብኝ
የሰራሁትን ቤት እያፈረሰብኝ

529. ወይ አልተቀረጥኩት ወይ አልተበጠረ
የእኔ እራስ አቻቻል በጣም አስቸገረ

530. ብሰራው አመመኝ ብላጨው ከፋኝ
አንድ ሰው እኮ ነው የሚያስቸግረኝ

531. ዘንድሮ አዝመራዬ ተልባ ሆኖብኝ
ለጀለ አላዘንኩም ሰው ለሳቀብኝ

532. አዳራሹ ቤቱ ጠንበለል ማገሩ
ሰተት ብለህ ግባ ይሸበር መንደሩ
ምን ያሸብረዋል የመንደሩ ሰው
የመጣውን ዕዳ እኔ ልችለው

533. አትታመም አይኔ ሆዴ አመል አታውጣ
የዛሬ ዘመን ሰው ጉድፍም አያጣ

534. ጨጓራና ጉበት ጥሩ ምግብ ነው
ሆድ የሚያሻክረው ክፉ ምላስ ነው

535. እንዳሻቸው ያርጉኝ ለሰው ምንቸገረኝ
አምተው መቅረት እንጂ ስጋዬን አይበሉኝ

536. አውቄ ነው እንጂ የማነክሰው
እኔ ራሴን ችዬ ቁሜ እምሄድ ሰው

537. ኧረ ላስታ ላስታ ኧረ ቆቦ ቆቦ
አይምሮ ነው እንጂ ሰውን ሰው ጠብቆ
538. ውሀው ወራጅ ወራጅ ድንጋው ቀሪ ቀሪ
ሰው ከየት ይገኛል የልብ አናጋሪ

539. እየጨነቀው ነው እያጣው ብልሀቱን
ወዳጅ የሚያደርገው ሰው ሁሉ ጠላቱን

540. አመሉ ነው ድሀ ሲሉ ሰማኒቸው
ጥሎባቸው እንጂ የዘር የለባቸው

541 ወንጭፍ ተጠቅሎ ይውላል ከማማ
ከአገር ሆድ ይሰፋል ላስቻለው ሰው እማ

542. መድፍ ተቀይዶ መትረየስ ሲያጎራ
ልብ አይታመንም እንኳን ባልንጀራ

543. ኧረ ሚዛንማ ጥጥም ይመዘናል አካል ይመዘናል
የማይመዘነው ሰው እንዴት ይሆናል

544. ጤፍ እንጀራው እንጂ አይበላ እሸቱ
አይታማ የለም ሰው በልጅነቱ

545. ኧረ ሰው ኧረ ሰው ኧረ የሰው ነገር
ልቤ ይዟል ተንኮል አፌ ባይናገር

546. አካል ይመዘናል ሰው አይመዘንም
እየሰሙ መቻል ያንንም ያንንም

547. እኔ ማስብበት ሳለ ልቦናዬ
እስኪ በሰው ነገር አትለቅ ገላዬ

548. ደገኛ በሬውን ይለዋል ቢራራ
ሞትና ኩነኔ ለሰው ባልተሰራ

549. ውሀው ወራጅ ወራጅ አሸዋው ቀሪ ነው
በልብሽ አስቢው ሰውስ ምቀኛነው

550. ማሰብ ምን ሊሆን ነው መበሳጨት ከቶ
አምላክ ያለው ላይቀር ሰው ያለው ቀረቶ

551. እኔው ተጎንብሼ እኔው እቃናለሁ
የሰውንስ ነገር አምና አይቼዋለሁ

552. የድንጋይ ሙገጫ አይነቃነቅም
ሰው በሰው ይስቃል የራሱን አያውቅም

553. እብዷት አሉኝ ሰዎች ሙሪት ሙሪት
መቼ ተወልጄ መቼ ልጨምት

554. የዛሬ ዘመን ሰው ነጠላ ነው ልብሱ
መሬት መሬት ብሎ ሊወጣ ነው ነብሱ

555. መስታዊት ይገዛል ሞኝ የሰው ልይ
መሰንበት አይደል ሁሉን የሚያሳይ

556. ላሚቱ ላም ወልዳ ተኝታለይ አራስ
እንግዲህ ጀመረኝ የዚህ አገር ምላስ

557. ሳንቲምና ወንድም ከመንገድ ወድቀው
ሳንቲሙን አነሳ የአሁን ዘመን ሰው

558 ይታክታል አሉ ሞኝ የሰው ልጅ
እሚሞት አይመስለው እሚኖር ነው እንጅ

## 5.2 የጎባንን ክፋት የሚገልፁ ቃል ግጥሞች

559. "አህያ" ነሽ አሉ ነይ ኩር ነይ ኩር
አንቺን የወደደ ነብሱም አይማር

560. እራሴን ልሰራ ቀጭን አፈሳሶ
ጎባኔ ሞታብኝ ልሄድ ነው ልቅሶ

561. ምነው ገለፈጥሽኝ ከጓዳ እንዳወጣ
ከየት ሂደሽ ኖሮል አጋድሞሽ ሲመጣ

562. ኧረ ያንቺው ጭንስ ቀጣፊ እንደሚዛን
ጅሉንም ድንቁንም አንድ አድርጎ ይይዛል

563. በሞቴ አትቆጪ እቴ ባልንጀራ
እንዴት ይጣፍጣል የስርቆት እንጀራ

564. ሽጋዬ በቤትህ አሞራ ይዞራል
ያች ከርፍፋ ሚስትህ ሙታልህ ይሆናል

565. አለች ከርፈፍ ከርፈፍ ምን ሰማች አመዱት
ላንቺ ብቻ ነው ወይ እናቱ ሲወልዱት

566. እኔ ምን አጠፋሁ ውላታ ዋልኩልሽ
የዶመውን ካራ ሞርጄ ላኩልሽ

567. እኔስ ለጎባኔ የምመኝላት
እጥር ያለች ቁምጣ ሽልብ ያለች ሞት

568. ከቤታችን በላይ ያለች ጥቁር ዶሮ
እባክህ አሞራ ውሰድልኝ ቶሎ

569. እንጨት እሰብራለሁ እንጨት አኸር ቃና
"እውሪት ደርጋሚት" ባንቺ ሰው ሊቀና

570. ክትክታ ፍሬውን ይሉታል ብሎኬት
አያወጣው የለ ጎባንና ወንፊት

571. የዘንድሮን ነገር እግዚአብሔር ያብጀው
ሰረጌን እየበላሁ ቤቴን ፍየል ፈጀው

572. አንቺ የእኔ ጎባን ወደሊቱ አርባጫ
መቀነት አይበቃት ምራን ከመርገጫ

573. ይህ የበሰበሰው የወደቀው ግራር
ወትሮም የቀና ሰው ብዙ ይናገራል

574. ባልሽ እኔን ወዶ አንቺ እኔን ጠልተሽ
እንደ ሽሮ ዱቄት ብን ብን ያድርግሽ

575. ሞያሽና አመልሽ ልቡን ያተከረው
ወደእኔ የመጣ ባልሽ ማን መከረው

576. አውራ ቢዘሩት ተመልሶ አውራ
አንቺ ከወፍጮ ስር ባልሽ ከእኔ ጋራ

577. አልጋውን ምንጣፉን እኔ ይገፍዋለሁ
በዱር መደፋቱን ለአንች ሰጥቻለሁ

578. ቡክብካ ብትሞቂ ባመድ ብትነጪ
ሰውዬው አይመጣም አንቺ ከእኔ አትበልጪ

579. ጎባኔ ታማብኝ እንደ ውድቂያ አርንት
አምጡልኝ በቶሎ እኔ ልገማት

580. ፈጭተው ካላኖሩ ከዱቄት እቃዎ
ጎባኔ ይሙቱ አይለምድም ባልዎ

581. የቆላው ነጭ ጤፍ የደጋው ግንቦቴ
ባሌ እንደምን ሳመሽ ንገሪኝ በሞቴ

582. እንዲህ አድርጎ ሳመኝ ብዬ ብነግርሽ
ውስጥ አንጀትሽ አሮ ይስቃል ጥርስሽ

583. ደህና ወዶኝ ነበር በሚስቱ ላይ እኔን
በእኔ ላይ ሰው ወዶ ጉድ አሳየው አይኔን

584. ሚስትህን አሟታል እያላት ብርድ ብርድ
ይሻላት እንደሆን ሰማኒያዋን አውርድ

585. አላየልሽም ወይ ሸንዳራው አይንሽ
አልሰማልሽም ወይ ቀርፋፋው ጆሮሽ
እንደ ካባ ለባሽ ሲደርብብሽ

586. እውነትን መሰለሽ እኔን ትቶ ካንች
የአላየውን አይቶ ሊመጣ ነው እንጅ

587. እንዲህ ብሎ ነው ወይ የሰው ባል ሲቀሙ
ከወፍጮ ላይ ሆኖ አሻሮ እየቃሙ

588. ውሻ ቁጭ ቁጭ ንጥር ቅቤ ላሽ
እሱ ጠላሽ እንጂ እኔ ምን ላርግሽ

589. እራቱን አብልቼ የምሰድልሽ
እህልን አይበቅልም እቴ ባገርሽ

590. አሻግረሽ አትይኝ እንደ ነፍሰ ገዳይ
ባልሽን እንደሆን ክተችው ከሙዳይ

591. ተይ አተነካኪኝ አትስደቢኝ እንጂ
እኔን ጠርቻለሁ እራሱ መጣ እንጂ

592. ከፍ አርጊው ቀሚሱን አታስረዝሚው
መወደድ መጠላት በውቃቤ ነው

593. በረት መዳመጫ ሁሉ የሚዋሰው
አንቺ ጉባን ብሎ አይቀናም ደና ሰው

594. ሰርቼ ጋግሬ እንካ ብላ ስለው
የያዘው ቁራኛ ቋንጣ ቋንጣ አሰኘው

595. የቋንጣን ጣምና ያወቀ ያውቀዋል
የክረምት አዛባን ማን ግባ ይለዋል

596. ደልደል ያለ ገላ ከዚህ ተቀምጦልህ
ከደረቀው እንጨት ላይ ምን አደላደለህ

597. ደልደል ያለ ገላ ከዚያ ቢቀመጥ
ከቋንጣ ወጥና ከዱባ ምረጥ

598. የሰውን አሮጌ እጠቅም ብለህ
የሰውን ትዝንትዝ እጠቅም ብለህ
ያንተን ቀጭን ኩታ ታስወስዳለህ

599. እኔም ሴት ነኝ እሷም ያው ሴት
ምን ወስደው ይሆን ወደ እሷ ቤት

600. ይቺን የዱር ሾላ ዝንጀሮ ለቀማት፣
ሞት አይሻልም ወይ አንተን ከመቀማት

601. እረፊ አንቺ ሰው ከእንግዲህ በኋላ
ለሁላችን ይሁን ሁሉን ሳያደላ

602. ተኩለሽ ተቀብተሽ ብትቁለጨለጪ
እኔ አልለቅልሽም አርፈሽ ተቀመጪ

603. የማጀቱ ናዛዥ የድስት አካፋይ
የእኔ ወደረኛ መሆንሽ ነው ወይ

604. የወጠንሽበቱ እንዝርቱ የእኔ ነው
ቶሎ ቶሎ ብለሽ ብትለቂልኝ ምነው

605. የእኛማ ቀርፋፋ የሰራችው ዶሮ
ኩክ ብሎ ሄደ መግላሊቱን ሰብሮ

606. ምኑንም ምኑንም ትለቃቅሚና
ውሻው ሲጮኽ ያድራል ኩርፌያሽን ሲሰማ

607. አመለ ልክስክስ አመለ ውዳቂ
ሰንጋ ፈረስ ታስሮ "አህያ" ናፋቂ

608. ባልሽን እሰሪ እንጂ ባውራ ጠፍረሽ
የእናቴ ልጅ ነሽ ወይ የምታመንልሽ


609. አይ የእኔ ጎባን የሰራችው ሽሮ
በርበሬ አበቀለ ባለሁለት ጆሮ

610. አሸሽ ወለሽ ብዬ ልሄድ ነው ሌላ አገር
ጎባን አለኝ ብዬ ለሰውም አልናገር

611. እንዝርቴ ድባቡ ዛቢያው መነመነ
ባሌስ ባሌ ነበር የሰው ባል ባልሆነ


612. ከአሸዋ መሬት ላይ ይበቅላል ባቄላ
ምን አረግሽው ይሆን ወደ አንቺ እያደላ

# አባሪ አራት - ካርታዎች




የእብናት ወረዳ ካርታ ከእብናት ወረዳ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የተገኘ፡፡


( በ04/05/05 እብናት በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )




የደቡብ ጎንደር ዞን ካርታ ከደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተገኘ ።


(በ06/06/05 ደብረታቦር በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )

## አባሪ አምስት - ፎቶግራፎች





ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ሞላ ዘገየ፣ታከለይ መኮንን፣ አረጋይ ድሌ፣ ወንድማገኝ ሞላ፣ ዘርፌ መኮንን፣ ሆነልኝ ደጀን ሆነው የቡድን ውይይት ሲያደርጉ የሚያሳይ ፎቶግራፍ



አቶ አብቦ ሹመት የእብናት ወረዳ

አስተዳደር ጽ/ቤት ሀላፊ

(በ04/05/05 እብናት በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ )



ከግራ ወደ ቀኝ ወንድማገኝ ሞላ፣ አበባ ፍስሐ፣ ቄስ ደረጀ አያናው፣ ቄስ ተሾመ ነጋሽ እና ቄስ ወርቁ ገላዬ የቡድን ውይይት ሲያደርጉ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

(በ19/05/05 አዲያ ቁርቋራ ቀበሌ በአጥኝው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)



ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ቡላድ አየለ፣ አቶ አለሜ ተገኝ፣ አቶ አለቤ ጥሩነህ እና ቄስ አሰፋ ይግዛው የቡድን ውይይት ሲያደርጉ የሚያሳይ ፎቶግራፍ

(በ21/05/05 ግብጻዊት ደብር ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)